# የሙስና ወንጀል ምርመራ

## በፌደራል ሥነምግባር እና ፀረ-ኮሚሽን የተዘጋጀ

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሰኔ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

## ምህጻረ ቃላት

**የወ/መስ/ስ/ሕ**---የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ህግ

**የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/አ**----የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአት አዋጅ

**በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ**--------የፍትሀብሄር ስነስርአት ህግ

**SMR**---------------በተባበሩት መንግስታት የእስረኞች አያያዝ አነስተኛ ደንቦች (The United Nation Standard Minimum Rules for the Treatment of Prisoners)

**DNA**-------------------deoxyribonucleic acid

**OECD**-----------The Organisation for Economic Co-operation and Development

## ማውጫ

1. የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወደምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን ....7
1.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ ....7
1.2. የምዕራፉ አጠቃላይ አላማ ....7
1.2.1. የምዕራፉ ዝርዝር ዓላማዎች ....7
1.3. የምዕራፉ ይዘት ....7
1.4. በጥቆማ ላይ የተመሰረተ የሙስና ወንጀል ምርመራ ውሱንነት ....8
1.5. ጥቆማ የማቅረብ መብትና ግዴታ ....9
1.5.1. ጥቆማን መመዝገብ እና ከጠቋሚው ሊገኝ የሚችለውን መረጃ ማሰባሰብ ....10
1.6. ጥቆማ ሲቀርብ በጠቋሚዎች ሊመጣ ከሚችል አደጋ ስለመጠንቀቅ ....13
1.6.1. ጠቋሚዎችን ስለመጠበቅና ከለላ ስለመስጠት ....16
1.6.2. ምርመራ እንዲደረግ ስለመወሰን ....18
1.7. በሙስና ወንጀል ከሚያስከስሱት ወንጀሎች ከባድ የህግ ጥሰት ሊባሉ የማይችሉት የትኞቹ ናቸው? ....19
2. የሙስና ወንጀል ምርመራ ....25
2.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ ....25
2.2. የምእራፉ አጠቃላይ ዓላማወች ....25
2.2.1. የምእራፉ ዝርዝር ኣላማዎች ....25
2.3. የምእራፉ ይዘቶች ....26
2.4. የወንጀል ምርመራ ምንነት ....26
2.5. የወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው አጠቃላይ መርሆዎች ....27
2.6. የምርመራ እቅድ ማዘጋጀት ....32
2.7. ማስረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር መተንተን ....35
2.8. ምስክሮችን ስለመለየት የምስክሮችን ቃል ስለመቀበል ....42
2.9. ንብረት ማሳገድ፣ማስከበርና ማስተዳደር ....49
2.10. ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ዋስትና፣ጊዜቀጠሮ እና የተጠርጣሪን ቃል ስለመቀበል ....55
2.11. የምርመራ ራፖርት ማዘጋጀትና ለውሳኔ ለአቃቤ ህግ ማቅረብ ....66
ማጣቀሻ ጽሁፎች/ዋቢዎች ....75

# አጠቃላይ መግለጫ

## መግቢያ

የሙስና ወንጀልን ጥቆማ በመቀበልና በመመርመር የህግ ማስከበር ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ስለሙስና ወንጀል መረጃ አቀባበልና አመዛዘን፣ የትኞቹ የሙስና ወንጀሎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ምርመራ ሊደረግባቸው እንደሚገባ፣ እንዲሁም የሙስና ወንጀል ምርመራ አጀማመር፣ ማስረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ ማድረግን በተመለከተ አቅማቸውን በየጊዜው ማሳደግ ሙስናን የመመርመርና የማጋለጥ ስራቸውን ውጤታማነት ስለሚጨምር አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ የስልጠና ሞጁል ዝግጅት ግብዓት ለማሰባሰብ በተደረገ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ወቅት በተደጋጋሚ ከተነሡ ነጥቦች ወይም ጉዳዮች መካከል የሙስና ወንጀል ጥቆማ ተቀባዮች እና የሙስና ወንጀል መርማሪዎች በጥቆማ አቀባበል፣ በጠቋሚዎችና ምስክሮች ቃል አቀባበልና መስተንግዶ፣ ተጠርጣሪን ስለመያዝና ቃሉን ስለመቀበል፣ እንዲሁም በአጠቃላይ በማስረጃ አሰባሰብ የአቅም ክፍተቶች ያሉባቸው ስለሆነ በሁሉም የጥቆማ አቀባበል እና የሙስና ወንጀል ምርመራ ሂደት የእውቀትና የክህሎት ስልጠና ተዘጋጅቶ ሊሰጣቸው እንደሚገባ አመላክቷል፡፡ ይህ ሞጁልም የተዘጋጀው በዚህ የዳሰሳ ጥናት የተሰባሰበውን ግብዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ይህ ሞጁል ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በክፍል አንድ ስለጥቆማ አቀባበል፣ የታወቁ እና ያልታወቁ ጠቋሚዎችን ስለማስተናገድ፣ በጥቆማ አቀባበል ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች፣ ጠቋሚዎችን ከቂም በቀል እርምጃ ስለመጠበቅ እንዲሁም ምርመራ ለማድረግ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስለሚመረጡበት ሁኔታ የሚዳስስ ሲሆን፣ በክፍል ሁለት የወንጀል ምርመራ አጠቃላይ መሰረተ ሀሳቦች፣ ስለምርመራ እቅድ ዝግጅት፣ የሙስና ወንጀል ማስረጃዎች መገለጫዎች፣ ማስረጃዎች የት ሊገኙ እንደሚችሉ፣ እንዴት ማሰባሰብ እንደሚቻል፣ የምስክሮች አመራረጥና ቃል አቀባበል፣ ስለብርበራና ፍተሻ፣ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ንብረትን ስለማገድና ማስተዳደር፣ የተጠርጣሪዎች አያያዝ፣ የዋስትና መብትና ጊዜ ቀጠሮ፣ የተጠርጣሪዎች ቃል አቀባበል እንዲሁም የምርመራ ሪፖርት ስለማዘጋጀት የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

## ስለሥልጠናው ይዘቶች አወቃቀር  እና የስልጠና ስነ-ዘዴ

ሥልጠናው የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ በሁለት ምእራፎች የተከፈሉ ይዘቶች ተካተውበታል፡፡ የመጀመሪያው ምእራፍ የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወ ደምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን

የተመለከተ ነው። ሁለተኛው ምእራፍ የወንጀል ምርመራ አጠቃላይ መሰረተ ሀሳቦችን የተመለከተ ነው።

ሠልጣኞች በሥልጠናው ሂደት፣ የጎላውን ድርሻ ወስደው፣ ጥያቄዎችንና የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት፣ በጥያቄዎች ዙሪያ በመወያየት፣ ተጨማሪ የሐሳብ ግብአቶችን በማምጣት፣ ተመክሮዎችን በማካፈል ሃሳቦችንም በማፍለቅ የእርስ በእርስ ተሞክሮዎቻቸውን በመለዋወጥ በንቃት የመሳተፍ እድል በመፍጠር መልኩ ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡በዚህም ሰልጣኞች በዕለት ከዕለት የስራና የሙያ ኃላፊነትን ሲያከናውኑ ሙስናና ብልሹ ተግባራትን በመከላከል የላቀ ሚና እንዲወጡ ይጠበቃል።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሥሩ ንዑሳን ርእሶችን ያቅፋል። አንድ ርእስ በማነቃቂያ ጥያቄዎች ይጀምራል። ጥያቄዎቹ የሠልጣኞችን ተሳትፎ የሚያበረታቱ ናቸው። ከማነቃቂያ ጥያቄዎቹ ቀጥሎ አጫጭር ማብራሪያዎች ይቀርባሉ። በየምዕራፉ መጨረሻ አስረጅ ናሙናዎች እና የማጠቃለያ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህ ጥያቄዎች፣ ሠልጣኞች የተወያዩባቸውን ሐሳቦች በርግጥ በተገቢው ደረጃ መረዳታቸውን የሚፈትሹ ናቸው።

ስልጠናው በአቀራረቡም **አሳታፊ የሥልጠና ሥነዘዴን** የተከተለ ነው ሲሆን በዚህም ስነዘዴ፡-

- እያንዳንዱ ንዑስ ርዕሶችን የማነቃቂያ ጥያቄዎች ላይ ሰልጣኞችን በግልና በአነስተኛ ቡድን ወይም በጎንዮሽ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በንቃት ማሳተፍ
- በጉዳዮች ላይ ማብራሪያዎችን መስጠት፣
- በአስረጅ ናሙናዎች እና በምዕራፉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ውይይት ማቅረብ፣
- ሰልጣኞችን የነቃና ሳቢ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታን ማመቻቸት፣

ስለሆነም በመወያያ ጥያቄነት እየተሰጡ በቡድን ጥልቅ ውይይቶች በማድረግ መሠራት የሚኖርባቸው መሆናቸውን ከወዲሁ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

### የሥልጠናው አጠቃላይ መገምገሚያ ስልት

በዚህ የስልጠና ሞጁል እያንዳንዱን አላማ ሰልጣኞች በሚገባ ስለመገንዘባቸው እና ስለመረዳታቸው እና በስልጠናው የተቀመጠውን ለውጥ ስለማሳካታቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ዘዴዎችን የምንጠቀም ሲሆን ፡-

1. ስልጠናው ከመጀመሩ በፊት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለመገምገም የቅድመ ስልጠና ግምገማ ቼክሊስቶች በሰነዱ ላይ አባሪ የተደረገውን በመምረጥ ግምገማ የሚካሄድ ይሆናል፡፡
2. በስልጠናው ጊዜ ሰልጣኞች በማነቃቂያ ጥያቄዎችን እና በምዕራፉን የማጠቃለያ ጥያቄዎች የሚገመገሙ ይሆናል
3. ከስልጠና በኋላ ሰልጣኞች የሚጠበቅባቸውን እውቀት እና ክህሎት ስለመጨበጣቸው የሚረዳ የመመዘኛ ጥያቄ ስልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላ በኮሚሽኑ የስልጠና ጥራትና ተገቢነት ዴስክ ስር በሰነዱ ዙሪያ በሚያዘጋጇቸው የጽሁፍ ፈተናዎች እና በድህረ ስልጠና ግምገማ ቼክሊስቶች መሰረት ሰልጣኞች የሚመዘኑ እና የሚገመገሙ ይሆናል፡፡

## የሞጅሉ አጠቃላይ አላማ

ሰልጣኞች በሙስና ወንጀል ምርመራ ሂደት ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮችን እና ለዓቃቢ ህግ እና ለፖሊስ ስለሚሚቀርቡ የምርመራ አተገባበሮችን በማወቅ ሙስና እና ብልሹ አሰራር እነዲከላከሉ ለማስቻል ነው፡፡

## የስልጠናው ተተኳሪዎች

በዚህ ሞጁል የሙስና ወንጀል በመመርመር እና በመክሰስ ስራ ላይ የተሰማሩ ፖሊሶች ፣አቃቤ ህጎች እና የሙስና ወንጀል መርማሪዎች የሚሰለጥኑበት ሰነድ ነው፡፡

## በሞጁሉ የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች

በዚህ የስልጠና ሞጁል የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ ዙሪያ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ያላቸው እና በዘርፉ የሰሩ (ማለትም በመርማሪነት ፣ በአቃቤ ህግነት) እና በኮሚሽኑ በዚህ ዙሪያ ያሰለጠኑ ሆነው ቢያንስ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የስልጠና ሞጁሉን ለመሸፈን የተዘጋጀ ግምታዊ የሰአት ድልድል

ይህንን የስልጠና ሞጅል ለማሰለጠን ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው የስልጠና ፕሮግራም ውስጥ የሚካተት ሲሆን ለእያንዳንዱ የሞጁሉ ምዕራፍ የተሰጡት ሰአቶች ግምታዊ ሰአቶች ናቸው፡፡ ስልጠናው ይሰጣል ተብሎ የተገመተው **አንድ ቀን ተኩል(ከግማሽ)** ሲሆን በአማካይ በአንድ ቀን የስልጠና ውሎ ውስጥ **6 ሰዓት** ያህል ለስልጠና ይውላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በመሆኑም

ለዚህ የስልጠና ሞጁል  አጠቃላይ የተሠጠው ግምታዊ ጊዜ  9፡00 ሰአት ሲሆን ለእያንዳንዱ ምዕራፍ የተሠጠው ሠዓት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ❖ ምእራፍ አንድ የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወደምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን(የተሠጠው ግምታዊ ሰዓት 3፡30)
- ❖ ምእራፍ ሁለት የሙስና ወንጀል ምርመራ (የተሠጠው ግምታዊ ሰዓት 5፡30)

# ክፍል አንድ

## 1. የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወደምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን

### 1.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ

በዚህ ክፍል የሙስና ወንጀል ጥቆማ ስለመቀበልና ምርመራ እንዲደረግበት ስለመወሰን ይቀርባል፡፡ በዚህም ጥቆማ ስለማቅረብ መብት እና ጥቆማ ስለማቅረብ ግዴታዎች፣ ጥቆማ ሲመዘገብ ሊደረጉ ስለሚገባቸው ተግባራት፣ በጠቋሚዎች ፍላጎት ላለመመራት ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች፣ ለጠቋሚዎች ከለላ ስለመስጠት እና ምርመራ ለማድረግ ለመወሰን ከግምት ሊገቡ ስለሚገባቸው ነጥቦች ይዳስሳል፡፡

### 1.2. የምዕራፉ አጠቃላይ አላማ

የሥልጠናው ተሳታፊዎች የዚህን ምእራፍ ስልጠና ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ❖ ሰልጣኞች በሙስና ወንጀል ምርመራ ሂደት  ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ያውቃሉ፡፡

#### 1.2.1. የምዕራፉ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ምዕራፍ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡እነርሱም፡-

- ጥቆማ የማቅረብ ግዴታ ያላቸው እነማን እና በምን ጉዳይ ላይ እንደሆነ ይዘረዝራሉ፡፡
- ጥቆማ ሲቀርብ ከጠቋሚው ሊሰባሰብ ስለሚገባው መረጃዎች ይገልጻሉ ፡፡
- ጥቆማ አቅራቢ የምርመራውን ስራ እንዳያዛባ ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ያብራራሉ፡፡
- ለጠቋሚዎች ከአደጋ ለመጠበቅ ከለላ ስለመስጠት ትክክለኛ አሰራርን ይተገብራሉ፡፡
- የቀረበ ጥቆማ ወደምርመራ ለመግባት ምን መስፈርቶች ከግምት ሊገቡ እንደሚገባ ይለያሉ፡፡

### 1.3. የምዕራፉ ይዘት

ይህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ይዘቶችን ያካትታል፡፡

- በጥቆማ ላይ የተመሰረተ የሙስና ወንጀል ምርመራ ውሱንነት
- ጥቆማ የማቅረብ መብትና ግዴታ
- ጥቆማን መመዝገብ እና ከጠቋሚው ሊገኝ የሚችለውን መረጃዎች ማሰባሰብ
- ጥቆማ ሲቀርብ በጠቋሚዎች ሊመጣ ከሚችል አደጋ ስለመጠንቀቅ

- ጠቋሚዎችን ስለመጠበቅና ከለላ ስለመስጠት
- ምርመራ እንዲደረግ ስለመወሰን

### 1.4. በጥቆማ ላይ የተመሰረተ የሙስና ወንጀል ምርመራ ውሱንነት የማነቃቂያ ጥያቄ

1. ከሚታወቅም ሆነ ከማይታወቅ ጠቋሚ ወንጀል ስለመሰራቱ ጥቆማ ሲቀርብለት የጥቆማ ተቀባዩ ምን እንዲያደርግ ይጠበቃል ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. ከሚታወቅም ሆነ ከማይታወቅ ጠቋሚ ወንጀል ስለመሰራቱ ጥቆማ ሲቀርብለት የጥቆማ ተቀባዩ ምን እንዲያደርግ ይጠበቃል ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. ጥቆማ ሲቀርብ በጠቋሚዎች ሊመጣ ከሚችል አደጋ እንዴት ራሳችሁን ትጠብቃላችሁ?

የሙስና ወንጀል (በቀጥታ እንደ ሌሎች ግለሰቦችን የሚጎዱ ወንጀሎች) ወዲያውኑ ተጎድቻለሁ ብሎ የሚያመለክት ተጎጂ ወይም ሰለባ ስለሌለውና የሚጠቁም ባለመኖሩ ብቻ ሳይታወቅ ተደብቆ ሊቀር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በጥቆማ ላይ ብቻ የተመሰረተ የሙስና ወንጀል ምርመራ ስራ ሁልጊዜም ቢሆን በሺዎች በሚቆጠሩ ጥቃቅን ጥቆማቸው የስራ ብዛት በመፍጠር በዋና እና ውጤታማ ጉዳዮች ላይ የማተኮር አቅሙን በመፈታተን፣ የጉዳይ አስተዳደር ስራውም አስቸጋሪና ቢሮክራሲያዊ በመሆን ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ይልቅ በትናንሽ ጉዳዮች አቅሙ ተወጥሮ ከረጅም ጊዜ አንጻር ውጤታማነቱ ጥያቄ ውስጥ እንደሚገባ እና በህዝቡ ተአማኒነት እንደሚቀንስ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡[1]

ከዚህ አንጻር በኢንተለጀንስ መረጃ ማሰባሰብ ላይ የተመሰረተ ማለትም ጥቆማዎችን ወይም ክሶችን ሳይጠብቅ ወንጀል ሊሰራባቸው ይችላል ተብለው በሚገመቱ አካባቢዎች የመረጃ ማሰባሰብናማጠናቀር ስራ ላይ በተመሰረተ መልኩ የወንጀል መሰራት ምልክቶች ሲኖሩ እነዚህን በማስረጃ አዳብሮ ለክስ ማቅረብ ወይም የወንጀል ስራ ዝግጅቶችን ቀድሞ በመድረስ ማክሸፍን ያካተተ የምርመራ ስራ ቢሆን ውጤታማ እንደሚሆን ይመከራል፡፡በተለይም በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ መደበቅ እና ከገቢ በላይ ሀብት ማካበት የመሳሰሉት ከባድ የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን የማጋለጥና ለፍርድ የማቅረብ ስራ  በምርመራ ስራ ካልተደገፈ ውጤታማ የመሆን እድሉ በጣም አናሳ ነው፡፡

[1] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption,p.11

የሙስና ወንጀል ምርመራ የሚጀምረው በአብዛኛው ጥቆማ በመቀበል አልፎ አልፎም በኦዲት ግኝቶች መሰረት እና በሚደረጉ የጥናት ስራዎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡በኢትዮጵያ እስካሁን ባለው ልምድ በዋነኛነት የሙስና ወንጀል ምርመራ የሚጀምረው በጥቆማዎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡

### 1.5. ጥቆማ የማቅረብ መብትና ግዴታ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. የወንጀል ክስ ጥቆማ ለማቅረብ ከጠቋሚዎች ምን ይጠበቃል?
2. ጠቋሚዎች የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ጥቆማ ማቅረባቸው የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

በመሰረቱ የወንጀል ክስ ማቅረብ የማንም ሰው መብት ነው፡፡ ይህ ማለት ወንጀሉ ስለመፈጸሙ የሚያውቅ ወይም ያየ ወይም መረጃ ያለው ሰው ፖሊስ ዘንድ ቀርቦ ለማመልከት መብት አለው ማለት ነው፡፡ በተወሰኑ የወንጀል ጉዳዮች ግን ስለወንጀሉ ያወቀ፣የጠረጠረ የሰማ መረጃ ያለው ጥቆማውን ማቅረብ መብት ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡ አለመጠቆም ያስጠይቃል ማለት ነው፡፡[2]

ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በተሻሻለው የፌዴራልና የጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 26 የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን ስለሙስና ወንጀል መረጃ ካለው ሊጠቁም ግዴታ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 27(8) ይህንን ሀላፊነቱን ሳይወጣ የቀረ እስከ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል እስራትና በመቀጮ ሊቀጣ እንደሚችል ተደንግጎ እናገኛለን፡፡[3] ስለሆነም የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ እያወቀ ሳይጠቁም ቀርቶአል በሚል ጥቆማ ቢቀርብ ጉዳዩ ተመርምሮ በማስረጃ ከተረጋገጠ የሚያስከስስ እና የሚያስቀጣ ነው ማለት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በጸ/ሙ/ስ/ስ/ማ/ሕግ አንቀጽ 50 እንደተመለከተው በህግ በቃለመሀላ ወይም በስምምነት ማስረጃን በምስጢር የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ማናቸውም ሰው ማስረጃውን አግባብ ላለው አካል በመስጠቱ ህጉን ቃለመሀላውን ወይም ስምምነቱን እንደጣሰ ያስቆጥረውል ተብሎ ተደንግጓል፡፡

---

[2]በወንጀል ህግ አንቀጽ 443

[3]አዋጅ ቁ. 433/97 በአዋጅ ቁ…1236/2013.የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን በተካው አዋጅ ተሻሽሎአል፡፡ ነገር ግን የተሻሩ ህጎች በሚለው አንቀጽ 24 ውስጥ በግልጽ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ጋር የሚቃረኑ ህጎች ተሸረዋል ይላል እንጂ፣ አዋጅ ቁ.433/97 ተሸሮአል አይልም፡፡ ስለሆነም በአዲሱ አዋጅ የሙስና ወንጀልን ስለመጠቆም የሚገልጽ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ የአዋጅ ቁ. 433/97 አንቀጽ 26 እና 28 ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

በስነስርአት ህጉ ሁለት አይነት ጠቋሚዎች እንደሚኖሩ ይደነግጋል፡፡ እነዚህም ለጥቆማ ተቀባዩ የሚታወቁ እና የማይታወቁ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

በስነስርአት ህጉ አንቀጽ 14 የወንጀል ክስ ያቀረበ ሰው ያቀረበውን ክስ ጥቆማ ተቀባዩ በጽሁፍ ከተቀበለ በኋላ ክሱን አንብቦለት ቀኑ ተጽፎ ክሱን ያቀረበው ሰው መፈረም እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ሁለተኛው አይነት ጠቋሚ ማንነቱን ሳያሳውቅ የሚጠቁም ነው፡፡ በስነስርአት ህጉ ቁ. 12 ማንነቱ ባልታወቀ ሰው ጥቆማ ሊቀርብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡እንዲሁም በጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አንቀጽ 49 ላይም ጠቋሚው ሳይታወቅ ሊያመለክት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ጠቋሚዎች የሀሰት ጥቆማ አቅርበው በተገኙ ጊዜ በወንጀል ህግ በተመለከተው መሰረት እንደሚቀጡ በስነስርአት ህጉ በቁጥር 18 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሆነ ብሎ ሌላውን ለመጉዳት የሚቀርብ የወንጀል ክስ ወይም የግል አቤቱታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 447 መሰረት ያስጠይቃል በማለት ይደነግጋል፡፡ስለሆነም ጠቋሚው ሳይታወቅ የሚቀርብ ክስ በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡ በአንድ በኩል ጠቋሚው ማንነቱ ስለማይታወቅ በሀሰት ክስ አቅርበሀል ተብሎ ሊከሰስና ሊቀጣ የሚችልበት ሁኔታ ስለማይኖር በሀሰት ሰውን ለመጉዳት ክስ ከማቅረብ የሚያስፈራው ወይም የሚያሰጋው ሁኔታ የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው ማንነቱን ደብቆ ክስ የሚያቀርበው ክስ ማቅረቤ ከታወቀ ወንጀል አድራጊው ወይም ተጠርጣሪው ይበቀለኛል ብሎ የፈራ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታዎች መርማሪውን(በጥቆማ ላይ የሚወስነውን አካል) ፖሊስ በሁለት ምርጫዎች ውስጥ እንደሚከቱት ግልጽ ነው፡፡ በአንድ በኩል ወንጀል አድራጊ እንዲጠየቅ በማድረግ ሕብረተሰቡን ከወንጀል ተግባር የመጠበቅና የመከላከል ምርጫ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ንጹህ ሰው ያለጥፋቱ ክስ ቀርቦበት ሰብአዊ መብቱ እንዳይጣስ የማድረግ ምርጫ ነው፡፡

### 1.5.1. ጥቆማን መመዝገብ እና ከጠቋሚው ሊገኝ የሚችለውን መረጃ ማሰባሰብ

የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አዋጅ አንቀጽ 49/51- ከታወቀም ሆነ ካልታወቀ ጠቋሚ የሚቀርብ ጥቆማ ሲኖር ጥቆማ ተቀባዩ ጥቆማውን የመመዝገብ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የወ/መ/ስ/ስ/ሕ ቁ.15 ጥቆማ የሚያቀርበው ሰው ወንጀለኛውን የማያውቀው ከሆነ ወንጀለኛውን ሊያሳውቁ የሚችሉ ልዩ ልዩ ምልክቶችን ሁሉ በዝርዝር መስጠት አለበት ይላል፡፡የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕግ ቁ.52/50 ደግሞ የሚታወቅ ከሆነ የጠቋሚውን ስም፣ የጥቆማውን ፍሬ ሀሳብና ጥቆማውን አስመልክቶ ስለተወሰደው እርምጃ መመዝገብ አለበት ይላል፡፡በወ/መ/ስ/ስ/ሕቁ. 25 ደግሞ

መርማሪው ፖሊስ ወንጀሉን የሚመለከቱትን ነገሮች ሁሉ ቀኑንና ዘመኑን የወንጀል አድራጊውን ስም ወይም መታወቂያውን የዋናዎቹን ምስክሮች ስምና አድራሻቸውን እንዲሁም የሚገኘውን ሌላ ማስረጃሁሉ የክስ አቤቱታ ካቀረበው ሰው ጠይቆ መመዝገብ አለበት ይላል፡፡ምርመራው ተጀምሮ ጊዜው በሄደ ቁጥር መረጃዎች የመጥፋት እድላቸው እየጨመረ፣ ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ሊጠፉ ተጠርጣሪዎችም ሊሰወሩ ስለሚችሉ ጥቆማ ተቀባዩ ወዲያውኑ ጥቆማው እንደቀረበለት ሊገኝ የሚችለውን መረጃዎችና ማስረጃዎች ሁሉ ከጠቋሚው ለማሰባሰብ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር ጥቆማ ተቀባዩ በምርመራ ስራ ወርቃማ ጥያቄዎች የሚባሉትን መሰረት አድርጎ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ እነሱም፣[4]

1. ማን? ተጠርጣሪ፣ ምስክር፣ ጠቋሚ፣ ተጎጂው ማን ነው? (ስሙ፣ እድሜው፣ አድራሻቸውን፣ የቅጽል ስም ካለው፣ ቀድሞ የወንጀል ተሳትፎ ወይም ሪከርድ ያለው መሆኑ፣ ዜግነት፣ የቤተሰብ አባላት እና በጉዳዩ ያላቸው አግባብ ወዘተ..)
2. ምን? የተፈጸመው ድርጊት ምንድነው? ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተጣሰው ስልጣን ምንድነው? የተገኘው የማይገባ ጥቅም ምንድነው? በወንጀሉ የገንዘቡ መጠን ምን ያህል ነው? በወንጀሉ ተጠርጣሪዎች ተሳትፎዋቸው ምንድነው? በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ምንድነው?
3. የት? የተፈጸመው ድርጊት የት ነው? በየትኛው መስሪያ ቤት ነው? የተገኘው የማይገባ ጥቅም የሚገኘው የት ነው? በሙስና የተገኘው ንብረት ወይም ጥቅም ወደየት ሄደ? ተጠርጣሪዎች ከየት ወደ የት ጉዞ አድርገዋል? ማስረጃው የት ሊገኝ ይችላል?
4. መቼ? ድርጊቱ የተከናወነው መቼ ነው? ወይም ከመቼ እስከመቼ የተከናወነ ነው?
5. እንዴት? ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታ እንዴት ነው? ከሀሳብ ወደተግባር እንዴት ተቀየረ ወይም አተገባበሩ ምን ይመስላል? ግንኙነት ሲያደርጉ የነበረው በምንድነው? በስልክ? ኢሜይል? ምስጢራዊ መገናኛ ቃላቶች? በሰዎች ግንኙነት ወዘተ..? ማለትም የወንጀል አድራጊዎችን ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀሙበትን እውቀትና ክህሎት ምንድነው? ተሳታፊዎች የወንጀሉን ፍሬ ለማጓጓዝ ምን አይነት ማጓጓዣ ተጠቅመዋል? መኖሪያ ቤት? መኪና? በምን አይነት እቅድ ነው የፈጸሙት?
6. ለምን? ወንጀሉን የፈጸሙት ምን ለማሳካት አስበው ነው? ያነሳሳቸው ምክንያት ምንድነው? የኑሮ ሁኔታቸው ምን ይመስላል?ከፍተኛ ወጪ ሲያወጡ ይታወቃሉ?

[4] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p. 84-88

ቤተሰቦቻቸው ወጪ አወጣጣቸው አኗኗራቸው ምን ይመስላል? ወንጀል የመፈጸም ዝንባሌያቸው ምንድነው? አዘውታሪ ወይም ደጋጋሚ ወንጀል ውስጥ የገቡ ናቸው?

7. ማስረጃዎቹ ሊጠፉ ሊሰወሩ የሚችሉበት እድል ወይም ክፍተት አለ ወይ?

እነዚህ መረጃዎች አንድም የምርመራ ስራውን የሚያቀሉት ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ምርመራው በምን አቅጣጫ መሄድ አለበት?ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄም አመላካች ሆነው ጠቋሚዎች በሚፈልጉት አቅጣጫ ብቻ ላለመመራት አስፈላጊ ጠቃሚ መረጃዎች ናቸው።

የፌዴራል ፖሊስ የሙስና ወንጀል ...የክስና ጥቆማ አቀባበል ..... ማንዋል በአንቀጽ 4(1) ጥቆማ ተቀባዩ ጥቆማውን በሚቀበልበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች ማጣራትና በተቻለ ማሰባሰብ እንዳለበት ያስቀምጣል፡-

1. የተፈጸመው ወንጀል ምን እንደሆነ፣
2. ወንጀል ፈጸመ የተባለው ተጠርጣሪ ማንነት፣ (ስም፣ ሙያ ወይም ስራ፣ አድራሻ፣ እድሜና የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ የስራ መደቡን)
3. ወንጀል የተፈጸመበት መስሪያ ቤት፣
4. ወንጀል ተፈጸመ የተባለበት ቦታና ጊዜ፣
5. በወንጀል የተጠቀሙ ወይም የተጎዱ ሰዎች፣
6. በገንዘብ ሊገመት የሚችል ከሆነ በወንጀል የተገኘ ጥቅም መጠን ወይም የደረሰ ጉዳት ግምት፣ ወይም ከወንጀል መፈጸም ጋር በተያያዘ በተደረገ ውል ብድር፣ ቀረጥ ወዘተ .... ያለው የገንዘብ መጠን፣
7. የሚታወቅ ከሆነ የተገኘው ጥቅም የሚገኝበት ቦታና ሁኔታ፣
8. የሚታወቅ ከሆነ በተጠርጣሪው ስም ያሉ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣
9. የጉዳዩን እውነተኝነት ሊያስረዱ የሚችሉ የሰነድ ማስረጃዎች የሚገኙበት ቦታ፣ ወይም ጉዳዩን የሚያውቁ ሰዎች ወይም ምስክሮች ስምና አድራሻቸው እንዲሁም ስልክ ቁጥራቸው፣
10. ጉዳዩን በተመለከተ ተጀምሮ ያለ ምርመራ መኖር ያለመኖሩን ወይም በጉዳዩ ላይ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ክርክር የተደረገበት ወይም ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን፣
11. የጠቋሚው ስም፣ የመኖሪያ፣ የሚሰራበት መስሪያ ቤት፣ የስልክ፣ የፋክስ አድራሻ፣ ጠቋሚው ስምና አድራሻውን ለመግለጽ ፈቃደኛ ካልሆነ ይህንኑ በሰነዱ ላይ መግለጽ፣

12. ጥቆማ አቅራቢዎቹ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ከሆኑ የሚያቀርቡት ጥቆማ የሂሳብ ምርመራና አስፈላጊው አባሪ ሰነዶች ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ማረጋገጥ፣ የሌላቸው ከሆነ አሟልተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

### 1.6. ጥቆማ ሲቀርብ በጠቋሚዎች ሊመጣ ከሚችል አደጋ ስለመጠንቀቅ

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. መርማሪዎች ጥቆማ ሲቀርብ ከጠቋሚዎች ሊመጣ ከሚችል አደጋ እንዴት ራሳችሁን ትጠብቃላችሁ?

ጠቋሚዎች በአብዛኛው ጊዜ በጥቆማው ጥቅም ያላቸው ማለትም የሚያገኙት ጥቅም ወይም የደረሰባቸው ጉዳት ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ በተለይም ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በጉዳዩ ፍላጎት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ምክንያቶች አሉ፡፡ ጠቋሚዎች ጥቆማ ከሚያቀርቡበት ምክንያቶች መካከል ለግላቸው የሚያገኙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት (ሹመት፣ የግዢ ክፍል ሀላፊ፣ ለመሆን)፣ ቂምበቀል መወጫ ለማድረግ፣ በወንጀሉ ተሳታፊ መሆናቸውን ለመደበቅ (Covering up personal involvement)፣ የወንጀል ሀላፊነቱን ወደሌላ ለማዛወር ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[5]ስለሆነም የምርመራ አቅጣጫውን እነሱ የሚፈልጉትን ግብ በሚያሳካ መልኩ እንዲመራ ጥረት ሊያደርጉ እና የእነሱ ፍላጎት መጠቀሚያ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጥቆማ ተቀባዮችም ሆኑ መርማሪዎች ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ስለሆነም ጥቆማ ሲቀርብ እና ሲመረመር ጠቋሚው እውነተኛውን መረጃ እያቀረበ ነው ወይስ የሀሰት መረጃዎችም ተደባልቀዋል? የተደበቁ ያልተገለጹ መረጃዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆን ወይ?ጠቋሚው ግለሰብም ይሁን ድርጅት (የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ህዝባዊ ድርጅት) ምን ሌላ አላማ ሊኖረው ይችላል?ጥቆማውን የሚደግፍ ወንጀል ስለመፈጸሙ ማስረጃዎች ይደግፋሉ? ተፈጸመ የተባለው ወንጀል በሪፖርት በቀረበው ጊዜ ነው? የወንጀል አፈጻጸሙ ጥቆማ (ሪፖርት) ያቀረቡት ሰዎች እንዳቀረቡት አይነት ነው? እና መሰል ጥያቄዎችን ማንሳትና የጥቆማውን አጠቃላይ ይዘት መመርመር ሁልጊዜም ሊዘነጋ አይገባም፡፡ ጥቆማ የሚያቀርብ ሰው በወንጀሉ ተሳታፊ ከሆነ እውነተኛው የወንጀሉ መረጃዎች ከሚገኙበት ቦታ ጥቆማ ተቀባዩን ወይም መርማሪውን ለማሳሳት ብዙውን ጊዜ ራሱን በወንጀሉ ተሳታፊ ባላደረገ መልኩ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ጊዜ እና ቦታ ለማስቀመጥ መሞከሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ጊዜውንና ቦታውን

[5] Introduction to criminal investigation, p.80, APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p..88

በተመለከተ ለሚቀርብለት ጥያቄ  ምናልባት እየዋሸ ለመሆኑ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሀሰት ጥቆማ የሚያቀርቡ ጠቋሚዎች ተአማኒ እንዲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ስለሚጠቁሙት ጉዳይ አጋነው እንዲሁም በጣም ዝርዝር የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ እንደሚያውቁ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ እናም ጥቆማቸውን ወይም ምስክርነታቸውን ከቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎችና መረጃዎች ጋር በማነጻጸር የሀሰት ጠቋሚዎች ማለትም ወይ ተሳትፎአቸውን ለመደበቅ ወይም ወንጀልን ለመደበቅ የቀረቡ ምስክሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ አመልካች ነገር ሊሰጥ ይችላል፡፡[6]

ከዚህ በላይ የቀረቡት የጥንቃቄ እርምጃዎችም ተወስደው ጠቋሚዎች ያቀረቡት ጥቆማ ማስረጃዎችን እና ወንጀል አድራጊዎችን እየደበቀ ወይም ንጹህንን ለማጥቃት መሆኑ ላይደረስበት ይችላል፡፡ ስለሆነም ጥቆማ አቅራቢው ያቀረበውን ጥቆማው የሚያስተባብል ሌላ መረጃ እስካልቀረበ ድረስ የሀሰት መረጃ(ጥቆማ) መሆን አለመሆኑ ላይ አለመዘናጋት(ማጣራት) እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ጥቆማውን እንደእውነት ተቀብሎ መሄድ ይገባል፡፡[7]

በጥቆማ አቀባበልና ምዝገባ ላይ ከሚነሱት ጥያቄዎች አንዱ የፍትሀብሄራዊ ጉዳይ ብቻ የሆኑትን ነገሮች እንደወንጀል ጉዳዮች ሆነው በመቅረብ የወንጀል ምርመራ ስራን የሚፈታተኑ መሆናቸው ነው፡፡

በወንጀል የማያስጠይቁ የፍትሀብሄር ጉዳዮች የፖሊስንና የዐቃቤ ሕግን ጊዜ በመሻማት ላይ የሚገኙ ከመሆናቸውም ባሻገር ወረቀትና ሌላም የመንግስት ንብረት አለአግባብ እንዲባክን የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም አንድ ምርመራ ለማድረግ ከመጀመሩ በፊት ጉዳዩ  ፍታብሔር ብቻ አለመሆኑን፣ ወንጀል መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡በአብዛኛው ጠቋሚዎች ወደፖሊስ ዘንድ የሚመጡት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያላቸው እንደሆኑ በወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ ላይ የተሰማሩ የሚገልጹት ነው፡፡ ስለሆነም ሰዎች (ጠቋሚዎች) የፍትሀብሄር ጉዳዮችን ብቻ ይዘው የሚመጡበት ምክንያቶች ይኖራቸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል፣

1/ ጉዳዮ የፍትሐብሔር መሆኑን እያወቁ በፍትሐብሔር ችሎት የፍትሐብሔር ክስ ካቀረቡ በኋላ በፍርድ ቤቶች የስራ ጫና ምክንያት ጉዳዩ ቶሎ እንደማይፈፀምላቸው ስለሚያውቁ ተከሳሹ በፖሊስ ቃሉን እንዲሰጥ ሲጠራ ፈርቶ ወይም ደንግጦ ገንዘባችንን ይከፍለናል የሚል እምነት ሲኖራቸው፣

---

6 introduction to criminal investigation,p. 80

7 APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.88

2/ የፍትሐብሔር ክስ የዳኝነት ወጪ የሚያስከፍል በመሆኑ በወንጀል ክስ ምንም ወጪ የሌለባቸው በመሆኑ፣

3/ ተከሳሽ በወንጀሉ ክስ ጥፋተኛ ከተባለ ይኸኛው ማስረጃ በኋላ ለፍትሐብሔሩ ክስ ይረዳኛል የሚል ግምት ስላላቸው፣

4/ አንዳንድ ጊዜ ገንዘብ ለተከሳሽ ለመስጠታቸው ምንም ማስረጃ ሳይኖራቸው ሲቀር በወንጀል ከሰው ቢያንስ በማጉላላት መበቀል ስለሚፈልጉ፣

5/ በውል ግዴታ የገባው ሰው ከአካባቢው ሲሰወርና አግኝተው ማነጋገር ሳይችሉ ሲቀሩ ወደ ወንጀል አዙሬ በፖሊስ ጣቢያ ብከስ ፖሊስ ይዞ ያቀርበዋል የሚል ግምት ስላላቸው የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም ወንጀል ያልሆኑ የፍትሀብሔራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ጥቆማ ተቀባዩ ለጠቋሚዎች በማሳወቅ ጉዳዩን በዚያው ደረጃ ማስቆም ያስፈልጋል፡፡

ይሁንና በሙስና ወንጀሎች ጉዳይ ግን የፍትሀብሔራዊ የሆኑ ጉዳዮች ብቻ ናቸው ብሎ ለማለት ቀላል ሆኖ አይታይም፡፡ በመሰረቱ የሙስና ወንጀል ከጥቅም ጋር የተያያዘ ስለሆነ እና ሁለት ወገኖችን የመንግስት መስሪያ ቤት(ህዝባዊ ድርጅት) ሰራተኞች እና የግል ተገልጋይ ሰዎች (ነጋዴዎች፣ ካምፓኒዎች፣ ግብር ከፋዮች ወዘተ) የሚያሳትፍ ስለሆነ በአብዛኛው ከውል ጋር ከግዢ ጋር የሚገናኙ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ከውል ጋርም ሆነ ከግብር አከፋፈል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጥቆማዎች ከገንዘብ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው የፍትሀብሄር ጉዳዮች እንደሚሆኑም ይታወቃል፡፡ነገር ግን የፍትሀብሄር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በውል አፈጻጸሙ የተደረጉ ክፍያዎች፣ የቀረቡ እቃዎችና አገልግሎቶች፣ የግብር ግምት ወዘተ የሙስና ወንጀል የተፈጸመባቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ስለሆነም ገና በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩ የፍትሀብሄር ጉዳይ ብቻ ነው የሙስና ወንጀል ባህርይ የለውም ብሎ ለመለየት የሚያስቸግርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ከጠቋሚው ወንጀል ለመሰራቱ ሊያስጠረጥሩ የሚችሉ መረጃዎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ያህል እቃው ወይም አገልግሎቱ በታቀደው ጊዜ ሳይቀርብ ከቀረና አልቀረበም የሚል ጥቆማ ቢኖር ያልቀረበበት ምክንያት ምንድነው? የሚለውን ከጠቋሚው ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ የቀረበው እቃ ወይም አገልግሎት ደረጃውን ያልጠበቀ ነው የሚል ጥቆማ ሲቀርብ ደረጃውን የጠበቀ ላለመሆኑ ማስረጃው ምንድነው? ብሎ መጠየቅ ለምሳሌ ስፔሲፊኬሽኑ ምን ይላል? ከዚህ በተጨማሪ የቀረበለት መስሪያ ቤት ምን አደረገ? እቃውን ተቀብሎታል? አጽድቆታል? ወዘተ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማጣራት ያስፈልጋል፡፡

ይህም ሆኖ ገና ጥቆማው በሚቀርብበት ጊዜ በጉዳዩ ሙስና ስለመፈጸሙ ወይም ፍትሀብሄራዊ ጉዳይ ብቻ መሆኑን ለመለየት ሊያስቸግር ስለሚችል፣ ጉዳዩ የፍትሀብሄራዊ ጉዳይ ብቻ ስለመሆኑ እርግጠኛ ካልተሆነ በስተቀር ጥቆማውን መዝግቦ ለሚመለከተው የምርመራ አካል ማስተላለፍ ይመረጣል፡፡እንደጉዳዩ ከባድነትና አስቸኳይነት አንጻርም ጥቆማው እንደቀረበ ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው የበላይ ሀላፊዎች ስለጥቆማው ማሳወቅ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

### 1.6.1. ጠቋሚዎችን ስለመጠበቅና ከለላ ስለመስጠት

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በጠቋሚዎች ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ ሀቀኛና በቀናነት ጥቆማ ያቀረቡ ደግሞ በወንጀሉ ተሳታፊ ከሆኑ ወገኖች ጥቃት ሊደርስባቸው ስለሚችል ለጠቋሚዎች ከለላና ጥበቃ ማድረግ በተለይ በሙስና ወንጀል ጉዳይ የሚመከርና የህግ ድጋፍም ያለው ነው፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕጉ የጥበቃና የከለላ ተጠቃሚ ጠቋሚዎች እነማን ናቸው ለሚለው አዋጁ በአንቀጽ 2(7) በሰጠው ትርጉም መሰረት ተፈጽሟል ወይም ሊፈጸም ነው ብሎ ያመነውን የሙስና ወንጀል የሚመለከት መረጃ አግባብ ላለው አካል ወይም ለሌላ የፍትሀ አካላት፣ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ ለመንግስት የልማት ድርጅት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት የበላይ ሀላፊ ወይም በህግ ወይም በመመሪያ የሙስና ወንጀል ጥቆማን እንዲቀበል ሀላፊነት ለተሰጠው ሌላ አካል የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ሲሆን፣ ለእነዚህ ለተጠቀሱት አካላት ጥቆማ ባያቀርብም የሙስና ወንጀል የተፈጸመበትን ኦዲት የሚያደርግ ወይም በኦዲት ተግባሩ ሙስና መፈጸሙን ያጋለጠ ኦዲተርን እና ጥቆማን የሚያጣራ ወይም የሚመረምር ሰውን ያካትታል በማለት ይደነግጋል፡፡

ጠቋሚን ከጥቃት ለመከላከል ዋናው የመጀመሪያው ጉዳይ ጠቋሚዎቹ ማንነታቸው እንዲገለጽ እስካልፈለጉ ድረስ የጠቋሚውን ማንነት እና የጥቆማውን ይዘት በምስጢር መያዝ ነው፡፡እርግጥ የጠቋሚዎች ማንነት በምስጢር መያዝ አንዱ የከለላ መንገድ ቢሆንም፣ ጠቋሚዎች ይህንን ምሽግ በመጠቀም መርማሪውን የምርመራ አቅጣጫውን እንዲስት የማድረግም አደጋ አለው፡፡ አንዳንዱ ጠቋሚ ጥቆማ የሚያቀርብባቸው አካላት እርሱ ወይም የእርሱ ቡድን አባላት በፈጸሙት ወንጀል ወይም ጥፋት ሊያጋልጡዋቸውና እርምጃ እንዲወስድ የሚንቀሳቀሱትን አካላት ለማስቆምና ጥፋቱን ለማዳፈን እና የምርመራ ተቋሙን የፍላጎቱ መጠቀሚያ ለማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ከዚህ በላይ እንደቀረበው ጥቆማ ተቀባዮች ወይም መርማሪዎች ከዚህ

በላይ የጠቋሚን አላማና ግብ ምን ሊሆን እንደሚችል ከመተንተን ስራ አንጻር ሊወስዱ የሚገባውን ጥንቃቄ መፈጸም የሚኖርባቸው መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

የጠቋሚውን ማንነት በምስጢር መያዝ የማይቻል ከሆነ ቀጣዩ ስራ የሚሆነው በጠቋሚው ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት ለመከላከል ምን አይነት ስጋት እንዳለ የስጋት ትንተና በመስራት ምን አይነት ጥበቃ ሊያገኝ እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጦ መንቀሳቀስ ነው፡፡ የስጋት ትንተናውን ለማግኘት በዋነኛነት መረጃው በመጀመሪያ ከራሱ ከጥቆማ ሰጪው የሚገኝ ሲሆን፣ እንደሁኔታው ሊወሰድ የሚገባውን የጥበቃና የከለላ እርምጃ ለመወሰን የስጋቱን ትክክለኝነት፣ የመፈጸም እድሉን በአግባቡ መተንተን ያስፈልጋል፡፡

ሊወሰዱ ከሚችሉ የከለላ እርምጃዎች አንዱ በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕግ እንደተሻሻለው በአንቀጽ 52 ጠቋሚው በሚሰራበት መስሪያ ቤት የአስተዳደራዊ እርምጃ ከተወሰደበት ይህ እርምጃ የቂም በቀል እርምጃ መሆኑን ካመነበት የአስተዳደራዊ ውሳኔ ተግባራዊ እንዳይደረግ ባለው የማገድ ስልጣን አግባብ ያለው አካል (የሙስና ወንጀልን የመመርመር ወይም የመክሰስ ስልጣን ያለው አካል) አስተዳደራዊ እርምጃውን ማገድ ነው፡፡ ይህ አግባብ ባለው አካል የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሊሻር የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ለፍርድ ቤት ቀርቦ በፍርድ ቤት ሲወሰን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስለጠቋሚዎችና ምስክሮች ጥበቃና ከለላ በሚደነግገው አዋጅ ቁ. 699/2003 የተዘረዘሩት የጥበቃና ከለላ እርምጃዎች (የመኖሪያ ስፍራን መቀየር፣ ማንነትን መቀየር፣ የአይነ ቁራኛ ጥበቃ ማድረግ፣ ማንነትንና ባለንብረትነትን መደበቅ፣ ለራስ መጠበቂያ የነፍስ ወከፍ መሳሪያ መስጠት፣ መረጃ በሰጠበት ወንጀል ጉዳይ ያለመከሰስ፣ ተከሳሽ ወደ ጠቋሚው አካባቢ እንዳይደርስ ማድረግ፣ ምስክርነትን በዝግ ችሎት ማድረግ፣ የትራንስፖርትና የውሎ አበል መሸፈን፣ ለደረሰ ጉዳት የህክምና ወጪ መሸፈን፣ በጉዳት ምክንያት የመስራት ችሎታ በማጣት የሚደርስ ጉዳትን ለመተካት ወጪን መሸፈን፣ የትምህርትና የስራ እድል እንዲያገኝ መርዳትን) እንደስጋቱ አይነትና ደረጃ ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

ሌላው ጠቋሚውን ከመጠበቅ አንጻር የሚመከረው አዎንታዊ እርምጃ ምስጢራዊ ሆነው ሊቆዩ የሚገባቸውን መረጃዎች መጠበቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ለጠቋሚው ስለምርመራው አካሄድ በየደረጃው መረጃ መስጠት ነው፡፡ ጠቋሚዎች በአንድ በኩል በደል የተፈጸመባቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ ፍትህ እንዲረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህ ጠቋሚዎች ለህግ ማስፈጸሙ መረጃ በመስጠትና በማቀበል፣ ምስክር በመሆን የወንጀል ፍትህ ስርአቱ ውጤታማ እንዲሆን እንደሚረዱ ይታወቃል፡፡  ስለምርመራው ሂደት በየደረጃው መረጃ አለመስጠት ምናልባትም

ከተጠቆመው አካል ጋር ምስጢራዊ ግንኙነት ተፈጥሮ ልጠቃ እችላለሁ የሚል ስጋትም ሊፈጥርባቸው ስለሆነም እራሳቸውን ለማዳን በማሰብ በቀጣይነት የምርመራ ስራውን የሚያደናቅፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም በምርመራ ስለተያዘው ጉዳይ በየጊዜው ምስጢራዊ ያልሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ምርመራው የሚገኝበትን ሁኔታ ማሳወቅ ሞራላቸውን የሚጠብቅና በሂደቱ ተሳትፎአቸውን እንዲያጠናክሩ ማስረጃዎችን ፈልገው እንዲያመጡ የማድረግ አዎንታዊ ጠቀሜታ አለው፡፡[8]

### 1.6.2. ምርመራ እንዲደረግ ስለመወሰን

በማንኛውም መልኩ ጥቆማ ከቀረበ በኋላ ቀጣዩ እርምጃ በጥቆማው ላይ ምርመራ ይጀመር? ወይስ ምን ይሁን? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው፡፡

በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 22 ፖሊስ የተሰራውን ወንጀል በሚያውቅበት ወይም በጥርጣሬ በሚረዳበት ጊዜ ሁሉ ምርመራ ያደርጋል ይላል፡፡ በቁ. 23 ደግሞ የቀረበው የክስ አቤቱታ ወይም መረጃ የሚያጠራጥር ነው ብሎ ቢያስብም ፖሊስ የምርመራ ተግባሩን ለመፈጸም ይገደዳል ይላል፡፡ ስለሆነም በማንኛውም ጥቆማ ላይ ምርመራ ማድረግ ግዴታ ነው፡፡ ምክንያታዊም ይመስላል፡፡ ካልተመረመረ ወንጀል መፈጸም አለመፈጸሙ ሊታወቅ አይችልምና!

ከዚህ አንጻር ጠቋሚው የሚታወቅ ከሆነ በጥቆማው ላይ የመፈረም ግዴታ ያለበት ከመሆኑ አንጻር ጠቋሚው በሰጠው ጥቆማ በጽሁፍ ተደርጎ ከፈረመበት ጠቋሚው ነገ ሊያስጠይቀው የሚችለውን ነገር አይፈርምም ከሚል መነሻ ምርመራውን መጀመር ተገቢና ትክክል ይመስላል፡ ጠቋሚው ያልታወቀ ከሆነስ?

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁ. 12 ካልታወቀ ጠቋሚ የሚቀርብ ጥቆማ ከፍ ያለ የህግ መጣስን የሚገልጽ ሆኖ ወንጀሉ ለመሰራቱ በአካባቢ ሁኔታ የተደገፈና የሚታመን መስሎ በተገኘ ጊዜ እውነትን ለማግኘት ያለበለዚያም የቀረበውን ክስ ለማረጋገጥ ስልጣን ባለው ፖሊስ ይመረመራል ይላል፡፡

---

[8]Keeping witnesses informed of the criminal prosecution process will instillconfidence in them and allay fear and apprehension.(best practices in investigating and prosecuting corruption,p. 88

## 1.7. በሙስና ወንጀል ከሚያስከስሱት ወንጀሎች ከባድ የህግ ጥሰት ሊባሉ የማይችሉት የትኞቹ ናቸው?

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. ጥቆማው መሟላት አለመሟላቱን የሚያረጋግጠው በምንድነው?
2. ክስና አቤቱታው ተሟልቷል የሚባለው ምን አግኝቶ ነው?
3. ጥቆማ ላይ ጠቋሚው ታወቀ አልታወቀ ምን ልዩነት ሊፈጥር ይችላል?
4. በምርመራ ሂደት ላይ የሀብት ብክነት እንዴት ማስቀረት ይቻላል?
5. ጥቆማውን በአካባቢ ማስረጃ ለማረጋገጥ መረጃዎችን የማቅረብ ስራ የማን ስራ ነው?
6. ፖሊስ በጥቆማው መሰረት መረጃ የማሰባሰብ ስራ ይሰራል ማለት ነው?

ማንነቱ ካልታወቀ ጠቋሚ ማለትም ስለጥቆማው እውነተኛነት በመፈረም ካላረጋገጠ ጠቋሚ ጥቆማ በመነሳት በማንኛውም ሁኔታ ምርመራ ይጀመር ቢባል የፖሊስን ሀይል በመጠቀም ንጹሀን ሰዎች ላይ በሀሰት በሚመሰረት ክስ ሰብአዊ መብታቸው እንዲጣስ እና ጉዳት እንዲደርስባቸው የማድረስ አደጋ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ውሱን የሆነውን የፖሊስ ሀብት (የሰው ሀይልም ሆነ የሎጂስቲክ) አላግባብ የሚባክንበት እና ከእውነተኛ የወንጀል ጉዳዮች የማዘናጋትና መንገድ የማሳት አደጋ አለው፡፡ ስለሆነም ጥቆማውን በአካባቢ ማስረጃዎች መደገፉ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን በፌዴራል ፖሊስ በታህሳስ 2009 ወጥቶ ስራ ላይ የዋለው የሙስና ወንጀሎች… የክስና ጥቆማ አቀባበል ስርአት አጭር የስራ ማንዋል አንቀጽ 4(1) ክሱ ማንነቱ ባልታወቀ ግለሰብ የቀረበ ከሆነ….ጥቆማ ተቀባዩ በተቻለ ፍጥነት ክስና አቤቱታው የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ያልተሟላ ከሆነ የሚሟላበትን አማራጭ ሁሉ ተጠቅሞ አሟልቶ በወንጀል እለት ሁኔታ መዝገብ መዝግቦ ለምርመራ ዲቪዥን ይልካል፡፡ የሀሰት ጥቆማ ከሆነ መባከኑ መድከሙ አይቀርም፡፡በስነስርአት ህጉ ቁ. 12 እንደተደነገገው ባልታወቀ ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወደምርመራ የሚገባው አንዱ መስፈርት ከፍ ያለ የህግ ጥሰት ከሆነ ነው የሚል ነው፡፡

የሙስና ወንጀል ምርመራ በጥቆማ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የጸረ ሙስና ወንጀል ምርመራ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት የጥቆማ ተቀባዮች በበርካታ ጥቆማዎች እንደሚጥለቀለቁ ነው፡፡[9] ስለሆነም የሚቀርቡ ጥቆማዎች ብዙ ሆነው የምርመራ አቅም ውሱን በመሆኑ ጠቋሚው ቢታወቅም ባይታወቅም በሁሉም ጥቆማዎች ላይ ምርመራ ለማድረግ የማይቻልበት አጣብቂኝ

[9] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.11

ውስጥ መገባቱ አይቀርም፡፡ከዚህ አንጻር ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊመረመር የሚገባው የትኛው ነው? የሚል ጥያቄን መመለስ ግድ ነው፡፡[10]

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ሲቀርብ የመጀመሪያው ጥያቄና ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው ከተጠናቀሩት ጥቆማዎችና መረጃዎች ተነስቶ በምን አግባብ ቢታዩ ይሻላል?የሚለው ነው፡፡ ከጥፋቱ አነስተኛነት ማለትም ካደረሰው ጉዳት ወይም የተገኘ የማይገባ ጥቅም አነስተኛነት አንጻር በወንጀል ክስ መስርቶ ከመከታተል በአስተዳደራዊ መልኩ ተመጣጣኝ እርምጃ ሊወሰድበት የሚችል ከሆነ በአስተዳደራዊ መልኩ እንዲያልቅ ማድረግ ይመረጣል፡፡[11]

ጉዳዩ በአስተዳደራዊ መልኩ ብቻ ቢታይ ተመጣጣኝ እርምጃ አይሆንም፣ ጥፋት አድራጊዎችን አያስተምርም ወንጀል እንዲስፋፋ ስለሚያደርግ የወንጀል ምርመራ ሊደረግበት ይገባል በሚል ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላም ቢሆን ካለው ውሱን ሀብት (የሰው ሀይልና ሎጂስቲክስ) አንጻር ሁሉንም በተመሳሳይ ጊዜ መመርመር ካልተቻለ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን መምረጥ የግድ ነው፡፡

ወንጀል ሲፈጸም እጅ ከፍንጅ የተያዘው ጉዳይ(ለምሳሌ ጉቦ ሲቀበል) ከመጣ በተለምዶ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ወንጀሉ ሲፈጸም እና ተጠርጣሪው ሲያዝ ለምርመራው የሚያስፈልጉ ዋነኛ ማስረጃዎች ሁሉ ስለሚሰባሰቡ ወንጀሉም ሆነ ተብሎ የሚሰራ በመሆኑ፣ ከዚህ በኋላ ጊዜ የሚወስድ ምርመራ ስለማይኖረው በቀጥታ ምርመራውን ማጠናቀቅ ስለሚቻል ሌሎች የተጀመሩ ምርመራዎችን ማቋረጥ ሳያስፈልግ ሊጠናቀቅ ስለሚችል ነው፡፡

ወንጀሉ እጅ ከፍንጅ ባልሆነ ጊዜ ግን ቅድሚያ የሚሰጠውን በምን መስፈርት መለየት ይቻላል? በግልጽ ወይም በዝምታ ያልተሻረው የስነምግባርና ጸረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 433/1997 አንቀጽ 2(9) ያስቀመጠው አመላካች ነገር አለ፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 2(9) ከባድ የሙስና ወንጀል የሚባሉት (ሀ) ከፍተኛ ስትራተጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ

---

[10]በመሰረቱ ወንጀልን በተለይም የሙስና ወንጀልን በህግ ማስከበር ብቻ መቋቋም አይቻልም፡፡ ከዚህ በላይ በቀረበው ክፍል እንደተመለከትነው የመንግስት በነዋሪው ህይወት ውስጥ ያለው ጣልቃ ገብነት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሙስና ወንጀል የመፈጸም እድሉ እየጨመረ ስለሚሄድ የህግ ማስከበር ስራውን አስቸጋሪ እና ከባድ ያደርገዋል፡፡ስለሆነም የመጀመሪያው ምርጫ የመንግስትን ሚና መቀነስ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ግልጽነት ያለበት አሰራን ትራንስፓረንት አሰራር በመዘርጋት ሙስና የሚፈጸምበትን እድል መቀነስ ነው፡፡ በሙስና ወንጀል ከሚገኙ ተሞክሮዎች በመነሳት በመንግስት መስሪያ ቤቶች የአሰራር ግልጽነትን መዘርጋት ወንጀሉ እንዳይፈጸም መከላከል ብቻ ሳይሆን፣ ወንጀሉ ሲፈጸም ማስረጃዎችን በቀላሉ ለማስገኘት የሚችልም ነው፡፡

[11] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.13

የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም (ለ) የመንግስት ባለስልጣናትን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም (ሐ) በአገር ሉአላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ናቸው ይላል፡፡

OECD ባዘጋጀው Corruption Investigation and Prosecution Training Manual ቅድሚያ የሚሰጠውን ለመምረጥ የሚከተሉት እንደ መስፈርት እንዲወሰዱ ይመክራል፡፡

1. የሙስና ወንጀሉ ከባድነት- ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ወይም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብን ካካተተ፤ የወንጀሉ ባህሪ አሳሳቢነት
2. የሙስና ወንጀሉ መንሰራፋት ለምሳሌ በጣም የተለመዱና በሰፊው የሚናፈሱ ወንጀሎች እንደ በመንግሥት ግዥ፣ ታክስ፣ ጉምሩክ ፣ ትራፊክ እና ሌሎች የስጋት ዘርፎች፤
3. በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ክስ ለማቅረብ እንደሚቻል ለመፈተን/ለማሳየት (ማለትም ትኩረት ያላገኙ ነገር ግን ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ጉዳዮችን በተመለከተ)-በሕግ የሰውነት መብት በተሰጣቸው ድርጅቶች ላይ ወይም ጉቦ በተቀበለ የውጭ መንግሥት ባለሥልጣን ላይ ክስ በማቅረብ የሕዝብን አመለካከት መቀየር አስፈላጊ ሲሆን፤
4. የምርመራ አቅምን ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንጻር በማነጻጸር- አንድን ጉዳይ ለመመርመርና ለመክሰስ ከመወሰን በፊት ጥቅምና ጉዳቱን መገምገም ያስፈልጋል፡፡ ትንንሽ ጉዳዮችን መመርመርና መክሰስ ብዙ ሀብት ሊፈጅ ነገር ግን ጉልህ/ጠቃሚ ተፅዕኖ ላይፈጥር ይችላል፡፡ ከባድ የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ ከፍያለ ወጪ ሊጠይቅና ብዙ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል፤ ሆኖም በሙስና የተዘረፈ ከፍተኛ ገንዘብ ሊያስመልስና በመንግሥት ላይ ያለን እምነት ሊያሻሽል ይችላል፡፡[12]

የፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቢሮ የሙስና ወንጀሎች ምርመራ ዳይሬክቶሬት የክስና ጥቆማ አቀባበል ስርአት አጭር የስራ ማንዋል በአንቀጽ 6(4)…. አንድ ጉዳይ በአስቸኳይ እንዲመረመር የሚወሰነው ከሚከተሉት አንዱ ሲሟላ ነው በማለት የሚከተሉትን ይዘረዝራል፡-

1. ከፍተኛ መጠን ያለው ግዢ ወይም ሽያጭ የመሳሰሉ አላግባብ የተፈጸመ ያለ ሲሆን ወይም
2. በተፈጸመው ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ጉዳይ ለነገ ይቆይ የማይባል ሲሆን ወይም
3. ወዲያውኑ ምርመራ ካልተጀመረ በስተቀር ማስረጃዎች ሊጠፉ የሚችሉ ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ሲኖር ወይም

[12]OECD — Corruption Investigation and Prosecution Training Manual p. 19

4. በከፍተኛ የሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ተፈላጊ ማስረጃዎችን ያጠፋል ተብሎ ሲገመት፣ ወይም ከአገር ለቆ የሚሄድ መሆኑ ሲገመት፣
5. የሙስና ወንጀል ሊፈጸም ወይም እየተፈጸመ መሆኑ መረጃ ሲደርስና ተጠርጣሪውን እጅ ከፍንጅ መያዝ ወይም ድርጊቱን ማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣
6. በሌላ መርማሪ አካል የተጀመረ ምርመራ ወደዳይሬክቶሬቱ ሲመጣና ተጠርጣሪው ተይዞ በቁጥጥር ስር ያለ ከሆነ፣
7. በእለቱ ተሰርተው ሊጠናቀቁ የሚችሉና አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የሚታመንባቸው ጉዳዮች፣
8. ወንጀሉ እጅ ከፍንጅ የተፈጸመ እንደሆነ ወይም ሊፈጸም በዝግጅት ላይ ያለ እንደሆነ፣
9. ምርመራው በአፋጣኝ እንዲጀመር ከሚመለከተው የበላይ አካል በቃል ወይም በጽሁፍ ትእዛዝ በተሰጠበት ጊዜ፣
10. በመንግስት እና በህዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ተብሎ በተገመተበት ወቅት፣
11. ወንጀሉ የተፈጸመው ከሀገር ድንበር ውጭ ሊወጣ ዝግጁ በሆነበት ወይም ሊወጣ ሲል የተያዘ እንደሆነ፣

ይሁንና በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ጥቆማ ሲመረጥ፣ለጊዜው ያልተመረጡትና ለጊዜው ይቆዩ የሚባሉት በመቆየታቸው ማስረጃ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ቢያንስ በምርመራ አካሉ ቁጥጥር ስር የገቡ መረጃዎችና ማስረጃዎች በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እዚህ ላይ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ የቅድሚያ መስጠት ጉዳይ በመጀመሪያ ወደምርመራ ለመግባት ሲወሰን ብቻ አይደለም፡፡ምርመራ እየተደረገም ቢሆን ከፍተኛ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ሲመጣና የምርመራ አቅም ውሱን ሲሆን የተጀመረው ምርመራ ለጊዜው አቁሞ ወደአዲሱ ጉዳይ ምርመራ መጀመር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ቅድሚያ የሚሰጥበት መስፈርት በዚህ ጊዜም ቢሆን አግባብነት እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም ቅድሚያ ለሚሰጠው ጉዳይ ቅድሚያ ይሰጠው ብሎ የሚወስነው አካል ይህንን ውሳኔውን ከተጽእኖ ውጭ መስጠት እንዲችል የምርመራ ተቋሙ ተቋማዊ ነጻነት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ይሰመርበታል፡፡[13] አለበለዚያ ተቋሙ በጠቋሚዎች ፍላጎት የሚፈለገውን

[13] United Nations Convention Against Corruption, art.6 Each State Party shall grant the body or bodies referred to in paragraph 1 of this article the necessary independence, in accordance with the fundamental principles of its legal system, to enable the body or bodies to carry out its or their functions effectively and

ማጥቂያ የሚፈለገውን ደግሞ ከወንጀል ምርመራ ማሸሻ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የሙስና ወንጀል ምርመራ ከአስፈጻሚው አካል አንጻራዊ ነጻነት ባለው አካል የሚከናወን ካልሆነ እንዲሁም በጠቋሚዎች ብቻ እየተመራ የሚሰራ ከሆነ የተደራጀ የሙስና ፈጻሚ አካል ሙስናን የሚዋጉትን ወገኖች ለማጥቂያ የሚጠቀሙበት ዱላ ከመሆን አያመልጥም፡፡

**ማጠቃለያ**

በዚህ ክፍል በጥቆማ ላይ የተመሰረተ የሙስና ወንጀል ምርመራ ስላሉት ውስንነቶች ቀርቧል፡፡ ከዚህ በመቀጠልም የሙስና ወንጀል ጥቆማ የማቅረብ መብት ማንኛውም ሰው ያለው ስለመሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ግን ግዴታ ያለባቸውና ስለሙስና ወንጀል መፈጸም አውቀው ጥቆማ አለማቅረብ በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑ ተካቷል፡፡ ማንነታቸው በሚታወቅና በማይታወቅ ሰዎች ስለሚቀርቡ ጥቆማዎች፣ እንደዚህ አይነት ጥቆማዎች ሲቀርቡ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ቀጣይ እርምጃዎች በወ/መ/ስ/ስ/ሕጉ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በማንሳት በአተገባበር ሊነሱ የሚችሉ ችግሮች ቀርበዋል፡፡ ጥቆማ ሲቀርብ ጥቆማ ተቀባዮች ከጠቋሚዎች በተቻለ መጠን በርካታ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ስለሚችሉበት ሁኔታ ማለትም ወርቃማ የምርመራ ጥያቄዎች(golden investigative questions) ምንን እንደሚያካትቱ በመዘርዘር መረጃና ማስረጃ ስለሚሰበስቡበት ሁኔታ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ የሙስና ወንጀሎችን ከፍትሀብሄራዊ ጉዳዮች ለመለየት እንደሚያስቸግር ከዚህ አንጻር በጥቆማ አቀባበል ጊዜ ምን አይነት ዝግጅቶችና ጥንቃቄዎች ሊደረጉ እንደሚገባ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ በሙስና ወንጀል ጠቋሚ ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች የራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ሊኖራቸው ስለሚችል የምርመራ ስራውን በሚፈልጉት መልኩ የእነሱ ፍላጎት ማስፈጸሚያ እንዳያደርጉት ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ተካቷል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ጥቆማ አቅራቢዎች ጥቆማ በማቅረባቸው ለቂምበቀል እርምጃ ሊጋለጡ ስለሚችሉ ሊወሰዱ የሚገባቸው የከለላ እና የጥበቃ እርምጃዎች ተካቷል፡፡ በመጨረሻም ከቀረቡት ጥቆማዎች መካከል ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ሊመረመሩ የሚገባቸውን ጥቆማዎች ለመምረጥ የሚያስችሉ የተለያዩ አማራጭ መመዘኛ መስፈርቶች በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

---

free from any undue influence. The necessary material resources and specialized staff, as well as the training that such staff may require to carry out their functions, should be provided.

## የምእራፉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

### አስረጅ ናሙና  አንድ

አንድ ሰዉ ጥቆማ ተቀባይ ዘንድ ቀርቦ የሙስና ወንጀል የተፈጸመ መሆኑን ሪፖርት ካደረገና መርማሪዉም ይህን ሪፖርት ከመዘገበ፣ ጠቋሚዉንም በዝርዝር ስለወንጀሉና ስለወንጀለኛዉ ጠይቆ ከመዘገበ በኋላ እንዲፈርም ሲጠይቀዉ አልፈርምም፣ ስሜም በምስጢር ይያዝልኝ ለበቀል ያጋልጠኛል በማለት ለጥቆማ ተቀባዩ ነግሮ ወጥቶ ሄደ፡፡

1. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና አንድ  መሰረት ይሄ ጥቆማ ቀረበ ነው ወይስ አልቀረበም ነው የሚባለው? ጥቆማ ቀረበ ተብሎ የሚወሰድ ከሆነ በሚታወቅ ጠቋሚ የቀረበ ነው ወይስ በማይታወቅ ጠቋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ነው የሚወሰደው ተጨማሪ ማብራሪያዎችን አቅርቡ?
2. የሙስና ወንጀል ምርመራ  ውሱንነቶች ዘርዝሩ?
3. ጥቆማዎች ሲቀርቡ ሊወሰዱ የሚገባቸው ቀጣይ እርምጃዎች እና በአተገባበር ሊነሱ የሚችሉ ችግሮችን አብራሩ?
4. ከቀረቡት ጥቆማዎች መካከል ቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ሊመረመሩ የሚገባቸውን ጥቆማዎች ለመምረጥ ከሚያስችሉ የመመዘኛ መስፈርቶች መካከል የተወሰኑትን ግለፁ?

# ክፍል ሁለት

## 2. የሙስና ወንጀል ምርመራ

### 2.1. የምዕራፉ አጭር መግለጫ

በዚህ ምእራፍ ማንኛውም የወንጀል ምርመራ ስራዎች ሊመሩባቸው የሚገቡ አጠቃላይ መርሆዎች፣ በምርመራ ሂደት የሚከሰቱ ተደጋጋሚ የምርመራ ስህተቶች፣ ምርመራ በእቅድ ሊመራ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የምርመራ እቅድ ሲዘጋጅ ሊያካትታቸው ስለሚገቡ ፍሬነገሮች፣ በሙስና ወንጀል ሊሰባሰቡ የሚገባቸው ማስረጃዎች አይነት፣ ማስረጃዎቹ የት እንደሚገኙ እና እንዴት ማሰባሰብ እንደሚቻል፣ ምስክሮችን እንዴት መለየት እና የምስክሮች ቃል አቀባበል፣ ለወንጀሉ ማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን ለመያዝ ብርበራና ፍተሻ ስለሚደረግበት ሁኔታ፣ በሙስና ወንጀል ተገኝተዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ንብረቶችን ስለማሳገድ፣ ስለማስተዳደር እንዲሁም ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ የተጠርጣሪ የዋስትና መብት ስለሚፈቀድበትና ስለሚከለልበት ሁኔታ፣ የተጠርጣሪን ቃል አቀባበል ስልቶችና ዘዴዎች እንዲሁም በመጨረሻ የምርመራ ሪፖርት ስለማዘጋጀትና ሪፖርቱ ስለሚይዛቸው ፍሬነገሮች በዝርዝር የሚቀርብበት ነው።

### 2.2. የምእራፉ አጠቃላይ ዓላማወች

የሥልጠናው ተሳታፊዎች የዚህን ምእራፍ ስልጠና ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- ❖ ለዓቃቢ ህግ እና ለፖሊስ ስለሚሚቀርቡ የምርመራ አተገባበሮችን ያውቃሉ።

#### 2.2.1. የምእራፉ ዝርዝር ኣላማዎች

ይህ ምዕራፍ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።እነርሱም፡-

- የወንጀል ምርመራ ስራዎች ሊመሩባቸው ስለሚገባቸው ህግጋቶች ይጠቅሳሉ።
- በምርመራ ሂደት ስለሚፈጸሙ የምርመራ ስህተቶች ተጨባጭ ዕውነታዎችን ይመረምራሉ።
- የምርመራ እቅድ ያዘጋጀሉ፣
- ማስረጃ በማሰባሰብ ያጠናቅራሉ፣
- ምስክሮችን በመለየት ቃል ይቀበላሉ፣
- ብርበራና ፍተሻ ሲደረግ ሊኖር ስለሚገባው ጥንቃቄና ድንጋጌዎች ይተገብራሉ

- በሙስና ወንጀል ተገኙ ተብለው ስለሚገመቱ ሀብቶችና ንብረቶች የሚታገዱበትና የሚተዳደሩበትን ደንብ ሥራ ላይ ያውላሉ
- የተጠርጣሪን ቃል አቀባበል ሥርዓት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

## 2.3. የምእራፉ ይዘቶች

በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ይዘቶች ያካትታል፡፡

- ➢ የወንጀል ምርመራ ምንነት
- ➢ የወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው አጠቃላይ መርሆዎች፣
- ➢ የምርመራ እቅድ ማዘጋጀት
- ➢ ማስረጃ ማሰባሰብ ማጠናቀርና መተንተን፣
- ➢ ምስክሮችን ስለመለየት የምስክሮችን ቃል ስለመቀበል፣
- ➢ ብርበራና ፍተሻ
- ➢ ንብረት ማሳገድ፣ ማስከበርና ማስተዳደር
- ➢ ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ ዋስትና እና ጊዜ ቀጠሮ እና የተጠርጣሪን ቃል ስለመቀበል
- ➢ የምርመራ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለውሳኔ ለአቃቤ ህግ ማቅረብ

## 2.4. የወንጀል ምርመራ ምንነት

የኢትዮጵያ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ መመሪያ የወንጀል ምርመራ አንድን ጉዳይ በተለያየ አቀራረብና ዘዴ በማጥናት ምን ዓይነት ወንጀል እንደተፈጸመ፣ ማን እንደፈጸመው፣ ለምን እንደተፈጸመ፣ ተጠርጣሪው ወንጀሉን መቼና እንዴት እንደፈጸመው በማያጠራጥር ሁኔታ የሚተነትንበት እና የሚያጣራበት ሂደት ነው ይለዋል፡፡[14]

የወንጀል ምርመራ ማለት ተፈጸመ ተብሎ መረጃ ወይም ጥቆማ በቀረበበት የወንጀል ጉዳይ ወንጀሉ መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙ ለማረጋገጥ እንዲሁም (ወንጀሉ ስለመፈጸሙ የቀረበው መረጃ ወይም ጥቆማ የሚያመለክትና በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ)፣ ወንጀሉን ፈጽሞአል ተብሎ የሚገመተውን ተጠርጣሪ ለመለየት፣ ማስረጃ ማፈላለግን፣ ማግኘትን፣ መተንተንን፣ ማደራጀትን እና በወንጀሉ ተጠርጣሪ ነው የተባለውን በመያዝ ለፍርድ ቤት እንዲቀርብ ማድረግን፣ የምርመራ ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ተጠርጣሪውን በሚመለከት ፍርድ ቤት በሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት

[14] የኢትዮጵያ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ መመሪያ፣ 2011 ዓ.ም ፣ ገጽ 8

መፈጸምን እና ምርመራው ሲጠናቀቅ ስልጣን ላለው አካል የምርመራ መዝገቡን በሚፈለገው ደረጃ አዘጋጅቶና አሟልቶ ማስረከብን  የሚያካትት ነው፡፡

ምርመራ አስቀድሞ በተፈፀመ የወንጀል ጉዳይ ላይ ወይም አፈፃፀሙ ተጀምሮ ባልተጠናቀቀ(በሙከራ ላይ ባለ የወንጀል ድርጊት) ወይም ገና ወደፊት ሊፈፀም በዕቅድና በዝግጅት ላይ በሚገኝ ተግባር ላይ ሊደረግ ይችላል፡፡

ማናችንም ብንሆን በተፈጥሮአችን መርማሪዎች ነን፡፡ ሰዎች ሁልጊዜ በስሜት ህዋሳቶቻችን (በማየት፣ በመስማት፣ በመንካት፣ በመቅመስ እና በማሽተት) አማካይነት በየእለቱ የምናገኛቸውን መረጃዎች እንተነትናለን፣ እናም እንዲህ ማለት ነው ብለን ተርጉመን ወደ ድምዳሜ እንደርሳለን፡ ፡ አንዳንድ ሰዎች እያንዳንዷን መረጃ ከመቀበላቸው በፊት ከተለያየ አቅጣጫ በመመዘን እና በመመርመር ወደድምዳሜ ሲደርሱ፣አንዳንዶች ደግሞ ሌላ ተቃራኒ መረጃ መጥቶ ሀሳባቸውን እስኪያስቀይራቸው ድረስ የመጣውን መረጃ ሳይመረምሩና ሳይተነትኑ (at face value) የሚቀበሉ አሉ፡፡[15] እነዚህ አማራጭ የመረጃ አቀባበልና አወሳሰድ አካሄዶች ለተራው ሰው እንደእምነታቸው መኖር፣ በዚህ ወይም በዚያ መልኩ መወሰን የራሳቸው ጉዳይ በመሆኑ የፈለጉትን አካሄድ መምረጥ ይችላሉ፡፡

የፖሊስ የምርመራ ስራ ግን ከተራው ሰዎች በእለት እለት ከምናደርገው የምርመራ፣ የመተንተንና ድምዳሜ የመድረስ ስራ የተለየ ነው፡፡ የፖሊስ የምርመራ ስራ የራሱን እምነት የማረጋገጥ እና ለራሱ ህይወት የሚሻለኝ ይሄ ነው ብሎ የሚወስንበት ሳይሆን፣ የህዝብን አደራ ተቀብሎ በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰራ በውሳኔው በሰዎች ህይወትና መብት ላይ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ተጽእኖ ለማድረስ የሚያስችል ስልጣን (ጉልበት) ያለው በመሆኑ እያንዳንዱን መረጃ እንዳለ ከመቀበል ይልቅ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመተንተን የመፈተን ስራዎችን መስራት ነው፡፡ ስለሆነም የወንጀል ምርመራ ስራ ሳይንሳዊ የምርመራ መርሆዎችን ተከትሎ የሚሰራ ነው፡፡

## 2.5. የወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው አጠቃላይ መርሆዎች

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

1. የወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው የተወሰኑ መርሆዎችን ዘርዝሩ?

[15] introduction to criminal investigaton- processes- practices-and- thinking , p.2

2. በወንጀል ምርመራ ሂደት የምርመራ ስራው መስመሩን እንዲስት ሊፈጸሙ የሚችሉ መሰረታዊ ስህተቶች ምንድናቸው?
3. በሙስና ወንጀል ምርመራ በማስረጃ ልናረጋግጠው የሚያስፈልገን የወንጀሉ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ምንድናቸው?
4. የሙስና ወንጀል ማስረጃዎች ሊገኙ የሚችሉት የት ነው?
5. መረጃዎችና ማስረጃዎችን እንዴት ማግኘት ይቻላል?

የወንጀል ምርመራ ሂደት የሕግ የበላይነት፣ ለሕዝብ ደህንነትና ሰላም ቅድሚያ የመስጠት፣ ለጉዳዮችና ለሁኔታዎች እንዲሁም ለጥቆማዎች ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት፣ የግልጽነት፣ የተጠያቂነት፣ እና በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሚዛናዊ(ፍትሀዊ) ውሣኔ የመስጠት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል፡፡በወንጀል ምርመራ ሂደት ከማንኛውም መርማሪ ህሊና ሁልጊዜ ሊጠፋ የማይገባው መሰረታዊ መርሆ ተጠርጣሪዎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ እስካልተፈረደባቸው ድረስ እንደንጹህ የሚቆጠሩ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ወንጀል የሰራን እንዲጠየቅ ማድረግ የማህበረሰቡን ደህንነት ሰላምና የሰዎችን መብት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ቢሆንም አጠፋ ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው ደግሞ አላግባብ መብቶቹ መጣስ የለባቸውም፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡን ከወንጀል ተግባር የመጠበቅ ስራ በተቻለ መጠን የተጠርጣሪዎችን መብት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በቀነሰ መልኩ ማድረግ የግድ አስፈላጊ ነው ማለት ነው፡፡ የወንጀል ስነስርአት ህጎች ዋና አላማና ግብም ይህ ነው፡፡ ስለሆነም የምርመራ ስራ በአንድ በኩል **<u>ተጠርጣሪውን ወንጀል መፈጸሙን የሚያስረዱ ብቻ ሳይሆን አለመፈጸሙንም ሊያረጋግጡ የሚችሉ ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ስራ ስለሆነ በምርመራ ሂደት የተጠርጣሪውን ንጹህነት የሚያሳይ ማስረጃ ከተገኘ በምርመራው መዝገብ ውስጥ መካተት ይኖርበታል ማለት ነው</u>**፡፡

በምርመራ ሂደት ማስረጃዎች ሲሰባሰቡ፣ ሲተነተኑ፣ ቀጣዩ እርምጃና ውሳኔ ሲወሰን፣ ወይም ተጠርጣሪን ለመያዝ እርምጃ ለመውሰድ ሲወሰን በሰዎች መብቶች ላይ ያላግባብ ጉዳት እንዳይደርስ ወይም ጉዳቱን ለመቀነስ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳትና መልስ ማግኘትን ይጠይቃል፡፡ ከእነዚህም መካከል…የንጹሀን ሰዎች ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ምን ማድረግ አለብኝ? በወንጀሉ ተጠርጣሪ የሆኑትን ለመለየት እና ለመቆጣጠር ምን አይነት እቅድ ሊኖረኝ ይገባል? ማን ላይ ነው እንደተጠርጣሪ ማተኮር ያለብኝ? መያዝ ያለበት ተጠርጣሪ ማን ነው? መቼ ነው? ሀይልን መጠቀም ያለብኝ መቼ ነው? ይህ እርምጃዬ ፍትህን የሚያስገኝ ነው? ማህበረሰቡን ከወንጀል የሚጠብቅ ነው? ወይስ የተወሰኑ ሰዎችን ጥቅም ለማረጋገጥ መሳሪያ

እየሆንኩ ነው? እውነተኛው ወንጀለኛ እንዲያመልጥ ወይም ሌላ ወንጀልን ለመደበቅ በሚሰራው ስራ መሳሪያ እየሆንኩ ነው?[16] የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አንስቶ ሙያዊ ስነምግባርን ባከበረ መልኩ መልስ ማግኘትን ይጠይቃል፡፡

የወንጀል ምርመራ ስራን የሚፈታተኑ የታወቁ የምርመራ አካሄድ ስህተቶች አሉ፡፡ መርማሪዎች እነዚህን ስህተቶች አውቀው ተመሳሳይ ስህተት የምርመራ ስህተት ከመስራት ሊጠበቁ ይገባል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ስህተቶች የሚባሉት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

<u>አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችና ማስረጃዎች አለመለየትና አለማሰባሰብ፡፡</u>[17] ማስረጃዎች በቀላሉ የምትፈልጋቸው ቦታ ሳይሆን በሌላ ቦታ ተደብቀው ሊሆን ይችላል፡፡ መርማሪ አእምሮውን ክፍት አድርጎ ከተለያዩ ቦታዎች መረጃዎች ሊሰባሰቡ እንደሚችሉ ማሰብና ሁልጊዜም ንቁ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠርጣሪ የሆነው ሰው ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊትና ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ የሚያሳያቸው እንቅስቃሴዎቹና ድርጊቶቹ፣ የተጠርጣሪው ያለፈ ጊዜ ታሪኩ፣ ተጎጂዎች ተብለው የቀረቡ፣ የጠቋሚዎች፣ የምስክሮች የቀድሞ ታሪክ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊትና ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ የሚያደርጉዋቸው እንቅስቃሴዎች በርካታ በግልጽ የማይታዩ መረጃዎችን ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡[18]

<u>ሁለተኛው ስህተት የተሰባሰቡትን መረጃዎች ቀጥተኛ ትርጉማቸውን ብቻ በመውሰድ ጥልቅ ትንታኔ አለማድረግ ነው፡፡</u>[19] የጥቆማ አቅራቢውን ቃል፣ የምስክሮችን ቃል፣ የተጠርጣሪን ቃል፣ የሰነድ ማስረጃዎች ኤግዚቢቶች እርስ በራሳቸው የሚናበቡ ናቸው ወይስ አንዱ ከሌላው ጋር የሚቃረን ነው? የተሰባሰቡት ማስረጃዎች ሌላ ወንጀልን እየደበቁ ነው? የተወሰኑ ወገኖችን ለማጥቃት የተዘጋጀ ድብቅ ሴራ አለ ወይ? ብሎ መተንተንን ይጠይቃል፡፡

<u>ሶስተኛውና ትልቁ ስህተት አቋራጭ መፈለግ (ወይም ቀላሉን ማብራሪያ መቀበል ነው፡፡</u>[20] ይህ አቋራጭና ቀላሉን መንገድ መምረጥ መረጃዎችን በስሜቱ ለደረሰበት ድምዳሜ በሚፈልገው መልኩ መተርጎም፣ እና በመጨረሻ ንጹሀን ሰዎችን ወደመክሰስና ወደማንገላታት በተቃራኒው

[16] Introduction to criminal investigation, p.2
[17] introduction to criminal investigaton- processes- practices-and- thinking , p.60
[18] ከላይ የተጠቀሰው ገ.61
[19] ከላይ የተጠቀሰው፣ The mistake of being too quick to proceed with charges, or even discounting and ignoring evidence that indicates innocence, is a trap that has led many investigators to the end their careers under accusations of lost objectivity or even incompetence፣ገ.16 እና 61
[20] ከላይ የተጠቀሰው፣ ገ. 63

እውነተኛው ወንጀለኛ እንዲያመልጥ የማድረግ እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ መርማሪ ከዚህ ስህተት ራሱን በመጠበቅ እንደኀበዝ መርማሪ አማራጭ ንድፈ-ሀሳቦችን እና ተጠርጣሪ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ሁልጊዜም ከግምት አስገብቶ ማስረጃዎችን ሲሰበስብም ሆነ የተሰባሰቡ ማስረጀዎችን ሲተነትን ከእነዚህ አማራጭ የወንጀል አፈጻጸሞች እና አማራጭ ተጠርጣሪዎች አንጻር እየተነተነ ምርመራውን ማስኬድ ይኖርበታል፡፡

**<u>አራተኛው ስህተት የምርመራ ስራውን በተመለከተ እኔ ወይም የእኛ የምርመራ ቡድን ብቻ ያልነው ነው ትክክል በሚል የሌሎች የስራ ባልደረቦችን አማራጭ ሀሳቦችና ትንታኔዎች ላለመስማት አእምሮን ዝግ ማድረግ ነው</u>**[21]፡፡ መረጃዎችን አግባብነት ካላቸው ሰዎች ጋር ማካፈል የተለያዩ ትርጉሞችን ለማየት፣ መርማሪው ያላየውን አቅጣጫ ለማሳየት ስለሆነም ከተሳሳተ ድምዳሜ ለመዳን ጠቃሚ ናቸው፡፡ እናም መርማሪዎች የተለያዩ ትርጓሜዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አውቀው ህሊናቸውን ክፍት አድርገው የሌሎችን እይታዎች ለመስማት ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**<u>አምስተኛው ስህተት ከሚገባው በላይ ምስጢራዊ መሆን ነው፡፡</u>**[22] በእርግጥ እንደመርማሪ በምስጢር ምርመራውን መያዝ ተገቢ ቢሆንም በጣም ከሚገባው በላይ ምስጢራዊ መሆን መረጃዎችን ለሌሎች ባልደረቦች ምስጢርን በማካፈል የተለያዩ ንድፈ-ሀሳቦችና ድምዳሜዎች ላይ የመድረስ እድሉን ይዘጋል በዚህም የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ያደርገዋል፡፡

በሙስና ወንጀል ምርመራ በዋነኛነት ትኩረቱ ስልጣንን አላግባብ የሚጠቀሙትን መመርመርና ለፍርድ ማቅረብ በመሆኑ እነዚህ ስልጣን ያላቸው ሰዎች ምርመራ ሲደረግባቸው በዝምታ የሚመለከቱት አይደሉም፡፡ የምርመራ ስራው ከመጀመሪያው እንዲዛባ፣ የምርመራ ስራው የእነሱ ፍላጎት ማሳኪያ እንዲሆን ከጥቆማ መስጠት፣ ማስረጃን በመስጠት ሂደት ሁሉ ስልጣናቸውን ከመጠቀም ወደኋላ አይሉም፡፡ ከዚህ አንጻር ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ የምርመራ ስህተቶች እንዳይሰሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በኢትዮጵያ የሙስና ወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው የወ/መ/ስ/ስ/ሕ ከቁ 22 እስከ 37 እና ከቁ. 49 እስከ 62 የሚገኙት ሲሆኑ፣ በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕግ (እንደተሻሻለው) ከሞላ ጎደል የተደነገጉት ድንጋጌዎች የምርመራ ስራውን ውጤታማነት ለማሳካት የተደነገጉ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

---

[21]ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገ. 9

[22]ከላይ የተጠቀሰው፣ ገ. 9

የሙስና ወንጀል ምርመራ ስራ ውጤታማ እንዲሆን መርማሪው ከውስጥም ሆነ ከውጭ ተጽእኖ ነጻ ሆኖ እንዲሰራ የሚያስችለው ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡[23] የሙስና ወንጀል ምርመራ ስራውን ማለትም ማስረጃ የማሰባሰብ፣ ተጠርጣሪን የመያዝና ለፍርድ የማቅረብ ስራውን በስኬታማ መልኩ ለማከናወን እንዲችልም አስፈላጊ የባለሙያ አቅም (በቁጥር በአይነትና በጥራት)፣ የፊዚካል ፋሲሊቲ፣ የሎጂስቲክስ እና የፋይናንሻል ግብአቶች ያስፈልጉታል፡፡ የሙስና ወንጀል ምርመራ የፋይናንሻል ምርመራ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት፣ የአለምአቀፍ ስምምነቶች፣ በድብቅ የወንጀል ቡድኖች ውስጥ ሰርጎ የመግባት (undercover operation)፣ የኢንተለጀንስ ስራዎችን የመስራት፣ ምስክሮችን የማዘጋጀትና የመጠየቅ ክህሎት፣ የኢንተለጀንስ መረጃዎችን የመተንተን፣ ንብረቶችን ፈልጎና አፈላልጎ የማግኘትና የማሳገድ እና ሪፖርት የመጻፍ ክህሎት ይፈልጋል፡፡[24]

የሙስና ወንጀል ምርመራን ስኬታማ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል የጠቋሚውን ማንነት በምስጢር መጠበቅ፣ ተጠርጣሪ የመንግስት ባለስልጣኖች ከምርመራ ባለሙያዎች ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ እንዳይኖር ማድረግ፣ ፋይሎችና ሪከርዶችን ያልተፈቀለደት ሰው እንዳይደርስባቸው ማድረግ፣ እንዲሁም መርማሪዎች ከተመደቡበት የምርመራ ስራ ላይ እንዳይነሱ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ የሙስና ወንጀል ምርመራ የሚደረግበት ቦታም ሲመረጥ ወደ ውስጥ የሚገባውን እና የሚወጣውን ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ ስለሆነም ያልተፈቀደላቸው እንዳይገቡ የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡

የሙስና ወንጀል ምርመራ ስራ ቶሎ መጠናቀቅ አለበት፡፡ ጊዜው በዘገየ ቁጥር ማስረጃዎች የመጥፋታቸው የመሰወራቸው እድል እየጨመረ ስለሚሄድ ወንጀሉ ተዳፍኖ የመቅረት እድሉም እየጨመረ ነው የሚሄደው፡፡

[23] United Nations Convention Against Corruption, art.6 Each State Party shall grant the body or bodies referred to in paragraph 1 of this article the necessary independence, in accordance with the fundamental principles of its legal system, to enable the body or bodies to carry out its or their functions effectively and free from any undue influence. The necessary material resources and specialized staff, as well as the training that such staff may require to carry out their functions, should be provided.
[24]APEC_investigation and prosecution of corruption p,7

## 2.6. የምርመራ እቅድ ማዘጋጀት

የወንጀል ምርመራ ስራ) እንደማንኛውም የምርምር ስራ) ሁሉ ማስረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ የማደራጀትና ሪፖርት የማዘጋጀት ስራ ነው፡፡

የወንጀል ምርመራ ስራ እንደምርምር ስራ ተመሳሳይነት ቢኖረውም ግን ያልተረጋገጠን ነገር ማረጋገጥ ስለሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ቀድሞ መገመት አይቻልም፡፡ ይሁንና ውጤቱን በእርግጥ ለማወቅ አለመቻል በእቅድ መመራት ያለበት መሆኑን ግን አያስቀረውም፡፡ የወንጀል ምርመራ ስራ ውጤታማ እንዲሆን ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ከመሄድ በፊት በቅድሚያ እንደማንኛውም የማናጅመንት ስራ እቅድ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡[25]

በሙስና ወንጀል ምርመራ ግቡ የሙስና ወንጀል መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን ማረጋገጥ፣ ወንጀሉ ተፈጽሞ ከሆነ ደግሞ ፈጸመ የተባለውን ተጠርጣሪ በመለየት ለፍርድ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር በቅድሚያ በእቅዱ ዝግጅት ሊነሳና ለሌሎች ጥያቄዎች ሁሉ መሰረት የሚሆነው ከቀረበው ጥቆማ እና ከተሰባሰቡት መረጃዎች በመነሳት ተፈጽሟል ተብሎ የሚገመተው የሙስና ወንጀል ወይም ወንጀሎች የትኞቹ ሊሆኑ ይችላሉ? የሚለው ነው፡፡

ይህንን ጥያቄ መመለስ ተጣሰ ተብሎ ሊገመት በሚችለው የሙስና ወንጀል ሊረጋገጡ የሚገባቸውን የወንጀሉን ፍሬነገሮች ለመለየት እና እነዚህ ፍሬነገሮች ስለመኖራቸው ወይም አለመኖራቸው ሊያረጋግጡ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመገመት ከዚህ በመነሳትም አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችን ለመለየትና ለማሰባሰብ የሚረዳ ነው፡፡ ተፈጽሟል ተብሎ የሚገመተው ወንጀል ወይም ወንጀሎች እነዚህ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት በእቅዱ መነሻ ካልተቀመጠ በስተቀር ልናሰባስበው የሚገባው አግባብነት ያለው ማስረጃ ምንድነው? የሚለውን ለመመለስ እንቸገራለን፡፡ ስለሆነም የማስረጃ ማሰባሰብ ስራችን ኢላማ የሌለው ጊዜና ጉልበትን የሚያባክን ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአቅጣጫ አለመቀመጥ አስፈላጊ ማስረጃዎች ሊጠፉና ሊሰወሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም በምርመራ እቅዱ በመጀመሪያ የትኛው የሙስና ወንጀል ድንጋጌ ነው የተጣሰው? ብሎ መላምት ወይም ግምት ማስቀመጥ መሰረታዊ እና ሊታለፍ የማይገባው ነው፡፡ የምርመራ መላምት ማስቀመጥ የምርመራውን አካሄድ ለመምራት አቅጣጫ ለመስጠት እንዲ

[25] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.6

የምርመራ ስራው አንዴ በተቀመጠ መላምት እንዲታጠር አይደለም፡፡ በምርመራው ሂደት በሚገኙ ማስረጃዎችና ማስረጃዎችን በመተንተን በሚገኙ አዳዲስ ግኝቶችና ድምዳሜዎች መላምቱ ሊቀየር ይችላል፡፡

ሁለተኛው መመለስ ያለበት ጥያቄ የምርመራ ስራው አሁን የሚገኝበትን ደረጃ መለየት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን በቁጥጥራችን ስር ያለው ማስረጃ ምንድነው? በቁጥጥራችን ስር ያለው ማስረጃ ትንታኔ ተደርጎበት ምርመራውን አጠናቆ ሪፖርት ለመጻፍ በቂ ነው? ካልሆነ የጎደለውና ልናሟላው የምንፈልገው ምንድነው? እንዴት ብናቅድና ብንንቀሳቀስ ነው መረጃዎቹን ልናገኝ የምንችለው? ምን አደጋዎች አሉ? እና መሰል ጥያቄዎችን በማንሳት ለእቅድ ዝግጅቱ ግብአት ማዘጋጀት ይገባል፡፡[26]

እቅዱ ሲዘጋጅም በምርመራ ሂደቱ ሊረጋገጡ የሚገባቸው ፍሬነገሮችን ለመለየት የታወቁትን ወርቃማ የምርመራ ጥያቄዎችን እያነሱ እቅዱን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡[27] እነዚህም፡-

1. ማን? ተጠርጣሪ፣ ምስክር፣ ጠቋሚ፣ ተጎጂው ማን ነው? (ስሙ፣ እድሜው፣ አድራሻቸውን፣ የቅጽል ስም ካለው፣ ቀድሞ የወንጀል ተሳትፎ ወይም ሪከርድ ያለው መሆኑ፣ ዜግነት፣ የቤተሰብ አባላት እና በጉዳዩ ያላቸው አግባብ ወዘተ..)
2. ምን? የተፈጸመው ድርጊት ምንድነው? ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የተጣሰው ስልጣን ምንድነው? የተገኘው የማይገባ ጥቅም ምንድነው? በወንጀሉ የገንዘቡ መጠን ምን ያህል ነው? በወንጀሉ ተጠርጣሪዎች ተሳትፎዋቸው ምንድነው? በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ምንድነው?
3. የት? የተፈጸመው ድርጊት የት ነው? በየትኛው መስሪያ ቤት ነው? የተገኘው የማይገባ ጥቅም የሚገኘው የት ነው? በሙስና የተገኘው ንብረት ወይም ጥቅም ወደየት ሄደ? ተጠርጣሪዎች ከየት ወደ የት ጉዞ አድርገዋል? ማስረጃው የት ሊገኝ ይችላል?
4. መቼ? ድርጊቱ የተከናወነው መቼ ነው? ወይም ከመቼ እስከመቼ የተከናወነ ነው?
5. እንዴት? ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታ እንዴት ቀነው? ከሀሳብ ወደተግባር ተቀየረ ወይም አተገባበሩ ምን ይመስላል? ማለትም የወንጀል አድራጊዎችን ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀሙበት እውቀትና ክህሎት ምንድነው? በምን አይነት እቅድ ነው የፈጸሙት? ወንጀሉን ለመፈጸም የሚያስችል ዘዴ ወይም አጋጣሚ/ ዐቅም (ሥልጣን፣ ሀላፊነት፣

---

[26]introduction to criminal investigation, p.4

[27] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.36-7,84-7

መሣሪያዎች እና አካላዊ ብቃቶችን ጨምሮ) ምንድነበር? ግንኙነት ሲያደርጉ የነበረው በምንድነው? በስልክ? ኢሜይል? ምስጢራዊ መገናኛ ቃላቶች? በሰዎች ግንኙነት ወዘተ..? ማለትም የወንጀል አድራጊዎችን ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀሙበትን እውቀትና ክህሎት ምንድነው? ምን ንብረት ተጠቀሙ? መኖሪያ ቤት? መኪና? በምን አይነት እቅድ ነው የፈጸሙት?

6. ለምንድን ነው? ወንጀሉን የፈጸሙት ምን ለማሳካት አስበው ነው? ያነሳሳቸው ምክንያት (ለምሳሌ የገንዘብ ጥቅም ወይም ብቀላ ወይስ ሌላ) ምንድነው? የኑሮ ሁኔታቸው ምን ይመስላል? ከፍተኛ ወጪ ሲያወጡ ይታወቃሉ? ቤተሰቦቻቸው ወጪ አወጣጣቸው አኗኗራቸው ምን ይመስላል? ወንጀል የመፈጸም ዝንባሌያቸው ምንድነው? አዘውታሪ ወይም ደጋጋሚ ወንጀል ውስጥ የገቡ ናቸው?
7. ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ ምን አይነት ነው?
8. ማስረጃው የት ሊገኝ ይችላል?
9. ማስረጃዎቹን ለማግኘት ምን አይነት ተግዳሮት ሊያጋጥም ይችላል? (ምን የሕግ ተግዳሮቶች ይኖራሉ?ማስረጃዎቹ ሊጠፉ ሊሰወሩ የሚችሉበት እድል ወይም ክፍተት አለ ወይ?
10. ማስረጃዎቹ ሊጠፉ፣ ሊሰወሩ የሚችሉ ከሆነ ምክንያቱ ወይም መንስኤው ምን ሊሆን ይችላል?
11. ማስረጃዎቹ ሳይጠፉና ሳይበላሹ በመርማሪው በእጅ ለማስገባት ምን አይነት እርምጃዎች ወይም ጥንቃቄዎች መደረግ አለባቸው?
12. በወንጀሉ ተገኝቷል ተብሎ የሚገመት ሀብት/ንብረት/ገንዘብ አለ ወይ? የሚገኘው የት ነው? እንዲታገድ ማድረግ ይቻላል ወይ? ለጊዜው ተጠርጣሪው እንዳይነቃና ማስረጃ እንዳያጠፋ ሳይታገድ ቢቆይ የሚደርስ ጉዳት ይኖራል? እንዲታገድ ሲደረግ ተጠርጣሪው ነቅቶ ማስረጃ ሊያጠፋ ይችል ይሆን? ስለሆነም ለጊዜው የማሳገዱ ጉዳይ ማቆየት አስፈላጊ ይሆን?
13. ተጠርጣሪዎች መቼ ተይዘው ይጠየቃሉ? ሰነዶች(ማስረጃዎች) ተጠርጣሪው ሳያውቅና ሳይነቃ በመርማሪ እጅ እንዴት ይገባሉ? ተጠርጣሪ ተብሎ የሚገመተውን ከመያዝና ማስረጃው እንዳይጠፋ ከመጠንቀቅ አንጻር ከሁለቱ ቅድሚያ የሚሰጠው ለየትኛው ነው? ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ከተለየ በኋላ አላስፈላጊ ጉዳት ለመቀነስ

እንዲቻል ምን መደረግ አለበት? ወዘተ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እቅዱን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በዋነኛነት የእቅዱ አላማና ግብ በምርመራ ሂደት ማስረጃን ለማሰባሰብ እና ተጠርጣሪን በመለየት ለፍርድ ለማቅረብ ማስረጃዎች እንዳይጠፉ፣ አግባብነት የሌላቸው ማስረጃዎች በማሰባሰብ ጊዜና ጉልበት እንዳይጠፋ እንዲሁም የመንግስት ስራ እንዳይጎዳ፣ አስፈላጊው ማስረጃ ሳይሰባሰብ እንዳይቀር፣ በምርመራ ሂደት በሰው፣ በንብረት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ አላስፈላጊ ጉዳት እንዳይደርስ ማድረግ ነው፡፡

## 2.7. ማስረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር መተንተን

የሙስና ወንጀል በጥቅሉ ሁለት ዘርፎች አሉት፡፡ አንደኛው ስልጣንን አላግባብ መጠቀም ሲሆን ሁለተኛው በዚህ ድርጊት የማይገባ ጥቅም ማግኘት ወይም ጉዳት ማድረስ ነው፡፡

የሚሰባሰቡት ማስረጃዎችም እነዚህን የሙስና ወንጀልን የሚቋቁሙ ፍሬነገሮች(1ኛ) ግዙፋዊ ፍሬነገሮች እና (2ኛ) የሞራል ፍሬነገሮች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን የሚያስረዱ ናቸው፡፡

በማስረጃ ሊረጋገጡ የሚገባቸው ግዙፋዊ የወንጀሉ ፍሬነገሮች በዋነኛነት ስልጣንን አላግባብ ጥቅም ላይ የማዋል ድርጊት፣ ከዚህ ድርጊት ጋር በተያያዘ የተጠየቀ፣ የተገኘ፣ የቀረበ ወይም የተሰጠ የማይገባ ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳት ናቸው፡፡ እነዚህም ስልጣኑ ምንድነው? ተደረገ የተባለው ድርጊት ምንድነው? ድርጊቱ በስልጣኑ ክልል ውስጥ የተሰራ ነው? ስልጣኑን በማለፍ የተሰራ ነው? ወይስ ስልጣን ሳይኖረው የተሰራ ነው? ከዚህ ድርጊት ጋር በተያያዘ የተጠየቀ፣ የተገኘ፣ የቀረበ ወይም የተሰጠ የማይገባ ጥቅም ምንድነው? ሊደርስ የማይገባ የደረሰ ጉዳት ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ነው፡፡

የሙስና ወንጀል ዋና ግቡ የማይገባ ጥቅም ማግኘት ስለሆነ፣ ይህ የወንጀሉ ዋና ፍሬነገር በመሆኑ ትኩረቱ በዚሁ በተገኘው ጥቅም ላይ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር የተገኘ ጥቅም አይነትና መጠኑ፣ የማይገባ ጥቅሙ ከማን ወደማን እንደተላለፈ እና ጥቅሙ የት እንደሚገኝ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል፡፡

የሞራል ፍሬነገርን በተመለከተ ማስረጃ የማሰባሰብ ጉዳይ አስፈላጊ የሚሆነው ማንኛውም ስልጣንን ያላግባብ በመገልገል የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ጉዳት

ለማድረስ የሚፈጸም ድርጊት በወንጀል የሚያስጠይቀው ይህንን ለማግኘት ታስቦ የተሰራ መሆኑ ወንጀሉን የሚያቋቁም የወንጀሉ ዋና ፍሬ ነገር በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተሳታፊዎች ፍላጎት፣ አላማ ምንድነው? በተሳታፊዎች መካከል የነበሩ ግንኙነቶች ምንድናቸው? የተገኘው የማይገባ ጥቅም እንዴት ተላለፈ የሚሉት የሞራል ፍሬነገሩ መኖር አለመኖሩን አመላካች ነጥቦች ናቸው፡፡

**የሙስና ወንጀል ማስረጃዎች ሊገኙ የሚችሉት የት ነው?**

በስልጣን አላግባብ መገልገል ድርጊት መፈጸሙን ማለትም አላግባብ የተሰራ ስራ መኖሩን ለማወቅ ወንጀሉ ተፈጸመበት የተባለውን መስሪያ ቤት አሰራር ማወቅ፣ ተደረገ የተባለው ድርጊት በመስሪያ ቤቱ ካለው አሰራር ጋር የተጣጣመ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማጣራት ነው፡፡ ለዚህ በዋነኛነት መሰረት የሚሆነው የመስሪያ ቤቱን አሰራር የሚደነግጉ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ቅጾች፣ ሰነዶች፣ የተጻጻፉ ደብዳቤዎች ወዘተ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በሙስና ወንጀል በማስረጃነት የሰነድ ማስረጃዎች ከፍተኛውን ቦታ የሚይዙ ናቸው፡፡

የማይገባ ጥቅም መገኘቱን በሚመለከት ገንዘቡን መከተል ነው፡፡ማን ጥቅም አገኘ? ጥቅም ሰጪው ከዚህ ምን አተረፈ? የሚለውን ለማወቅ ማለት ነው፡፡ እራሳቸው ተገኝተዋል ተብለው በጥቆማ የሚቀርቡት የጥቅም አይነቶች በራሳቸው ማስረጃዎቹ የት እንደሚፈለጉ ያመለክታሉ፡፡ ስለሙስና ወንጀሎች በተዘጋጀው የዚህ የስልጠና ሰነድ አካል በሆነው ሞጁል አንድ፣ ክፍል ሁለት፣ ንዑስ ክፍል ሁለት በሙስና ወንጀል ስለሚገኝ የማይገባ ጥቅም አይነቶች እንዲሁም ሙስና የሚፈጽሙ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች የሚቀበሉት የማይገባ ጥቅም አይነቶች ተዘርዝረዋል፡፡

የደረሰ ጉዳትን በሚመለከት በጥቆማው መሰረት ደረሰ የሚባለው ጉዳት ከድርጊቱ ይዘት መገመት ስለሚቻል ከዚሁ ተነስቶ ጉዳቱ መድረሱን ማረጋገጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በድርጊቱ የተጎዳ ሶስተኛ ወገን ከሆነ ይህ ወገን ራሱ ጠቋሚ የመሆን እድሉ ወይም ምስክር የመሆን እድሉ ከፍተኛ ስለሚሆን የደረሰውን ጉዳት ማስረጃዎችን ከዚሁ ሰው ማሰባሰብ ይቻላል፡፡ ደረሰ የተባለው ጉዳት በመንግስት ጥቅም ላይ ከሆነም ድርጊቱ ተፈጸመበት የተባለው መስሪያ ቤት ላይ የደረሰውን ጉዳት ከራሱ ከመስሪያ ቤቱ ሀላፊዎችና ሰራተኞች ማግኘት ይቻላል፡፡

**ስልጣን አላግባብ መገልገልና በተገኘው ጥቅም መካከል ግንኙነት መመስረት**

ከተወሰኑት የሙስና ወንጀሎች (ምንጩ ያልታወቀ ሀብት (አንቀጽ 21) እና ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት ወይም መቀበል(አንቀጽ 19 እና 26) በስተቀር የሙስና ወንጀልን ለማቋቋም በስልጣን አላግባብ መገልገሉ እና በተገኘው ጥቅም ወይም በደረሰው ጉዳት መካከል ምክንያታዊ ትስስር መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻርም ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል፡፡ በተፈጸመው የስልጣን አላግባብ መገልገል የተጠቀመው ወገን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስልጣን ላለው ተጠርጣሪ ወይም ቤተሰቦች ጥቅም መስጠቱን ማረጋገጥ ከተቻለ (ማለትም መስጠቱ ከታወቀ) በመካከላቸው ግንኙነት አለ ማለት ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በዚህ ድርጊት በአንድ ሌላ ሰው (ለምሳሌ ተወዳዳሪ ነጋዴ ላይ) የደረሰው ጉዳት(ፈቃድ መከልከል፣ ወይም ለማደስ መከልከል) ጥቅም ሰጪውን የሚጠቅመው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘት ከተቻለ ምክንያታዊ ግንኙነት አለ ማለት ነው፡፡

ቀጣዩ ጥያቄ እነዚህ ድርጊቶች መካከል የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ቢኖርም ሆነ ተብሎ የተደረገ ስለመሆኑ ማስረጃ ማሰባሰብ ነው፡፡ ህጉ የሞራል ፍሬነገር (የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ለመጉዳት አስቦ ማድረግ) ስለመኖሩ ግምት ይወሰዳል ማለቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በግምት ላይ ከመንጠልጠል ተጨባጭ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ይመረጣል፡፡ ከዚህ አንጻር የተጠርጣሪውን የህሊና ሁኔታ ሊያሳዩ ሊያመለክቱ የሚችሉ ደብዳቤዎች፣ ንግግሮች በተቻለ መጠን በማስረጃነት ሊሰባሰቡ ይገባል፡፡

**የመረጃ ወይም የማስረጃ ምንጮች**

በገንዘብ ወይም በንብረት መልክ የተገኙ የማይገቡ ጥቅሞች ወይም የደረሱ ጉዳቶችን በተመለከተ ግልጽ የመረጃ ምንጮች (ኢንተርኔት፣ መገናኛ ብዙሀን፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች፣ የፍቺ እና የመሳሰሉት የፍርድ ቤት ክርክሮችና ውሳኔዎች(የሀብት ክፍፍል መረጃዎች)፣ የኪሳራ ውሳኔዎች፣ አስተዳደራዊ እና ዲሲፕሊናዊ ክርክሮችና ውሳኔዎች፣ በጉዳዩ ግንኙነት አለው ተብሎ የሚጠረጠር ድርጅት አድራሻው፣ አደረጃጀቱ፣ የሚሰራባቸው ቦታዎች፣ የስራ ዝርዝር እና ሀላፊነቱ፣ ገንዘብ ዝውውሩ፣ የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴው (ከሌሎች ተመሳሳይ ካምፓኒዎች ጋር በማመሳከር)፣ የክንውን እና የፋይናንስ ሪፖርቶች፣የተለያዩ የኢንስፔክሽን ሪፖርቶች፣የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የኢንሹራንስ መረጃዎች፣ የባንክ የገንዘብ እንቅስቃሴ መረጃዎች፣ ንብረቶችና የንብረት ምዝገባዎች፣የሀብትና ንብረት መግለጫዎች፣ የአገር ውስጥ ገቢ ወይም የጉምሩክ መረጃዎች (የታክስ ክፍያዎችና ገቢዎች መጠን እና ከየት እንደተገኙ)፣ የፋይናንሻል ሞኒተሪንግ መረጃዎች፣የተመዘገቡ ወጪዎች፣ የሽያጭ ስራው ክንውን፣ የተላኩ ግብዣዎች ፣ በሂሳቡ

መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡ የሆቴል ደረሰኞች፣ ፓርኪንት ቲኬቶች፣ የምሳ ደረሰኞች፣ የበረራ ቴኬቶች ወዘተ)፣ ሶስተኛ ወገን ወኪሎችን ስለመጠቀማቸው፣ የፖለቲካ ፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ የሀብት ምንጮች፣ የምርጫ ቦርድ ወይም የመሳሰሉት ኮሚሽኖች መረጃዎች፣ ለእርዳታ ድርጅቶች የተሰጡ እርዳታዎች (የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሪከርዶችና የፋይናንሻል ስቴትመንቶች)፣ ሌሎች በሂደት ላይ ያሉ የወንጀል ምርመራዎች፣ የተጠርጣሪ አኗኗር ሁኔታ ህገወጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ናቸው ተብለው ከሚገመቱ ጋር ሊኖር የሚችል ግንኙነቶች፣ የተሰጡ ወይም የታደሱ የንግድ ፈቃዶች፣ ምዝገባዎች …… ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[28]

ተጠርጣሪ በሆኑት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛውን በተመለከተ ህጋዊ ገቢው፣ ያስመዘገበው የሀብትና ንብረት መግለጫ፣ መኖሪያ ቦታው፣ እንዲሁም የእሱንና የቤተሰቡ አባላትን ጨምሮ የፋይናንሻል መረጃዎች፣ መኖሪያ እና በግል የያዙት ንብረት፣ የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴ፣ ለከፍተኛ ትምህርት፣ ለህክምና የተከፈሉ ክፍያዎች፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጉዞዎችና ለጉዞ የወጡ ወጪዎች(ትራንስፖርት፣ የሆቴል ወጪዎች ወዘተ)፣ የቤተሰቡ አባላት ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነ የት? መቼ? እና እንዴት? ስራውን አገኙትና የመሳሰሉት የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ህጋዊ እውቅና ባላቸው የውድድር(የቁማር) የንግድ ቦታዎች በህገ ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ ለማድረግ አመቺ ቦታዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ተጠርጣሪ የሆኑት የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው እና ተጠርጣሪ የሆኑ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች ሀላፊዎች በእነዚህ ቦታዎች የሚያዘወትሩ መሆኑ፣ በእነዚህ የውድድር መድረኮች ያገኙዋቸው ክፍያዎች በሙስና ወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ጥቅም ስለመሆኑ የመረጃ ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

### መረጃዎችና ማስረጃዎችን እንዴት ማግኘት ይቻላል?

የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ በሚደረግ ምርመራ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማግኘት በተቻለ መጠን ድብቅ በሆነ መልኩ ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ መስራት ለውጤታማነቱ ይመከራል፡፡ [29]በተቻለ መጠን በእጅ ሊገቡ የሚችሉ ማስረጃዎችን ሁሉ መሰብሰብ ይመረጣል፡፡ በመጀመሪያ አግባብነት ያላቸውና የሌላቸው ብሎ ተጠንቅቆ መርጦ ከመሰብሰብ እና በኋላ ይሄ ማስረጃ

[28] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.39-40
[29] APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption, p.14-15

ብሰበስብ ኖሮ ከማለት፣ በመጀመሪያ በእጅ ሊገቡ የሚችሉ ማስረጃዎችን በሙሉ ሰብስቦ በኋላ አላስፈላጊ የሆኑትን ከምርመራ ሰነዱ ማውጣት ይመረጣል፡፡[30]

ተጠርጣሪዎች ነቅተው ማስረጃ የማጥፋትና የመሰወር ስራ ውስጥ እንዳይገቡ፣ ማንነታቸው ሳይታወቅ ወይም በምን ጉዳይ መረጃ እንደሚያሰባስቡ የማይታወቁ መረጃ አሰባሳቢዎች ማለትም በተቻለ መጠን እንደመርማሪ ሳይሆን እንደተራ ሰው ሆነው ማስረጃ የሚያሰባስቡ መርማሪዎችን አሰማርቶ መረጃ የማሰባሰብ ስራን መስራት ያስፈልጋል፡፡

በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች ተሰርተዋል ተብለው የሚጠረጠሩ የሙስና ወንጀሎችን በተመለከተ ከስራው ጋር ግንኙነት ካላቸውና ስለተፈጸመው ነገር እውቀት አላቸው ተብለው ከሚገመቱ ሰራተኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ወይም በሌሎች አማካይነት በማመቻቸት ስለተፈጸሙ ወንጀሎች በርካታ መረጃዎችንና ፍንጮችን ለማግኘት ያስችላል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ገንዘብ በማቀባበል ላይ የተሰማሩትን ለይቶ ለማወቅ፣ በሰንሰለቱ ከፍተኛ ተጠቃሚ ሳይሆን አነስተኛ ተጠቃሚ የሆነውን እና ተጠቃሚነቱ በሚገባው መጠን አይደለም ብሎ ቅሬታ የሚያቀርበውን ወገን ለይቶ ለማግኘትም ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ማንነታቸውን በመደበቅ (እየተከፈላቸውም ሆነ ሳይከፈላቸው) መረጃ የሚያቀብሉ ሰዎችን መጠቀም የተደበቀውን ወንጀል ለማግኘት በሙስና ወንጀል ውጤታማ እንደሆነ የሚጠቀስ ነው፡፡ ከባድና ውስብስብ የሙስና ወንጀሎችን ለማጋለጥ የሀሰት ካምፓኒዎችን ፈጥሮ ወደእነዚህ የወንጀል መዋቅሮች ገብቶ መረጃ ማሰባሰብ በድብቅ በመግባት በሌሎች አገሮች አልፎ አልፎ የሚተገበር ነው፡፡[31]በኢትዮጵያ የተደራጀ ወንጀል ቡድን ውስጥ በድብቅ በመግባት ማስረጃዎችን ማሰባሰብን የሚፈቅድ ወይም የሚከለክል ህግ የለም፡፡ ይሁንና ግብረአበርን ወደምስክርነት ማዞር እንደሚቻል የሚፈቅድ ድንጋጌ በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 43 ስለሚገኝ በድብቅ የወንጀል ቡድን ውስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በማሰባሰብ መረጃ አሰባሳቢውን ምስክር ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ መተግበር እንደሚቻል መገመት ይቻላል፡፡ በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 46(2) ለሙስና ወንጀል ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በካሜራ፣ በድምጽ መቅረጫ እና የመሳሰሉት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካይነት ማስረጃዎች ለማሰባሰብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ መርማሪው እነዚህን የመቅጃ መሳሪያዎች እንደሁኔታው ተጠርጣሪው ሰው ቤት

---

[30] introduction to criminal investigation, It is better to collect everything that could possibly be relevant or could become relevant፣ገ.113

[31]APEC handbook best practices in investigating and prosecuting corruption,p.39፣ የተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ስምምነት አንቀጽ 50

ወይም ሌላ ቦታም ቢሆን በማድረግ መቅዳትና ማስረጃዎቹን መሰብሰብ ከቻለ በማስረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ማንነታቸው የማይታወቁ መረጃ አቅራቢዎችን መጠቀም፣ በድብቅ በመግባት እና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ሁለት አይነት ጥቅም አላቸው፡፡ አንደኛው ተከሳሹን/ተከሳሾችን ለማስቀጣት ጠንካራ ተአማኒነት ያለው ማስረጃ ለማግኘት ያስችላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የወንጀል አድራጊዎችን እቅድ ቀደም ብሎ አውቆ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ለመከላከል ያስችላል፡፡[32]

በሙስና ወንጀል ምርመራ አገልግሎት ጠያቂ መስሎ በመቅረብ የተጠረጠረን የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛን መፈተን እንደአንድ ጠቃሚ የሙስና ወንጀልን ማጋለጫ መንገድ ለመጠቀም ይመከራል፡፡[33] በኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ የህግ ማስከበር ስራ በተለይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የማይቆርጡትን ለመያዝ እንዲህ አይነቱ የምርመራ ስልት ውጤታማ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የገንዘብ እንቅስቃሴ ሁልጊዜም አሻራ እየጣለ ይሄዳል፡፡ እናም የፋይናንሻል ሰነዶችና የገንዘብ እንቅስቃሴዎች በአግባቡ ከተመረመሩ የገንዘቡ የወንጀል ምንጭን ለማወቅ የሚያስችል ይሆናል፡፡ የፋይናንሻል ምርመራ የተለያዩ መንገዶችን ሊከተል ይችላል፡፡ ከእነዚህ መካከል ዝርዝር ክፍያዎችን መተንተን፣ ገቢና ወጪን መተንተን፣ አጠራጣሪ የሆኑ የፋይናንሻል ገንዘብ እንቅስቃሴዎችን መተንተን ያካትታል፡፡ የባንክ ሂሳብ ሲመረመር ሁሉም ገቢዎች ምንጫቸው እና አላማቸውን ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም ወጪ የተደረጉትን በሙሉ የት እንደገቡ? ለምን አላማ እንደተከፈሉ? መመርመርና ማጣራት በመጨረሻም በሂሳቡ የመጀመሪያ የመጨረሻ ያለውን የሂሳብ ሁኔታ ማነጻጸርን ያካትታል፡፡[34] ከፋይናንሻል ምርመራ ጋር በተያያዘ የሀሰት ደረሰኞችን፣ የሂሳብ መዝገቦችን መፍጠር፣ ወይም የሀሰት ወይም ያልተሟላ መረጃዎችን መያዝ፣ ወይም መመዝገብ ያለበትን መረጃ ወይም ክፍያ ሳይጠቀስ መቅረቶች ስለተገኙት ጥቅሞች የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት መረጃዎችን ለማግኘት በዋነኛነት የፋይናንሻል ፎረንሲክ ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

[32] APEC Handbook, p. 10
[33] UN anti-corruption toolkit (2004),p. 386
[34] ከላይ የተጠቀሰው፣

በሙስና ወንጀል ምርመራ ማስረጃዎችን ለማግኘት እንዲቻል በህግ ለምርመራ አካል የተሰጡ ስልጣኖች አሉ፡፡ እነዚህም፣

1. በፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 433/97 አንቀጽ 26[35] የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ስልጣን ያለው ማንኛውም መርማሪ በፌዴራልም ሆነ በክልል መስሪያ ቤት መረጃ ሲጠይቅ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ መረጃውን የማሳየት ወይም የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡
2. በልዩ ስነስርአት ህግ አንቀጽ 46 (1) ለሙስና ወንጀል ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በስልክ፣ በቴሌኮሚኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚደረግ ግንኙነት እንዲሁም ደብዳቤ እንዲጠለፍ አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊ ማዘዝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 2(3) እንደተደነገገው የሙስና ወንጀልን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡
3. በልዩ ስነስርአት ህጉ እንደተሻሻለው በአንቀጽ 44(4) ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ስልክ በመደወል ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ ወይም ምስክርን፣ ጠቋሚን፣ ባለጉዳይን፣ መርማሪን፣ አቃቤ ህግን ወይም ዳኛን ያስፈራራ ሰውን ማንነት እና አድራሻ ጉዳዩ የሚመለከተው የቴሌኮሚኒኬሽን አካል እንዲያሳውቀው አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊ ሲጠይቀው መረጃውን ማለትም የደዋዩን ማንነትና አድራሻ ሳይዘገይ መረጃውን መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን የግል ግንኙነት በህግ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር የማይደፈር ስለመሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 26(2) የተደነገገ በመሆኑ፣ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ማድረግ ህገመንግስቱ ያስቀመጠውን መሰረታዊ የግል ግንኙነት የመከበርና የመጠበቅ መብት ማክበር ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጠለፋው የተገኘው ምስጢር ለምርመራው አላማና ምርመራውን በሚጠቅም መልኩ ከማዋል በስተቀር ለሌላ አላማ ሰውየውን ለመጉዳት ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙ ከማድረግ ድርጊት መታቀብ ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ጠለፋው እንዲደረግ ፈቃድ የሚሰጠው በልዩ ስነስርአት ህግ አንቀጽ 46(3) እንደተደነገገው ለጠለፋው ምክንያት የሆነውን ወንጀል እና ጠለፋው የሚቆይበትን ጊዜ የሚጠለፈው የስልክ ግንኙነት ከሆነ ጠለፋው የሚመለከተውን

---

[35] ይህ አዋጅን የሚተካ የስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁ. 1236/2013 ወጥቶአል፡፡ ይሁንና ይህ አዲሱ አዋጅ አዋጅ ቁ.433/97ትን ሙሉ በሙሉ አልሻረውም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 24(1) የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች በሚለው ድንጋጌ ስር በአዋጅ ቁ.433/1997 እንደተሻሻለው ተደንግገው የነበሩ እና በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል ነው የሚለው፡፡ በአዋጅ ቁ. 1236/2013 የሙስና ወንጀልን ስለመጠቆም መብት ወይም ግዴታ የሚደነግግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም ይህ ድንጋጌ ያልተሸረ እና አሁንም ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌ ነው፡፡

የግንኙነት መስመር መግለጽ ይኖርበታል፡፡ አግባብ ያለው አካል የበላይ ሀላፊ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በቀር ትእዛዙ የሚጸናው ከአራት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጠለፋ ምክንያት በማስረጃነት እንዲቀርብ ሊሟሉ ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ በልዩ ስነስርአት ህጉ አንቀጽ 47(1) እንደተደነገገው ትእዛዙን የሚፈጽመው አካል በእያንዳንዱ ጠለፋ የተቀዳውን እና ጠለፋው የተጀመረበትንና ያበቃበትን ሰአት መመዝገብ እንደሚኖርበት እንዲሁም በአንቀጽ 47(2) እንደተደነገገው ትእዛዙ የተላለፈለት አካል በጠለፋ ከተቀዳው ውስጥ ከወንጀሉ ጋር በተያያዘ እውነቱን ለማወቅ የሚረዳውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ የሚኖርበት መሆኑ ነው፡፡

4. በወንጀል ምርመራው ተጠርጣሪ ያልሆነ ሶስተኛ ወገን እጅ ሊገኝ የሚችል ማስረጃን በተመለከተ በፍርድ ቤት ፈቃድ ማስረጃውን ማግኘት እንደሚቻልም በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 42 ተደንግጎአል፡፡ አንድ መርማሪ ወይም አቃቤ ህግ አንድ ተጠርጣሪ በወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆኑን ወይም ከወንጀል ድርጊት የተገኘውን የጥቅም መጠን ወይም የሚገኝበትን ቦታ ለማወቅ አግባብ ያለው ሰነድ በእጁ ያለ ወይም የሚገኝበትን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወይም አካል እንዲሰጠው ወይም እንዲያይ ለፍርድ ቤት ሲያመለክትና ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን አግባብነት ያለው ሆኖ ካገኘው ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው መጥራት ሳያስፈልግ በእጁ የሚገኘውን ወይም ይገኛል ተብሎ የሚጠረጠረውን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ በሚወስነው ቀን ውስጥ ሰነዱን ለመርማሪው ወይም ለአቃቤ ህጉ እንዲሰጥ ወይም እንዲያሳይ ለማዘዝ ይችላል፡፡

5. ገንዘብን ማጠብ (ህጋዊ አድርጎ ማቅረብ) ጋር በተያያዘ ከአገር ውጭ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ያጸደቀችው የተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ስምምነት የውጭ አገራት እንዲተባበሩ ያበረታታል፡፡ ኢንተርፖል ከዚህ አንጻር ግንኙቶችን ለማቀላጠፍ ስለሚረዳ እንዲሁም መረጃዎችን ለመለዋወጥ ሊረዳ ስለሚችል በግል ግንኙነትና እውቅና) ይህንን ምቹ ሁኔታ መጠቀም ይገባል፡፡[36]

## 2.8. ምስክሮችን ስለመለየት የምስክሮችን ቃል ስለመቀበል

የሙስና ወንጀል መፈጸሙን እና በወንጀሉ ተሳታፊ የሆኑ ተጠርጣሪዎችን እና የጥፋት ደረጃቸውን የተገኘውን ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳት በተመለከተ የሰው ምስክሮች ከፍተኛ የማስረጃ ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡ በስልጣን አላግባብ መገልገል ወንጀል ከስራው ጋር የሚገናኙ

[36] UN anti-corruption toolkit (2004),p. 412

የመንግስትና የህዝባዊ ድርጅት ተቀጣሪ ሰራተኞች(ተላላኪ፣ ጸሀፊ፣ ጥበቃ ሰራተኛ ወዘተ ጨምሮ)፣ የፋይናንስ ሰራተኞች፣ ኦዲተሮች፣ በመንግስት ግዢ ተሳታፊ የሆኑ ተሸናፊ ተወዳዳሪዎች ሙስናን በመጠቆም መረጃ በመስጠት ምስክር በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ በሙስና ወንጀሉ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የወንጀሉ ሰለባ ስለሚሆኑ ስለወንጀሉ አከናወን ሆነ ስለደረሰባቸው ጉዳት ማስረጃ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ ተሳታፊ የሆኑ ነገር ግን እንደጠበቁት ብዙ ጥቅም ያላገኙ ወይም በጥቅም ክፍያ ጉዳይ የተጋጩም ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[37]

በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 30 እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው በመርማሪው ጥሪ ሲቀርብለት የመቅረብ፣ የሚሰጠው መልስ ራሱን የሚያስወነጅለው እስካልሆነ ድረስ ለሚቀርብለት ጥያቄ ሁሉ እውነተኛ መልስ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡[38]

ፖሊስ/መርማሪ የምስክሩን ቃል ሲቀበልም ተጠያቂውን መደለል፣ ወይም እንዲደለል ማድረግ የተስፋ ቃል መስጠት የማስፈራራት የሀይል ስራ ወይም ሌሎች ከህግ ውጭ የሆኑ ዘዴዎች መፈጸም ወይም ማድረግ ወይም መጠቀም እንደማይችል በግልጽ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 31 ተደንግጓል፡፡

የሙስና ወንጀልን ልዩ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ወንጀሉ ሲፈጸም የነበሩ ወይም ተሳታፊ የሚሆኑ ወገኖች ሁሉ ተጠቃሚ መሆናቸው ነው፡፡ ይህንኑ ግምት ዉስጥ በማስገባት በወንጀል የተሣተፈ ሰው ከክስ ነፃ በማድረግ ወደ ምስክር ማዞር የሚያስችል ስርዓት በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 43 ላይ ተደንግጓል፡፡በዚህ አንቀጽ በሙስና ተካፋይ የነበረ ሰዉ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ድርጊትና ስለተካፋዮቹ ሚና ጠቃሚ መረጃ የሰጠ እንደሆነ ወደ ምስክር ሊዞር ይችላል፡፡

ጠቃሚ ማስረጃ የሚባለውም፡-

- የቀረበዉ ማስረጃ ብቻዉን ወይም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በመቀናጀት የጥፋተኛነት ዉሳኔ ለማሰጠት በቂ ከሆነ፤ ወይም
- ማስረጃዉ በመገኘቱ ሌሎች መረጃዎችም ለማግኘት መሰረታዊ ፍንጭ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነና፣

[37]APEC_investigation and prosecution of corruption,p. 10
[38]የሚሰጠው ቃል ራሱን ሊያስወነጅል የሚችል ከሆነ ግን በህገመንግስቱ አንቀጽ 20(3) እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ እንዲመሰክር ያለመገደድ ህገመንግስታዊ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

- ይኸዉ ማስረጃ ባለመካተቱ ወንጀሉን ለማረጋገጥ በሌላ መልኩ የተሰባሰበዉ ማስረጃ በቂ የማይሆን ነዉ ተብሎ ሲታመን ነዉ፡፡

ወደምስክር የዞረዉ ሰዉ የሚሰጠዉ ምስክርነት ክብደት ማናቸዉም ምስክር ከሚሰጠዉ ጋር እኩል ዋጋ ያለዉ ነዉ፡፡ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት የሚለዉ ፍሬ ነገር የክሱን ጫና በማመዛዘን ራስን ነፃ ለማዉጣት የሚያስቡ ሀሰተኛ ምስክሮችን ለመከላከል እንደሆነ ይገመታል፡፡

**ምስክሮችን በተመለከተ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች**

የሙያ ምስክር ከሚሆነው ውጭ ተራ ምስክር በተመለከተ ከምስክሩ የሚሰባሰበው ማስረጃ የግል አስተያየቱን ሳይሆን ስለወንጀሉ እና ስለተጠርጣሪው የሚያውቀውን ማለትም ያየውን፣ የሰማውን ወይም በስሜት ህዋሳቱ አማካይነት ስለተረዳቸው ስላወቃቸው ነገሮች ነው፡፡ ምስክሮቹ ስለወንጀሉ መፈጸም ወይም ስለወንጀል አድራጊው ወይም ወንጀል ስለተፈጸመበት ሰው ያወቁት በቀጥታ ነው በተዘዋዋሪ? በአይናቸው ተመልክተዋል? በጆሮአቸው ሰምተዋል? ወይም በሌላ የስሜት ህዋሳታቸው ተረድተዋል? ወይስ ሌሎች ሰዎች ሲያወሩ ሰምተው እየተናገሩ ስለመሆኑ በግልጽ አጣርቶ ምስክርነቱን መቀበል ይኖርበታል፡፡

መርማሪ የምስክሮችን ቃል ሲቀበል የሚከተሉት ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ከግምት በማስገባት ምርመራው አላማውን እንዳይስትና ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድ፣ እውነተኛ ወንጀል እንዳይደበቅ፣ ወይም እውነተኛ ወንጀለኞች እንዳያመልጡ እና ንጹሀን እንዳይጎዱ አእምሮውን ክፍት አድርጎ ከሁሉም አቅጣጫ ለማየት በሚያስችለው መልኩ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

1. ምስክሮች(የሙያ ምስክሮችን ጨምሮ) በተለይም በሙስና ወንጀል እነሱ ራሳቸው ዋናው ወንጀል ፈጻሚ ወይም በወንጀል ድርጊቱ የተነካኩ፣ ወይም ለራሳቸው ጥቅም የሚፈልጉ፣ ወይም በሀሰት የተደራጁም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በግብረአበርነት ተሳታፊ የነበሩ ወደምስክርነት እንዲዞሩ ሲደረጉ ከተጠያቂነት ነጻ የሚሆኑ በመሆናቸው በጉዳዩ ላይ ጥቅም እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ያልተፈጸመን ነገር ተፈጸመ በማለት የተፈጸመ ነገርን በመደበቅ ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2. መርማሪው ምስክርነቱን የሚቀበለውን ሰው የህይወት ታሪኩን ከግምት ማስገባት ያስፈልገዋል፡፡ ለምሳሌ በቀድሞ ታሪኩ በሀሰት በመመስከር የሚታወቅ ከሆነ የሚያቀርበው ምስክርነትም ከዚህ አንጻር በሀሰት የተዘጋጀ ሊሆን ይችላል፡፡[39]
3. አንዳንድ ጊዜ ምስክሮች የሚሆኑ ሰዎች በጉዳዩ ባለጉዳይ በመሆን በመሆን በትክክል የሚያውቁትን ከመናገር ወይም የማያውቁትን አላውቅም ከማለት ይልቅ የራሳቸው ግምታቸውን እውነት ለማድረግ በመፈለግ እንዳዩት ወይም እንደሰሙት አድርገው ሊመሰክሩ ይችላሉ፡፡
4. በሌላ በኩል ምስክሮች ሊደርስባቸው የሚችለውን የአካላዊ ስነልቡናዊ ወይም ሌሎች ዛቻና ጥቃቶችን በመፍራትም ራሳቸውን ከዚህ ለማዳን እውነተኛ ያልሆነ ወይም የተበረዘ ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
5. ምስክሮች ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ ወይም የሚዲያ ተጽእኖን በመፍራትም ትክክለኛ ያልሆኑ ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
6. ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለው ጊዜና ምስክሩ ምስክርነቱን በሚሰጥበት ጊዜ መካከል ከፍተኛ የጊዜ ርቀት ካለ መርሳት ወይም አለማስታወስ ብቻ ሳይሆን ያልሆነን ነገር ሆነ ብለው በቀናነት ሊመሰክሩም ይችላሉ፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በDNA ምርመራ ወንጀለኛ አለመሆናቸው ከተረጋገጡት ከ70-90 በመቶ ለቅጣት የተጋለጡት በምስክሮች የተሳሳተ ወይም ሆነ ተብሎ በተደራጀ ምስክርነት እንደሆነ ነው፡፡[40]ስለሆነም ሰዎች በምስክርነት ሲፈለጉ እና የምስክር ቃል አቀባበል ጊዜ እነዚህ የጥንቃቄ ጉዳዮች ምንጊዜም ከመርማሪው ህሊና ሊጠፉ አይገባም፡፡

### ምስክርነትን በመቀበል ጊዜ ሊተገበሩ የሚገባቸው መርሆዎች

ምስክሮች ሌሎች ምስክሮች ከሚናገሩት ጋር ሀሳባቸውን ለማጣጣምና ላለመለየት ሲሉ የማያውቁትን ወይም ከሚያውቁት እውነታ በተቃራኒ ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ከምስክሮች መካከል ተጽእኖ አድራጊ ምስክሮች የሚባሉ የሌሎችን ምስክሮች ቃል ተጽእኖ የሚያሳድሩ አሉ፡፡

---

[39]introduction to criminal investigation, p.90

[40]Introduction to criminal investigations.p. 94.In 1996, for example, the National Institute of Justice in the United States released a report concerning the implications of eyewitness testimony and false memories, and in it, reported that 90% of all DNA exoneration cases defendants were wrongly convicted upon the false memories of eyewitnesses (Brainerd, 2005). More
recently, Smarlarz and Wells (2015), citing *The Innocence Project,* noted that eye-witness testimony was used to convict innocent people in over 70% of DNA exoneration cases. More recently yet, Rose and Beck (2016) note that eyewitness testimony accounts for more wrongful convictions than anything else.

[41] ምስክሮች ለእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሊጋለጡ እንደሚችሉ ተገንዝቦ ምስክሮች ምስክርነት ከመስጠታቸው በፊት እንዳይገናኙ ወይም እንዳይተዋወቁ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህ ካልተቻለም እያንዳንዱ ምስክር ሲጠየቅ ለብቻው እንዲሆን፣ እናም ከሌሎች ጋር በጉዳዩ ላይ የተወያዩ ስለመሆኑ መጠየቅ፣ ወይም ሌሎች ሲናገሩ የሰሙ ስለመሆናቸው መጠየቅና የእነዚህ የሰሙዋቸው ቃላቶች ከግምት ባላስገባ ሁኔታ የራሳቸውን የሚያውቁትን ብቻ እንዲመሰክሩ፣ የሚሰጡት ምስክርነትም ሌሎች ሳያውቁት በምስጢር እንደሚያዝም ሊነገራቸውና እንዲረጋጉ ማድረግ ይገባል፡፡[42]

የምስክሮችን ደህንነታቸውን መጠበቅና ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታና ሁኔታ ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣ እንደሁኔታው ወደምርመራ ቦታም ወይም ወደፍርድ ቤት ለምስክርነት ሲሄዱ የትራንስፖርትና የጥበቃ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

**የምስክር ቃል አቀባበል ጊዜ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች እንዲከበሩ ይመከራል፡፡**[43]

1. ምስክርነት በሚሰጥበት ክፍል በቂ ወንበርና ጠረጴዛ እንዲኖር ማድረግ፣ በክፍሉ የምስክሩን ሀሳብ ሊሰርቅ የሚችል ምንም አይነት ስእልም ሆነ ፎቶግራፎች እንዳይኖር ማድረግ፣ አስፈላጊ ከሆነም ከገጠር ወይም ከሩቅ ቦታ ለሚመጡ ወደሚገኙበት በመሄድ ምስክርነታቸውን መቀበል ሊመረጥ ይችላል፡፡
2. ምስክርነቱን ከመስማት በፊት እስካሁን የተሰባሰቡትን ማስረጃዎች አጭር መግለጫ ማዘጋጀትና አንብቦ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡
3. ከእያንዳንዱ ምስክር ምስክርነት ከመቀበል በፊት ስለምስክሩ ማንነት ማጣራት፣ በምን ጉዳይ ላይ ምን አይነት ምስክርነት ሊሰጡ እንደሚችሉ መገመት እና እነዚህን ከምስክሩ የሚፈለጉ የምስክርነት ቃሎችንና ማስረጃዎችን እንዴት ማግኘት ይቻላል ለሚለው ቅድመዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

---

[41] ከላይ የተጠቀሰው ገ. 94
[42] ከላይ የተጠቀሰው ገ. 94
[43] Introduction to criminal investigation, 96-98

**ምስክሩ ወደ ምስክርነት መስጫ ክፍሉ ሲገባ፣**

1. በመጀመሪያ ለምስክሩ በአክብሮት ተቀብሎ እንዲቀመጥ ከተደረገ በኋላ ለምስክርነት የተጠራበት ምክንያት፣ እናም እንዲናገር የሚፈለገው እውነቱን የሚያውቀውን ብቻ እንደሆነ ይህ የምስክርነት ቃሉ ፍርድ ቤት በማስረጃነት እንደሚቀርብ ሊነገረው ይገባል፡፡
2. በመቀጠል ምስክሩ በራሱ ቋንቋ የሚያውቀውን በመሰለው መንገድ እና በራሱ ፍጥነት እንዲገልጽ እድል መስጠት ነው፡፡ (Obtain a Narrative Overview)[44]በዚህ ጊዜ መርማሪው በቀጣይነት ሊያነሳቸው የሚፈልጋቸውን ጥያቄዎች ምስክሩ ከሚናገረው በመነሳት በማስታወሻው ላይ እየያዘ ከመቆየት ያለፈ እንዲያቋርጠው አይመከርም፡፡ እነዚህ የሚይዛቸው ማስታወሻዎች ምን ተፈጸመ? መቼ ተፈጸመ? የት ተፈጸመ? ለምን ተፈጸመ? እነማን ነበሩ? እንዴት ተፈጸመ? በማለት በቀጣይነት ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መነሻ የሚሆኑ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ መስካሪው ራሱ ወንጀል አድራጊው እና በወንጀሉ ተሳታፊ ሊሆን ስለሚችል እንደፈለገ በነጻነት ያለገደብ እንዲያወራ ሲፈቀድለት የእሱን ተሳትፎ የሚገልጹ ነገሮች አፈትልከው ሊወጡ ይችላሉ፡፡ ይሁንና እንዲህ አይነት እራሱን በወንጀሉ ተጠያቂ የሚያደርገው ነገር መናገሩን ተከትሎ ምስክሩን ከማፋጠጥ በተቻለ መጠን በዚህ መልኩ ሊጠየቅ የሚችል መሆኑን እንዳያውቅ፣ በቂ መረጃ እስኪገኝ ድረስ ጉዳዩን በምስጢር በመያዝ ምስክርነቱን እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡[45]
3. ምስክሩን እየሰማሀው መሆኑን እንዲረዳው እና በንቃት ምስክርነቱን እንዲቀጥል አልፎ አልፎ ምስክሩ የተናገረውን ደግመህ በመናገር ስታረጋግጥለት የምትከታተለው መሆኑን አውቆ ይቀጥላል፡፡ በተቃራኒው ፊትህን በማዞር የተለያዩ ነገሮችን በመስራት ላይ ከሆንክ ምስክሩ

---

[44]Introduction to criminal investigation, p.96.A pure version statement needs to be the witness's best,uninterrupted narration of the events, as they recall it. As the witness recounts their best memory of the event,the investigator must resist the temptation to intervene and ask clarifying questions on the points being revealed.Clarifying questions like the question used to start an interview can be leading and can influence the witness'statement.

[45]ከላይ የተጠቀሰው፣ ገ.97.it sometimes happens that a witness or a reporting victim will turn out to be the perpetrator ofa crime. In these cases, allowing the person to provide their full uninterrupted statement can produce incriminatingindicators or even evidence of involvement. There is a tendency for criminals who fabricate their report of acrime to make sure they are adding information in their statement that helps eliminates them as a suspect. Thiscan include unsolicited alibis for their whereabouts and their activities at the time of the reported event. When awitness supplies this type of information without being prompted, it can be an indicator of personal involvementin the criminal event. Any such voluntary explanations of personal activities should be recorded carefully andclosely scrutinized to confirm the validity of facts. Follow up questions to unsolicited explanations should includeseeking the names of independent witnesses who might be able to corroborate the witnesses account.

የመናገር ፍላጎት እንዳይኖረው ሊያደርግ ስለሚችል ከዚህ አይነት የምስክሩን ሀሳብ ከሚሰርቁ ተግባራት መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በጣም ጥሩ አዳማጭ መሆን አስፈላጊ ነው፡፡

4. በቀጣይነት ምስክሩ ያለምንም ገደብ በነጻነት የተናገራቸውን በጽሁፍ የመመዝገብ ስራ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ጊዜ መርማሪው በማስታወሻ ይዞአቸው የነበሩትን ግልጽ ያልሆኑለትን ጥያቄዎች እያነሳ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምስክሩ የሚሰጣቸውን መልሶች በምስክሩ ቃል ውስጥ ያካትታል፡፡ምስክርነቱ ቅደም ተከተሉን ተከትሎ ለአንባቢ ሂደቱን በቀላሉ ለመገንዘብ በሚያስችል መልኩ መጻፍ ተገቢ ነው፡፡ ይህ የምስክርነቱን ቃል የሚይዘው ሰነድ የምስክሮችን ቃል ለመቀበል በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ሆኖ የተመሰከረበትን ጉዳይ፣ ቀን፣ ሰአት፣ የምስክሩ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ የአባትና የእናት ስም፣ የስራው አይነትና የሚሰራበት ቦታን የሚገልጽ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ መርማሪው መሪ ጥያቄዎችን (ለምሳሌ ሁለቱ ሰዎች ሲነጋገሩ ብታይም፣ ያወሩትን መቼ አልሰማህም አይደል? የሚመስል ጥያቄ) ከማንሳት መቆጠብ፡፡[46]ከዚህ ይልቅ እስቲ የምታውቀውን ንገረኝ ብሎ መጠየቅ ነው የሚመረጠው፡፡ ተራ ሰው የሆነ የማይገባውን ቴክኒካል የሆኑ የፖሊስ ቃላቶችን ከመጠቀም መቆጠብ፣ ጥያቄዎችን ሳይደራርቡ አንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ ብቻ መጠየቅ ይገባል፡፡
5. የመጨረሻው ወይም አራተኛው ደረጃ ምስክርነቱ የሚጠናቀቅበት ነው፡፡ መርማሪው የመዘገበውን የምስክሩን ቃል ለምስክሩ ያነብለታል(የሚጨምረው የሚያስተካክለው ካለ እድል ይሰጠዋል)፡፡ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ምስክሩ እንዲፈርም ያደርጋል፡፡ በምርመራው ላይ የተገኘው ወይም የተገኙት መርማሪዎችም በእያንዳንዱ ገጽ ላይ እንዲፈርሙበት ይደረጋል፡፡
6. ምስክሩን ስታሰናብተውም ምንም የምትፈልገው መረጃ ባታገኝም እንኳ ማንነትህን በመግለጽ ወይም ቢዝነስ ካርድህን በመስጠት መረጃ ሲኖረው ሊያገኝህ እንደሚችል ንገረው፡፡
7. በመቀጠልም በምርመራ መዝገቡ የእለት ሁኔታ መዝገብ ላይ በአጭሩ የተሰጠው ምስክርነት አጭር መግለጫን መጻፍ ይገባል፡፡ ይህም በመጨረሻ የምርመራ ራፖር ሲዘጋጅ የሚጠቅም ይሆናል፡፡ በዚህ አጭር መግለጫ ላይ መርማሪው ስለምስክሩ ያለውን አስተያየት (የሚታመን ወይም የማይታመን ስለመሆኑ) ሊያካትት ይችላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምስክሩ የቀረቡ

[46]Introduction to criminal investigation, p. 96.Like the threat of conformity being induced by a dominant witness, a witness can also be influenced by leading questions asked by an investigator. Some witnesses are so eager to assist in solving the crime that they will attempt to guess the answer to a leading question instead of admitting that they do not know the answer. The caution here is to avoid asking leading questions. Leading questions are questions that a witness might be able to infer theanswer by the nature of the wording.

ሌሎች ማስረጃዎች(ሰነዶች፣ ኤግዚቢቶች ሌሎች ምስክሮች ወዘተ) ካሉም እነዚህ ሊመዘገቡ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የምስክሮችን ማንነት እና የሰጡትን ምስክርነት በምስጢር መጠበቅ(ማለትም በቀጥታ በምርመራው ላይ ከሚሳተፉት መርማሪዎች በስተቀር ለሌሎች መርማሪዎችም ቢሆን ከመናገር በምስጢር መጠበቅ) በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.9. ንብረት ማሳገድ፣ማስከበርና ማስተዳደር

የሙስና ወንጀል ዋና አላማና ግብ የማይገባ ጥቅም ማግኘት ነው፡፡ ስለሆነም የሙስና ወንጀልን ለመቆጣጠር አንዱና ዋነኛው መፍትሄ በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረትን ሙሰኞች እንዳይጠቀሙበት ማድረግ ወይም መውረስ ነው፡፡ የአለምአቀፍ የጸረሙስና ስምምነቶች ሁሉም ፈራሚ መንግስታት በሙስና የተገኘ ንብረት ወይም ተመጣጣኝ ሀብት የሚወረስበትን አሰራር እንዲደነግጉ ይጠይቃል፡፡[47]

በሙስና ወንጀል ምርመራ የተጀመረባቸው ተጠርጣሪዎች ይፈጽማሉ ተብሎ ከሚገመተው ተግባር አንዱ በሙስና ያገኙትን ንብረት እንዳይወረስባቸው ደብዛው እንዲጠፋ ማሸሽ ወይም ማዛወር ነው፡፡ ይህንን ለመከላከልም በሙስና ወንጀል ምክንያት ተገኝተዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ንብረቶች ስለሚታገዱበትና ታግደው በሚቆዩበት ጊዜ ንብረቱ እንዳይጠፋና እንዳይባክን ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህግ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ እንደተደነገገው ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ ንብረት ማገድ በሁለት መልኩ ሊፈጸም ይችላል፡፡ እነርሱም(1) በሙስና ወንጀል የተገኘ ነው ተብሎ በሚገመት ንብረት ላይ የሚሰጥ የእግድ ትእዛዝ እና (2) በሙስና ወንጀል የተገኘ ባይሆንም በተጠርጣሪው ወይም ከተጠርጣሪው ጋር የቤተሰብ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ስም ያሉ ንብረቶች ላይ የሚሰጥ የእግድ ትእዛዝ ናቸው፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህግ አንቀጽ2(2) በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት ማለት በተከሳሽ ባለቤትነት ወይም ይዞታ ስር የሚገኝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሲሆን ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ከተከሳሹ <u>በስጦታ</u>

[47]OECD, INVESTIGATION AND PROSECUTION OF CORRUPTION OFFENCES: MATERIALS FOR THE TRAINING COURSE 2012፣ ገ.11

**<u>የተሰጠ በአደራ የተቀመጠ እና የተሸሸገ</u>** ማናቸውንም የወንጀሉ ፍሬ የሆነ ንብረትን ወይም ገንዘብን ይጨምራል፡፡

በተሻሻለው የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ አዋጅ አንቀጽ 8(1) ፍርድ ቤት በወንጀል የተገኘ ማንኛውም ንብረት እና በወንጀል የተገኘው ንብረት ያፈራውን ንብረት ለማገድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ 8(4) እግድ ትእዛዙ በፍርድ ቤት እስከሚሰጥ ድረስ አግባብ ያለው አካል ንብረቱ እንደሚባክን ሲያምንበት ለ48 ሰአት የሚጸና ጊዜያዊ የእግድ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

እግድ ትእዛዝ ማለትም በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህግ አንቀጽ 2(4) እንደተደነገገው ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በንብረቱ ላይ ያለውን መብት እንዳይጠቀምበት የሚከለክል ትእዛዝ ሲሆን በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍን የመጠቀም መብት መስጠትንና ማስወገድን የሚከለክል ነው፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ አንቀጽ 9 ሌሎች ንብረቶች ስለሚታገዱበት ሁኔታ በሚለው ስር ንብረቱ በሙስና የተገኘ ለመሆኑ መረጃ ባይቀርብም ምርመራ በተጀመረበት ወይም ክስ በቀረበበት የሙስና ወንጀል ተከሳሽ ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ለመኖሩ በቃለመሀላ ሲረጋገጥ በወንጀሉ ተገኘ ከተባለው የማይገባ ጥቅም ወይም ደረሰ ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በተከሳሽ፣ በትዳር ጓደኛ፣ ወይም ከ18 አመት በታች በሆነ ልጅ ስም በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም በእነዚሁ ሰዎች ስም ያለ ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ ወይም እንዳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ በመርማሪ ወይም በአቃቤ ህግ አቤቱታ ሲቀርብ ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሁንና የታገደው ንብረት በባንክ ተቀምጦ ከሚገኘው ገንዘብ ወይም ንብረት ከሆኑት በስተቀር በሌሎች ንብረቶች ላይ የሚሰጥ ትእዛዝ ተጠርጣሪው ወይም ቤተሰቦቹ በንብረቱ የመጠቀም መብታቸውን አይከለክልም፡፡

ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የመጠቀም መብቱ ባልተከለከለው ንብረት ላይ ንብረቱ ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ ማለትም ወደፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢወሰንበትና ተመጣጣኝ ንብረት ወይም ገንዘብ እንዲከፍል ቢወሰንበት ይህንን ላለመክፈል በማሰብ በንብረቱ ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ እየተጠቀመ መሆኑ ከተገመተ መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ ንብረቱን ከጉዳት ለመከላከል የሚጠቅም ትእዛዝ እንዲሰጥለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ተገቢ የሆነውን ውሳኔ ይሰጣል(አንቀጽ 9(3)፡፡ ተገቢ የሆነው ትእዛዝ ምን ሊሆን እንደሚችል በግልጽ

ባይቀመጥም ምናልባት ለተጠርጣሪው ማስጠንቀቂያ መስጠት ወይም በንብረት አስተዳዳሪ ስር ሆኖ እንዲተዳደር ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህግ አንቀጽ 8 እንደተደነገገው ንብረት ሊታገድ የሚችለው በመርማሪው ወይም አቃቤ ህግ በቃለመሀላ የተደገፈ አቤቱታ ሲቀርብ ነው፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህግ በአንቀጽ 11 እንደተደነገገው በቃለመሀላ ተደግፎ የሚቀርበው የአቤቱታው ማመልከቻ በውስጡ የወንጀሉን ፍሬነገርና በየደረጃው የተወሰዱትን እርምጃዎች፣ ክስ ያልተመሰረተ ከሆነ ጉዳዩ የሚገኝበትን ደረጃ፣ የሚታገደው ንብረት ወይም ገንዘብ በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት መሆኑን፣ ወይም ተፈጽሟል በተባለውና ምርመራ በተጀመረበት የሙስና ወንጀል አማካይነት ተጠርጣሪው ያገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳትን በሚመለከት አሳማኝ ምክንያቶች፣ የንብረቶቹን ዝርዝርና አድራሻ የያዘ መሆን እንደሚኖርበት ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

ንብረት እንዲታገድ የሚደረግበት ጊዜ በሙስና ወንጀል ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ንብረት የማስከበር ሂደት ቸኩሎ ማድረግም ሆነ ዘግይቶ ማድረግ የራሱ ጉዳትም ሊኖረው ይችላል፡፡ ቸኩሎ ንብረት እንዲታገድ ቢደረግ ተጠርጣሪው ምርመራ እንደተጀመረበት ነቅቶ ሌሎች ንብረቶችን እንዲያሸሽ ሊያደርገው እንደሚችል ሁሉ ዘግይቶ ንብረት እንዲታገድ ማድረግም ተጠርጣሪው ቀደም ብሎ አውቆ ሁሉንም ንብረት በማሸሽ ጨርሶውኑ የሚታገድ ንብረት እንዳይኖርም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠርጣሪው ምርመራ እንደተጀመረበት ካላወቀ ወይም አያውቅም ተብሎ ከተገመተ፣ ንብረቱን በማሳገድ ተጠርጣሪን ከማሳወቅ ይልቅ ንብረቱ እንዳይሸሽ ክትትል እየተደረገ ሌሎች ያልታወቁ ንብረቶችን እና ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ይመከራል፡፡ [48]

ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በሙስና የተገኘ ስለመሆኑ ማስረጃ የሌለውን ተመጣጣኝ ንብረት እንዲታገድ ሲደረግ የተገኘውን ጥቅምና የደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ ተመጣጣኝ ከሆነው በላይ ንብረት እንዲታገድ ማድረግ በራሱ አላግባብ የንብረት መብትን መጉዳት ሰብአዊ መብትን መጉዳት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር መርማሪዎች ንብረት እንዲታገድ ሲጠይቁ ከተመጣጣኝ በላይ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለባቸው፡፡

[48] APEC_investigation and prosecution of corruption,p.124

በመሰረቱ የህጉ ሀሳብ ግልጽ ነው፡፡ ሊታገድ የሚገባው የንብረት መጠን ከተገኘው ጥቅም ወይም ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ መጠኑን ገምተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ መጠኑን ገምተው ያላቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ መጠኑ ተገልጾ እንዲቀርብ ማዘዝ ይህንን ማድረግ ካልቻሉ ውድቅ ማድረግ ይገባዋል፡፡

የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ አንቀጽ 12 የእግድ ትእዛዝ እንደተሰጠ ለተከሳሹ እና በእግድ ትእዛዙ ስማቸው ለተጠቀሰው ትእዛዙን እንዲያውቁት በመርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ ሊደርሳቸው እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ከትእዛዙ ጋርም በቃለመሀላ የቀረበው አቤቱታ ግልባጭ እንዲደርሳቸው ያስገድዳል፡፡አላማውም የእግድ ትእዛዙ የደረሳቸው ባለጉዳዮች ትእዛዙ ላይ ቅሬታ ካላቸው እንዲያነሱ ለማድረግ ነው፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ አንቀጽ 16- እንደተደነገገውም እግድ በተሰጠው ንብረት ላይ ትእዛዙ የደረሰው ማናቸውም ሰው እግዱ እንዲነሳ ማመልከት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ባለጉዳዮች በተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ላይ ከተገኘው ጥቅም ወይም ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መጠን ተብሎ የታገደው ንብረት (1) በሙስና ተገኘ ከተባለው በቃለመሀላ አቤቱታው ላይ ከተመለከተው ጥቅም ወይም ጉዳት መጠን በላይ የሚሆን ግምት ያለው ንብረት ላይ የተጣለ እግድ እንዲቀነስልን ብለው ለማመልከት ይችላሉ ወይም (2) በእግድ ትእዛዙ ላይ የተመለከተው ተጠርጣሪ ወይም ቤተሰቦች ንብረት ያልሆነ ከሆነ እግዱ እንዲነሳ በማለት አቤቱታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን ከተቀበለው መርማሪው ወይም አቃቤ ህግ ምላሽ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም እግዱ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ፣ በከፊል እንዲነሳ ወይም የሰጠውን እግድ ሊያጸናው ይችላል፡፡

**የማይታገዱ ንብረቶች**

የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ በአንቀጽ 10 ለተከሳሽ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ የማይታገዱ ንብረቶችን ዘርዝሮአል፡፡ እነርሱም፣

1. ለተከሳሹ እና ለቤተሰቡ የእለት አገልግሎት የሚጠቅሙ ልብሶች፣ የምግብ ማብሰያ የሆኑ ቁሳቁሶች አልጋ የአልጋ ልብሶች፣
2. ለራሱና ለቤተሰቡ የእለት ኑሮ ጠቃሚ የሚሆን ከሶስት ወር ያልበለጠ ስንቅ፣

3. የተከሳሹንና የቤተሰቡን የእለት ኑሮ ለማሟላት የሚያገለግሉ ቀላል መሳሪያዎች (የሽማኔ እቃ፣ የአናጢ እቃ ወዘተ..)
4. ተከሳሹ እና ቤተሰቡ የሚተዳደሩበት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆንና የሚተዳደሩት ከታገደው ንብረት ከሚገኝ ገቢ ከሆነ መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ለተከሳሹና ለቤተሰቡ ፍርድ ቤቱ በቂ ነው ብሎ የሚገምተውን ያህል ገቢ፣

በተሻሻለው የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ አንቀጽ 8 በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ የመጠቀም መብት ቢከለከልም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ፍርድ ቤቱ እንዲታገድ ከተደረገው ከዚህ ገንዘብ ወይም ንብረት ውስጥ ተጠርጣሪው ሊጠቀምበት የሚገባ መጠን በመወሰን እንዲያገኙ እና እንዲጠቀሙበት የሚደረግበት ሁኔታ ሊኖርእንደሚችል ተመልክቷል፡፡

**ንብረቱን እንዳይበላሽ ስለመጠበቅና ስለማስተዳደር**

ንብረቱ ከታገደበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ ተሰምቶ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ንብረቱ እንዳይባክንና እንዳይበላሽ መደረግ አለበት፡፡ በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ ንብረቱ እንዳይበላሽና እንዳይባክን ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ተደንግገዋል፡፡ እነሱም ንብረቱን አሽጎ ማስቀመጥ(አንቀጽ 22)፣ ታሽጎ በመቀመጡ የሚበላሽ ከሆነ በሀራጅ ተሽጦ የተገኘው ገንዘብ በባንክ እንዲቀመጥ ማድረግ(አንቀጽ 25(3) ወይም ንብረቱን የሚያስተዳደር ንብረት አስተዳዳሪ መሾም ነው(አንቀጽ 13)፡፡

እግድ የተሰጠበትን ንብረት አሽጎ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በመርማሪው/ዐቃቤ ህጉ አመልካችነት ንብረቱ ሊታሸግ ይችላል፡፡ አፈፃፀሙም ከአንቀፅ 22-28 መሰረት ይመራል፡፡ ታሽጎ በመቀመጡ የሚበላሽ ከሆነ በሀራጅ ተሽጦ የተገኘው ገንዘብ በባንክ እንዲቀመጥ ይደረጋል(አንቀጽ 25(3)፡፡

ይሁንና በፍርድ ቤት የታገደው ንብረት የንግድ ድርጅት (ሆቴል፣ ፋብሪካ፣ ህንጻ …) ወዘተ ከሆነ የንግድ እንቅስቃሴው ሳይቆም እንዲቀጥል ፍርድ ቤቱ ንብረት አስተዳዳሪ ሊሾም ይችላል፡፡

በሌሎች አገሮች (ለምሳሌ በአሜሪካ፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ) ንብረት ለማስተዳደር በመንግስት የተቋቋሙ ንብረት አስተዳዳሪዎች ሲኖሩ እነዚህ አስተዳዳሪዎች ንብረቶቹን ገቢ በሚያስገኝ ስራ ላይ በማሰማራት ገቢ የሚያስገኙ ሲሆኑ በዚህ መልኩ የሚገኘው ገቢም ሆነ ንብረቱ ሲወረስ የሚገኘው ገቢ በቀጣይነት ንብረት ሲታገድ ለማስተዳደር ስራ እንዲውል ይደረጋል፡፡[49] በኢትዮጵያ

[49] APEC_investigation and prosecution of corruption,p.135-6

ህግ መሰረት ግን ግራ ቀኙ ንብረት አስተዳዳሪ እንዲሆን ከሚያቀርቡት እጩ መካከል ፍርድ ቤት መርጦ የሚሾመው ነው እንጂ ንብረት ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ተቋም የለም፡ :[50] ፍርድ ቤት የሚሾመው ንብረት ጠባቂ የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ንብረት ጠባቂነት ለመሾም መልካም ስነምግባርና ችሎታ ያለው እንዲሁም ከተከሳሽ ጋር ዝምድና ወይም የጥቅም ግንኙነት የሌለው መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚሾመው ንብረት ጠባቂ የህግ ሰውነት ያለው ከሆነ ያለፉት ሶስት አመታት የሂሳብ አያያዙ ንጹህ መሆኑንና የጥቅም ግጭት አለመኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል(አንቀፅ17(5)፡፡

ፍርድ ቤቱ ለንብረት ጠባቂው ከማስተዳደር ስልጣን ጋር የተያያዙ፡ የመከራከር፣ ትርፍና ኪራይ መሰብሰብ፣ የሰበሰበውን ጥቅም ላይ የማዋል ስልጣን ወዘተ.. ሊሰጠው ይችላል (አንቀፅ17 (2)፡፡ ንብረት ጠባቂው ለስራው አበል ይከፈለዋል(አንቀፅ 18)፡፡

ህጉ ንብረት አስተዳዳሪው ንብረቱን በማስተዳደር ስለሚጠበቅበት ግዴታ በአዎንታዊ መልኩ የገለጸው ባይኖርም፣ ነገር ግን በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ አንቀጽ 20 እንደተመለከተው ንብረት ጠባቂው ዋስትና የማቅረብ፣ የሂሳብ መግለጫ የማቅረብ፣ በራሱ ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ በንብረቱ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ ከሆነ ባደረሰው ጉዳት ልክ ካሳ እንዲከፍል እንዲደረግ ይደነግጋል፡፡

ንብረት የሚታገደው ወንጀል ስለመፈጸሙ ከተረጋገጠ በኋላ ሳይሆን ወንጀል ተፈጽሞአል የሚል ጥርጣሬ በመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም የተጠርጣሪውን ንብረት ላይ እግድ እንዲሰጥ ማድረግ በንብረት መብቱ ላይ ገደብ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አላግባብ በግለሰብ መብት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊደረግ ያስፈልጋል፡፡ ንብረት ማስተዳደር ከባድና ወጪ የሚያስወጣ ነው፡፡ ምናልባትም ንብረቱን ለማስተዳደር የሚወጣው ወጪ ንብረቱ በመወረሱ ሊገኝ ከሚችለው ጥቅም ሊበልጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም ጥቅምና ጉዳቱን በማመዛዘን ንብረቱ እንዲታገድ ሳይደረግ በተለይም ንብረት አስተዳዳሪ ሳይሾም ተከሳሹ እያስተዳደረው እንዲቆይ ማድረግ ይመረጣል፡፡ አስፈላጊ ከሆነም ተጠርጣሪው ስለንብረት አስተዳደሩ በየጊዜው የፋይናንሻል እና የስራ ክንውን ሪፖርት እንዲያቀርብ በማድረግ ንብረቱ ያለበትን ሁኔታ መቆጣጠር ይቻላል፡፡ እንዲህ አይነት አማራጭ ቢወሰድ ባለንብረቱ በወንጀሉ ጥፋተኛ አይደለም ተብሎ ነጻ የሚሆን ቢሆን ሊደርስ የሚችለውን

[50]ንብረት አስተዳዳሪውን ለማሾም አቤቱታው በመርማሪው፣ በአቃቤ ህጉ ወይም በተጠርጣሪው ሊቀርብ ይችላል (አንቀጽ 17(6)፡፡

የንብረት ብክነት ለመቀነስ ያስችላል፣ መንግስትም ላላስፈላጊ ክስና ወጪ እንዳይዳረግ ያደርጋል። [51]

## 2.10. ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ዋስትና፣ጊዜቀጠሮ እና የተጠርጣሪን ቃል ስለመቀበል

የወንጀል ምርመራ ስራ አንዱና ዋናው አካል በወንጀሉ ተሳታፊ ነው የተባለውን ተጠርጣሪ መለየት፣ መያዝ፣ የተጠርጣሪውን ቃል መቀበል እና ይህ ተጠርጣሪ ክስ የሚመሰረትበት ከሆነ ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ማድረግ ወይም ማረጋገጥ ነው። በዚህ ክፍል ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ ቃሉን ለመቀበልም ሆነ ለፍርድ ቤት ለማቅረብ የወንጀል መርማሪ በህግ ስላሉት ስልጣንና ሊያደርጋቸው ስለሚገቡ ህጋዊ ግዴታዎችና ጥንቃቄዎች እንመለከታለን።

### ተጠርጣሪን ስለመያዝ

መያዝ ለሚለው ቃል ትርጉም በስነስርአት ህጉ አይገኝም። ብላክስ ሎው መዝገበቃላት መያዝን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል። መያዝ ህጋዊ ስልጣን ባለው አካል በተለይም የወንጀል ክስን በተመለከተ ህጉን ለማስከበር ሲባል በተለይም አንድን ሰው ወደፍርድ ቤት ለማቅረብ በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም መጠበቅ ነው።[52]

በአንድ በኩል ህግና ስርአትን ለማስከበርና ወንጀል አድራጊ ከተጠያቂነት እንዳያመልጥ ለማድረግ፣ በሌላ በኩል የሰዎችን ሰብአዊ መብቶች በማክበርና በመጠበቅ መካከል አንዱን ከሌላው ለመምረጥ የሚያስቸግር ይሆናል። በምርመራ ሂደት ለተወሰነ ጊዜ ተጠርጣሪ ሆኖ በመያዝ የሚያስከትለው የመብት መገደብ እያንዳንዱ ዜጋ የጋራ የሆነው የነዋሪዎችን ሰብአዊ መብት ለማስከበር መሰረት ለሆነው የህግ የበላይነት ሲል ሊከፍለው የሚገባ ዋጋ ነው። ማንም ሰው በወንጀል ሊጠረጠር ይችላል። ስለሆነም ፖሊስ ተጠርጣሪ ነህ ብሎ ሊይዘው ሲመጣ ይህንን ተቀብሎ ህጉን አክብሮ መታዘዝ የሚገባ ሲሆን፣ በወንጀሉ አላግባብ ተጠርጥሮም ከሆነ በተቻለ መጠን አስፈላጊውን መረጃ ለፖሊሱ በመስጠት የሚከፍለውን ዋጋ ሊቀንስ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባዋል።ይሁንና የሚከፈለው ዋጋ እንዲቀንስ ከማድረግ አንጻር ትልቁ እና ዋናውን ሀላፊነት የተሸከመው የህግ አስከባሪው ፖሊስ ነው።

[51] APEC_investigation and prosecution of corruption p. 136
[52] blacks law dictionary, eighth edition, 2008

**በወንጀል ያለመከሰስ መብት እንዴት ይነሳል?**

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 3 መሰረት ያለመከሰስ መብትን ስለማንሳት በሌሎች ህጎች የተደነገገውም ቢኖርም የመመርመር እና የመክሰስ ስልጣን የተሰጠው አካል በተሠጠው ጉዳዮች ዙሪያ ያለመከሰስ መብት የማንነት ጥያቄን እንደሁኔታው ጉዳዩን ለሚመለከተው የህዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክርቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**የጊዜ ቀጠሮና የዋስትና መብት**

**በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 28 ወይም በጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ አ ጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አ አንቀጽ 4(2) ተጠርጣሪ በዋስትና ሊለቀቅ ስለሚችልበት ሁኔታ**

በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ ቁጥር 28 እና በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አ አንቀጽ 4(2) በተመሳሳይ ቃላትና ሀረጎች ፖሊስ የተያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ ሊለቅ እንደሚችል ይደነግጋሉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ፖሊስ የተያዘውን ሰው በዋስትና መልቀቅ የሚችለው፣(1) የተሰራው ወይም አቤት የተባለበት ወንጀል በጽኑ እስራት ወይም ይህንኑ በመሰል ተለዋጭ ቅጣት የማያስቀጣ ሲሆን ወይም (2) ወንጀል የተሰራ ለመሆኑ ወይም እንዲቀርብ የተጠራው ወይም የተያዘው ተከሳሽ አቤት የተባለበትን ወንጀል መስራቱ የሚያጠራጥር ሲሆን ነው ይላል፡፡

ጽኑ እስራት ማለት ከአንድ አመት እስከ ሃያ አምስት አመት እስራት ሊያስቀጣ የሚችል ማለት ሲሆን (የወንጀል ህግ አንቀጽ 108(1) ፣ ወንጀሉ በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ማወቅ የሚቻለው ወንጀሉ በተደነገገበት ድንጋጌ ውስጥ በጽኑ እስራት ያስቀጣል የሚል ሀረግ ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡

ስለሆነም ፖሊስ ተጠርጣሪን ከመያዙ በፊት የትኛውን የወንጀል ድንጋጌ እንደጣሰ ማወቅና መወሰን የሚገባው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ተጠርጣሪን ከመያዝ በፊት በፖሊሱ ሊጣራና ሊታወቅ የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት ማለትም አስፈላጊውን ማጣራትና ዝግጅት ፖሊስ ማድረግ እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም ሁኔታዎች በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ ቁ. 28 መሰረት የተሟሉ ከሆነ ሰዎችን ለአንድ ደቂቃም ቢሆን እንኳን በእስር ማቆየት ሊተካ የማይችል ጉዳት (ቅጣት) ስለሆነ እንደፖሊስ ሀላፊነት በተሞላው መልኩ ዋስትናቸውን ማክበር ይበረታታል፡፡

በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው የሚቀርብበት ፍርድ ቤትን በተመለከተ የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አ እንደተሻሻለው በአንቀጽ 7(5)- ተጠርጣሪውን ለማቅረብ የሙስና ወንጀልን ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዲታዩ መደረጉ የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን አግባብ ያለው አካል ካመነበት እንደሁኔታው በአቅራቢያው በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ስልጣን ይሰጣል፡፡ ስለሆነም በማንኛውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል ማለት ነው፡፡

መርማሪ ወይም ፖሊስ በህግ በተደነገገው መሰረት በ48 ሰአት ውስጥ የተያዘውን ሰው አቅራቢያው ላለው ፍርድ ቤት ካላቀረበው፣ ድርጊቱ ህገመንግስትን እና የስነስርአት ህጉን የመጣስ ድርጊት ስለሚሆን በህገመንግስቱ አንቀጽ 19(4) እንደተደነገገው የተያዘው የአካል ነጻነቱ እንዲከበር ለፍርድ ቤት ጥያቄ የማቅረብ የማይጣስ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡

አካልን ነጻ ስለማውጣት የሚመራበትን ስርአት የሚደነግገው የፍትሀብሄር ስነስርአት ህግ ከቁ. 177-179 ተደንግጎአል፡፡ በፍትሀብሄር ስነስርአት ህግ ቁ.177 መሰረት ከህግ አግባብ ውጪ የተያዘው ሰው እሱ ካልቻለ ደግሞ ማንኛውም ሰው በቃለ መሀላ በተደገፈ አቤቱታ የተያዘውን ሰው ስም፣ የአስገዳጁን ወይም የያዡን ሰው ስም ተገዶ የተያዘበትን ስፍራ ይህንኑም የሚያረጋግጡ ሰዎች እንዳሉ የምስክሮቹን ስምና አድራሻ ዘርዝሮ ሲያቀርብ፣ ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ ቁ. 178 እና 179 በተደነገገው መሰረት አመልካቹን የያዘውን የመንግስት ሰራተኛ ወይም ሀላፊ የተያዘውን ሰው ይዞ እንዲቀርብና ይህንንም ሰው የማይለቅበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ቀነቀጠሮ ወስኖ በመጥሪያ እንዲጠራ ያደርጋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው ከህግ አግባብ ውጭ መሆኑን ሲረዳ የተያዘው ሰው ወዲያውኑ እንዲለቀቅ ወይም አቤቱታው የሚያጠራጥር መስሎ ከታየው በዋስትና እንዲለቀቅ ትእዛዝ እንደሚሰጥ ይደነግጋል፡፡

የተያዘው ሰው ለፍርድ ቤት ከቀረበና የያዘው የመንግስት ሰራተኛ(ፖሊስ) የተያዘበትን እና በ48 ሰአት ውስጥ ማቅረብ ያልቻለበትን ምክንያት ካስረዳ በህገመንግስቱ በአንቀጽ 18(4) እንደተደነገገው ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ስር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ፍርድ ቤት የተያዘው ሰውን በተመለከተ በፖሊስ የቀረበውን ምክንያት ካልተቀበለው እና የተያዘው ሰው እንዲለቀቅ ከወሰነ የያዘው የመንግስት ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን ከህግ ውጭ እንዲያዝ  አድርጎአል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በወንጀል ህግ 423 በህግ ከተመለከተው ውጭ ወይም ህጋዊ ስርአትና ጥንቃቄ ሳይከተል ሌላውን ሰው በመያዝ፣ በማሰር ወይም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ነጻነቱን ያሳጣው እንደሆነ ከአስር አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና በመቀጮ እንደሚቀጣ በሚደነግገው መሰረት በወንጀል ክስ ተመስርቶበት ያስቀጣዋል ማለት ነው፡፡

**በፍርድ ቤት በዋስትና የመለቀቅ መብት**

የኢፌዲሪ ህገመንግስት በአንቀጽ 19(6) የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው፣ ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የዋስትና ጥያቄውን ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ እንደተሻሻለው አንቀጽ 4(1) በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተያዘ ሰው የተከሰሰበት ወይም የተጠረጠረበት ወንጀል  ከአስር አመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ ወይም የተከሰሰው ከአንድ በላይ ወንጀል ከሆነና እነዚህ የተጠረጠረባቸው ወይም የተከሰሰባቸው ተደራራቢ የወንጀል ድንጋጌዎች የሚያስቀጡት ከአራት አመት በላይ ሆኖ እስከ አስር አመት የሚያስቀጡ ከሆነ እና እነዚህ ሲደመሩ ከአስር አመት በላይ የሚያስቀጡ ከሆነ በዋስትና መለቀቅ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ ተደራራቢ በሆኑ ወንጀሎች ዋስትና የሚከለከለው የተደራራቢ ወንጀሎቹ መነሻ ቅጣት ከአራት አመት በላይ ከሆነ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ የሙስና ወንጀሎች የቅጣት መድረሻቸው ከአስር አመት ያልበለጡትን ስንመለከታቸው ሁሉም መነሻቸው ከአራት አመት በታች ነው፡፡

በህግ በዋስትና እንዳይለቀቁ ከተከለከሉት ውጭ የዋስትና መብት በፍርድ ቤት ሊከለከልባቸው የሚችሉት በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 4(4) በተደነገገው መሰረት  ሀ/ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ በዋስትና ቢለቀቅ ይጠፋል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ወይም ለ/ ማስረጃዎችን ያጠፋል ወይም ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ተብሎ ሲገመት እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 4(4) መሰረት ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የዋስትና መብቱ እንዳይፈቀድ የሚያደርጉ እነዚህ ሁኔታዎች መኖራቸውን የማስረዳት ሀላፊነት ያለበት

መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ ነው፡፡ በድንጋጌው መሰረት ዋስትናን ለመከልከል በድንጋጌው የሰፈሩት ግምቶችን ፍርድ ቤቱ እንዲኖረው በመርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ ሊቀርቡ የሚገባቸው አመላካች ማስረጃዎች ወይም ክርክሮች መኖር እንዳለባቸው ያመለክታል እንጂ መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪ ሊጠፋ፣ ወይም ማስረጃ ሊያጠፋ ወይም ሌላ ወንጀል ሊሰራ ይችላል ብዬ እገምታለሁ ስላለ ብቻ ዋስትና ይከለከላል አይልም፡፡ የህጉ ሀሳብ እንዲህ  ቢሆን ኖሮ አንቀጹ አቀራረጹ ፖሊስ ማስረጃ ያጠፋል ወይም ይጠፋል አይለቀቅ ብሎ ካመለከተ ዋስትና ይከለከላል በሚል ሊቀረጽ ይገባው ነበር፡፡

ፖሊስ በዚህ አንቀጽ መሰረት ዋስትና እንዲከለከል የሚያቀርበው መቃወሚያ እንዲሁ ተጠርጣሪው በእስር እንዲቆይ በመፈለግ ሳይሆን በእርግጥም በቅንነት ላይ በተመሰረተ መልኩ እነዚህ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ምክንያታዊ ግምት ሊያሳድሩ የሚችሉ አመላካች ማስረጃዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/ሕ አንቀጽ 6 ዋስትና ከመከልከል በመለስ የሚሰጡ የጥንቃቄ እርምጃዎች ተደንግገዋል፡፡ እነርሱም ተከሳሽ(ሀ) ከተወሰነ ክልል ውጭ እንዳይንቀሳቀስ ወይም(ለ) ማስረጃ ሊያጠፋ በሚችልባቸው ቦታዎች እንዳይደርስ ወይም (ሐ) በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት እንዲያደርግ ወይም (መ) ወደውጭ አገር እንዳይወጣ የሚሰጡ የእግድ ትእዛዞች ናቸው፡፡

እነዚህ አይነት የእግድ ትእዛዞች ዋስትና ከመከልከል መለስተኛ የሆነ ገደብ የሚያደርጉ ስለሆነ ጥፋተኛ ተብሎ ለማይገመተው ተከሳሽ ሰብአዊ መብት አጠባበቅ ረገድ የተሻሉ እርምጃዎች ናቸው፡፡ ፖሊስ የሰዎችን ሰብአዊ መብት የማክበርና የማስከበር ሀላፊነት ስላለው በዋስትና መለቀቃቸው ስጋት የሚኖረው ከሆነ፣ እነዚህን ዋስትና ከመከልከል በመለስ የተቀመጡ የእግድ ትእዛዞች ስጋቱን ሊቀንሱ ወይም ሊከላከሉ የሚችሉ እስከሆነ ድረስ ጨርሶ ዋስትና እንዳይሰጣቸው ተቃውሞ ከማቅረብ እነዚህን ከግምት ባስገባ መልኩ እንዲንቀሳቀስ ይጠበቃል፡፡

**በዋስትና ጉዳይ ይግባኝ**

የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አ ቁጥር 434/97 እንደተሻሻለው በአንቀጽ 5 በዋስትና ጉዳይ ላይ ፖሊስ ወይም አቃቤ ህግም ይግባኝ ሊጠይቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሹ በዋስትና እንዲለቀቅ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ወይም የዋስትና መጠኑን በመቃውም ፖሊስ ወይም

አቃቤ ህግ ይግባኝ የጠየቀበት ከሆነ ጉዳዩ በይግባኝ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በዋስትና እንዲለቀቅ የተሰጠው ውሳኔ ሳይፈጸም እንደሚቆይም ይደነግጋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም ለይግባኝ ማቅረቢያ የሚበቃ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ዓ/ሕጉ ወይም መርማሪው በፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የጠየቀበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዋስትና ጥያቄው ላይ ውሣኔ ለሰጠው ፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚሁ ውሣኔው ላይ መርማሪው ወይም አቃቤ ህጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ባይወጣ ተጠርጣሪው ግዴታዎቹን እንዳሟላ ወዲያዉ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ማስፈር እንዳለበት በአንቀጽ 5/3/ ሥር ተመልክቷል፡፡

አቃቤ ህግ ይግባኝ ማለቱን የሚያሳይ ማስረጃ የሚያቀርበዉ ከይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሬጅስትራር ነዉ፡፡ ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እግድ ማምጣት  አይጠበቅም ማለት ነዉ፡፡ ይግባኙ ታይቶ ዉሳኔ እስኪሰጥ ድረስም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ታግዶ ይቆያል፡፡

**የተጠርጣሪን ቃል መቀበል**

አንዳንድ ጊዜ የምርመራ ስራውን ውጣ ውረዱን በመፍራት ወይም ማስረጃ አናገኝም በማለት በተጠርጣሪ የእምነት ቃል ላይ ለመመስረት ሲባል ተጠርጣሪ ቃሉን እንዲሰጥ የተለያየ ተጽእኖዎችን ማድረግ በመርማሪ ፖሊሶች ዘንድ ይታያል፡፡ ነገር ግን እንደመርማሪ ፖሊስ አንድ የወንጀል ድርጊትን ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረን ሰው ድርጊቱን መፈጸሙን ለማረጋገጥ ተጠርጣሪው በሚሰጠው የእምነት ቃል ላይ ጥገኛ መሆን አይገባም፡፡

ተጠርጣሪው በፍርድ ጥፋተኛ ነው ተብሎ እስከሚወሰንበት ጊዜ ድረስ ጥፋት እንዳላጠፋ ተደርጎ ስለሚቆጠር፣ ፖሊስ በተቻለ መጠን ማስረጃዎችን ከተጠርጣሪው የእምነት ቃል ውጭ በሌላ መንገድ ማሰባሰብ አለበት እንጂ ተጠርጣሪ እንዲያምን ማስገደድ ወይም ተጽእኖ ማድረግ ይህንን መሰረታዊ ሕገመንግስታዊ መርሆ ተቃርኖ መቆም፣ ስለሆነም ንጹሀን ሰዎች ያለጥፋታቸው ጥፋተኛ ነን ብለው እንደሚያምኑ በማድረግ የፍትህ አላማው ስቶ እውነተኛውን ወንጀል አድራጊ ለይቶ በማውጣት በመቅጣትና ህብረተሰቡን ከወንጀል በመጠበቅ ፋንታ፣ ንጹሀንን የሚጎዳ ስርአት ሆኖ ወንጀልን እንዲስፋፋ የማድረግ አደጋ አለው፡፡

ፖሊስ ማስረጃን የሚሰበስበው እውነተኛው ወንጀል አድራጊን ለይቶ በማውጣት እንዲቀጣ በማድረግ ህብረተሰቡን ከወንጀል መጠበቅ ነው እንጂ በዚያም ሆነ በዚህ ወንጀሉን አድርጌያለሁ የሚል ቃል ከተጠርጣሪው ማግኘት መሆን የለበትም፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠርጣሪ ያልፈጸመውን

ወንጀል ፈጽሜያለሁ በማለት በሚሰጠው ቃል የሚደርሰው ጉዳት ከፍ ያለ ነው፡፡ እነዚህም፣(1) ንጹህ ሰው ያለጥፋቱ እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡ (2) እውነተኛው ወንጀል አድራጊ ሳይቀጣ ያመልጣል፡፡ (3) ሕብረተሰቡ ከወንጀል አድራጊዎች ሳይጠበቅ በመቅረቱ በአጠቃላይ የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ በአጭሩ የወንጀል ህግ አላማና ግብ ሳይሳካ ይቀራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ የእምነት ቃል የተገኘው በማስገደድ ከሆነና ይህም በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ ማስረጃው ተቀባይነት ስለማያገኝ፣ የተለፋው ልፋት ጊዜና ገንዘብ ከንቱ ኪሳራ ይሆናል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ቃሉን በማስገደድ የተቀበለው ፖሊስም በወንጀል ህግ አንቀጽ 424 እንደተደነገገው በወንጀል ተጠያቂ ሆኖ የሚቀጣበት ይሆናል፡፡ ስለሆነም መርማሪ የተጠርጣሪን ቃል ሲቀበል አስፈላጊ ጥንቃቄዎችን ሊያደርግ ይገባል፡፡

ይህ ማለት ተጠርጣሪ በነጻ ህሊና፣ ያለምንም ፍርሀትና መገደድ ቃሉን ለመስጠት ከፈለገ ቃሉን መቀበል የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ተጠርጣሪ ያለመናገር መብት እንዳለው አውቆ ይሁንና ፈቅዶና ፈልጎ ቃሉን የሚሰጥ ከሆነ ሰብአዊ መብቱ ተከበረ እንጂ ተጣሰ አይባልም፡፡

ተጠርጣሪን የመጠየቅና የመመርመር ዋና አላማና ግብ የተጠርጣሪውን እምነት ቃል ለማግኘት ሳይሆን እውነቱን ለማውጣት ነው፡፡[53] በማስገደድ በማስፈራራት የተገኘ የእምነት ቃል እውነት መሆኑ ቀርቶ እውነቱን መደበቅ ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም በነጻነት ያለምንም ማስፈራራትና ተጽእኖ ቃሉን የሚሰጥ ከሆነ ከተጠርጣሪነት እራሱን የሚያወጣ እና ሌሎች የበለጠ ወንጀሉን የፈጸሙ ተብለው የሚገመቱ ሰዎችን የሚያጋልጥ ማስረጃ በመስጠት ወደእውነቱ ሊመራ ይችላል፡፡

የተያዘው ሰው ቃሉን እንዲሰጥ የሚደረግበት ምክንያቶች (1) ተጠርጣሪው ወንጀሉን ፈጽሞ ከሆነ መፈጸሙን እንዲያምን፣ (2) ወይም ወንጀሉ ውስጥ ተሳትፎ የሌለው ከሆነ ይህንን እውነት እንዳልሆነ ለማስረዳት እንዲችል፣ (3) በጉዳዩ ላይ እሱ የተረዳውን እና የሚያውቀውን እንዲያስረዳ፣ (4) ማስረጃዎችን ለተጠርጣሪው በማሳየት ተጠርጣሪው በማስረጃዎቹ ላይ ያለውን ምላሽ በመገምገም ተጠርጣሪው እየዋሸ ወይም እውነቱን እየተናገረ መሆኑን እንዲረዳ፣(5) መርማሪው ተጠርጣሪው ሊገልጻቸው ስላልፈለጋቸው ነገሮች የሚረዳበት ነው፡፡[54]

[53] Introduction to criminal investigation, In modern day policing, interviewing, questioning, and interrogation techniques are measured, objective, and ethical. They are aimed at the goal of discovering the truth; not just getting a confession to a crime, p. 122
[54]ከላይ የተጠቀሰው፣ .

አንድ ሰው የእምነት ቃል እንዲሰጥ የሚያደርጉት ምክንያቶች እራሱን ከህሊና ጸጸት ለመገላገል ወይም በመርማሪው እጅ ያለውን የማስረጃ ጥንካሬ በመረዳት ይህንን ማለፍ እንደማይችል ተረድቶ እጅ መስጠት ብቸኛ አማራጭ ነው ብሎ ወስኖ ሊሆን ይችላል፡፡ በወንጀሉ ከፍተኛ ተሳትፎ የሌላቸው ሰዎች ይህንን አነስተኛ ተሳትፎአቸውን በመግለጽ በቀላሉ ቅጣት ሊታለፉ እንደሚችሉ በመገመትም ዋናውን ወንጀል አድራጊ ለማጋለጥ ብለው የእምነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ተጠርጣሪው ሰው ቃሉን ሲሰጥ ማስገደድ ባይኖርበትም የሀሰት የእምነት ቃል የሚሰጥባቸው ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-

1. የተደራጀ ወንጀል(የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣኖች የተሳተፉበት ሲሆን) ዋናውን ወንጀል እና ወንጀለኞችን ለመደበቅና ተዳፍኖ እንዲቀር ለማድረግ ነገ ከእስር እንድትወጣ እናደርጋለን አንተ እኔ ነኝ የፈጸምኩት ብለህ የእምነት ቃል ስጥ ብለውት በገቡለት ቃል መሰረት ሊሆን ይችላል፡፡
2. ዘመዶቹን ወይም የቅርብ ወዳጆቹን ከእስርና መንገላታት ለመጠበቅ እኔ ልቸገር ልቀጣ ብለው ያልሰራውን ወንጀል ሰርቻለሁ ብሎ ቃሉን ሊሰጥ ይችላል፡፡ ወይም
3. የአእምሮ ችግር ያለበት ሆኖ ጀግና ለመባል ያላደረገውን አድርጌያለሁ ሊል ይችላል፡፡[55]

ስለሆነም የተጠርጣሪን ቃል አቀባበል ጊዜ መርማሪ ፖሊስ ቃል ሲቀበል እነዚህ ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ከግምት ባስገባ መልኩ መሆን አለበት፡፡

የተጠርጣሪን ቃል በመቀበል ጊዜ የኦዲዮ ወይም ቪዲዮ ሪከርዲንግ ከሁሉም የሚመረጥ ነው፡፡[56] ምክንያቱም ተጠርጣሪው እየተጠየቀበት ያለበትን ክፍል እና አጠቃላይ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ የሚጠየቅበት ክፍል በክፍሉ ለሚኖሩት ሰዎች በቂ መቀመጫና ጠረጴዛ፣ የሚመች ድምጽን የማይረብሽ ማድረግ፣ ከተጠርጣሪው ጀርባ ከመሆን ወይም ወዲያና ወዲህ እያሉ ከመንጎራደድ መቆጠብ ፍርሀት እንዳያድርበት ያደርጋል፡፡[57]ተጠርጣሪዋ ሴት ከሆነች ቢያንስ አንዲት ሴት እዚያው ክፍል አብራ እንድትኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተጠርጣሪው ከጠበቃው ጋር እንዲነጋገርም መፍቀድ ያስፈልጋል፡፡ በቃል መቀበሉ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ

[55]ከላይ የተጠቀሰው ገ.126፣128-129
[56]ከላይ የተጠቀሰው ገ.125
[57]ከላይ የተጠቀሰው

የእረፍት ጊዜም በተለይም ተጠርጣሪው ምቾት የማይሰማው መስሎ ከተሰማው ምክንያታዊ በሆነ መልኩ መፍቀድ ይገባል፡፡

በቃል አቀባበል ጊዜ መርማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ የቃል አቀባበል ሞዴል ‘PEACE’ model›[58] እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርቧል፡፡

1. P(Preparation) ሲሆን ቃል መቀበል ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ቅድመዝግጅት ማድረግ ማለት ነው፡፡ የተጠርጣሪውን ቃል ለመቀበል የተዘጋጀ መርማሪ በቅድሚያ የተጠርጣሪውን ማንነት፣ የወንጀል ሪከርድ ያለበት ስለመሆኑ፣ ቀድሞ በሌላ ጉዳይ በምርመራ ውስጥ ያለፈ ስለመሆኑ ማጣራት እንዲሁም እስካሁን የተሰባሰቡትን ማስረጃዎች በደንብ በዝርዝር አንብቦ መዘጋጀት፣ እንዲሁም የትኛው ወንጀል ስለመፈጸሙ ማስረጃ የሚፈለገውም የትኛውን ወንጀል ለማረጋገጥ እንደሆነ መዘጋጀት፣ ከዚህ ቀድሞ የተሰባሰበው ማስረጃ ክስ ለመመስረት ብቃት ያለው መሆኑን መወሰን፣ግልጽ የሆነ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች የያዘ ሊስት ማዘጋጀት፣ እንዲሁም ለምሳሌ ተጠርጣሪው ሊመልስ ፈቃደኛ ባይሆን ምን መደረግ እንዳለበት አማራጭ እቅድ የያዘ እንዲሆን ይመከራል፡፡ [59]
2. E (Engage) ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ራሱን ያዘጋጀ መርማሪ ከተጠርጣሪው ጋር ከተገናኘ በኋላ ራሱን ያስተዋውቃል፡፡ የቃል መቀበሉ አላማ ምን እንደሆነ ይነግረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ፣

2.1. ምን አይነት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ እንደተያዘ በሚገባውና በሚረዳው ቋንቋ በአጭሩ ይነግረዋል (ሕገመንግስት አንቀጽ 19(1)፡፡ (ተጠርጣሪው ለምን ተይዞ እንደሚቆይ ሳያውቅ በጭንቀትና በመሳቀቅ እንዲቆይ ህገመንግስቱ አይፈቅድም፡) ምናልባትም በቋንቋ ችግር ምክንያት የተሳሳተ አረዳድና ግንዛቤ በመያዝ ያልሆነ ነገር እንዳይናገር ለመጠበቅም በሚገባው ቋንቋ ሊነገረው እንደሚገባ ሕገመንግስቱ በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህንን ህገመንግስታዊ ግዴታ ፖሊሱ ለተያዘው ሰው መንገር መሰረታዊ ግዴታው መሆኑን አውቆ ሊተገብረው የሚገባ ነው፡፡

2.2. በሚጠየቀው ጥያቄ ያለመናገር መብት እንዳለው ይነገረዋል፡፡ (ህገመንግስቱ ፖሊስ ተጠርጣሪው ይህ መብት እንዳለው እንዲነግረው ማለትም ቃሉን ለመስጠት የማይገደድ

[58]THE PEACE MODEL OF INVESTIGATIVE INTERVIEWING:p. 25-29
[59]introduction to criminal investigation, p. 125-6

መሆኑን የመንገር ግዴታ እንዳለበት ደንግጎአል፡፡ (ህገመንግስት አንቀጽ 19(2)፡፡ ይህ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ የተጠርጣሪውን ሰብአዊ መብት ከማስከበር አንጻር መሰረታዊ ድንጋጌ ነው፡፡ ይህንን ማስጠንቀቂያ ሳይነግረው መርማሪው ቃልህን እንድትሰጥ ብሎ ቢጠይቀው ተጠርጣሪው ምናልባት ለመርማሪው ቃል መስጠት ግዴታ ነው ብሎ በማመን ቃሉን ሊሰጥ ስለሚችል፣ ይሁንና ተጠርጣሪው ቃል መስጠቱ ግዴታ እንዳልሆነ በትክክል አውቆ እንዲሰጥ ተብሎ በህገመንግስቱ እንዲካተት የተደረገ መሰረታዊ መርህ ነው፡፡

2.3. ከዚህ በተጨማሪ ይህ ተጠርጣሪው በፈቃኝነት የሚሰጠው ቃል በማስረጃነት እንደሚቀርብበት ለተያዘው ሰው ሊነገረው ይገባል፡፡ የወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ ቁጥር 27(2) ይህንኑ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

2.4. ከዚህ በመቀጠል መርማሪው የሚመረመረው ወንጀል ምን እንደሆነ ለተጠርጣሪው በዝርዝር በመንገር፣ እናም ተጠርጣሪው ያለውን ይህንን አጋጣሚ በራሱ የሚያውቀው ምን እንደሆነ የሚናገርበት መሆኑን ገልጾ እንዲናገር ይጋብዘዋል፡፡ ለምሳሌ ስለሚጠረጠርበት ወንጀልና እስካሁን ስለተሰባሰበው ማስረጃዎች በመግለጽ እንደሚከተለው ሊጋብዘው ይችላል፡፡ ‹አንተን ለመያዝ በማስረጃነት ያሰባሰብናቸው ማስረጃዎች እነዚህ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ማስረጃዎች ሌላ ትርጉም ሊኖራቸው ከቻለ ልታስረዳን ትችላለህ› ብሎ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ስለሆነም ተጠያቂ እራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን እድል ያገኝበታል ማለት ነው፡፡ አሳማኝ በሆነ መልኩ ሌላ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ማስረዳት ከቻለ ተጠርጣሪነቱ ሊቀርለት ይችላል፡፡

3. A(Account) ማለትም ተጠርጣሪው እሱ የሚያውቀውን የሚናገርበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መርማሪው ተጠርጣሪው ከተጠየቀው ውጭ እንዳይሄድ ከመቆጣጠር በስተቀር ተጠርጣሪውን ሳያቋርጠው መስማት አለበት፡፡ ተጠርጣሪው ለመናገር ካልፈለገ ወይም የተወሰነውን ብቻ ብሎ በሌላው ጉዳይ ላይ ዝምታን ከመረጠ፣ መርማሪው ቁልፍ የሆኑ ጥያቄዎችን እየጠየቀ ተጠርጣሪው ሊል የሚችለውን ቃል ለማግኘት ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ እውነትን ለመናገር ቀላል ነው፡፡ የሆነን ነገር ነው የሚነገረው፡፡ አንድ ሰው የሚዋሽ ከሆነ ግን የመጀመሪያውን ውሸት የማያሳምን መስሎ ከተሰማው ወይም የመጀመሪያውን ውሸት ይደግፍልኛል በማለት ሌላ ተጨማሪ የውሸት ሀሳቦችን ማቅረቡ አይቀርም፡፡ በዚህ መልኩ የሚሰጡ የሀሰት ቃሎች እርስ በራስ የመጋጨት እና የመጋለጥ አደጋ ስላላቸው መርማሪው አንዳንድ ጊዜ እነዚህን የሚቃረኑ ሀሳቦችን

በማውጣት ተጠርጣሪው ሀሰተኛ እንደሆነ ለማሳየት የሚችለው በመጀመሪያ ሲናገር ሳያቋርጠው ሲመዘግብ በመቆየት ነው፡፡ መርማሪው ለተጠርጣሪው የጠየቃቸውንና እና ተጠርጣሪው የመለሳቸውን መልሶች መመዝገብ አለበት፡፡ ፖሊስ የሚፈልገውን ቃል ብቻ መዝግቦ፣ የማይፈልገውን እንዲተው ህጉ አይፈቅድም፡፡ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ ቁ. 27 ተጠርጣሪው የሚሰጠው ቃል ሳይጨመር ወይም ሳይቀነስ መመዝገብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህ ቃል ወደፊት በማስረጃነት የሚቀርብበት በመሆኑ በአግባቡ ያልተመዘገበ ቃል ያልተጠበቀ ውጤትን ያመጣልና፡፡ ተከሳሹ ያልተናገርኩት ቃል ተመዝግቧል፣ ቃሌን በዚህ መልኩ አልሰጠሁም የሚል ሙግት ያስከትላልና ነው፡፡ ለዚህ በኦዲዮ ወይም በቪዲዮ መቅረጽ አንድም ቃል ሳይረሳ ሳይመዘገብ እንዳይቀር ያደርጋል፡፡

4. C (Challenge) ማለት ሲሆን ተጠርጣሪው የራሱን ታሪክና እይታ ካቀረበ በኋላ መርማሪው ተጠርጣሪውን በተለይም ደብቆአል ወይም ዋሽቶአል፣ ወይም አሳሳች የሚመስሉ ንግግሮችን ወይም ግልጽ ያልሆኑ ንግግሮቹን አድርጎአል በማለት በማስታወሻ የያዛቸውን ጥያቄዎች ለማጣራት የሚጠይቅበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መርማሪው ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ተጠርጣሪው የሚሰጣቸው መልሶችም በተመሳሳይ ይመዘገባሉ፡ ፡ በመጨረሻም የተጻፈው ለተጠርጣሪው ተነቦለት ምናልባት የሚያስተካከለው እንዳለም የሚያስተካክለው ተጽፎለት በእያንዳንዱ ገጽ ላይ እንዲፈርምበት ይደረጋል፡፡ በምርመራው ጊዜ የነበሩ መርማሪዎችም(ወይም የተጠርጣሪ ጠበቃም የነበረ ከሆነ) እንዲፈርሙበት ይደረጋል፡፡
5. E (Evaluation) የቃል መቀበሉ የመጨረሻ ደረጃ ሲሆን የተሰጠውን ቃል በመገምገም ከተጠርጣሪው ቃል ሌላ ተጨማሪ የምርመራ ስራ ያስፈልግ አያስፈልግ እንደሆነ የሚወስንበት ነው፡፡ ይሄ ውሳኔ የመጨረሻ እና የማይለወጥ አይደለም፡፡ በየጊዜው ሊለውጠው ይችላል፡፡

በመጨረሻም የተጠርጣሪው ቃል በአጭሩ በምርመራ መዝገቡ እለታዊ መዝገብ ላይ ይመዘገባል፡፡ ይሄ በመጨረሻ ለሚዘጋጀው የምርመራ ሪፖርት ጠቃሚ ነው፡፡

ተጠርጣሪው ወንጀሉን መፈጸሙን ያመነ ከሆነ መርማሪ ፖሊስ በስነስርአት ህጉ ቁ.35 አንደተደነገገው ለፍርድ ቤት አቅርቦ ይህ የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ተጠርጣሪ በምርመራ ጊዜ በፈቃደኝነት የሰጠው ቃል ማስረጃ ሊሆንበት እንደሚችል ሊገለጽለት እንደሚገባ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ

ተነግሮት በፈቃደኝነት ቃሉን ከሰጠ፣በበወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 35 መሰረትም ፍርድ ቤት ቀርቦ የሰጠው የእምነት ቃል ክስ ሲመሰረትበት ማስረጃ ሆኖ ይቀርብበታል፡፡ ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት ከቀረበ በኂላ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ብሎ በመካዱ ምክንያት በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 27 ወይም ቁ.35 የሰጠው ቃል ዋጋ ያጣል ማለት አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ቃሉን አቃቤ ህጉ ከሚያቀርባቸው ሌሎች ማስረጃዎች ጋር በመተርጎምና በመተንተን ተገቢውን የማስረጃ ክብደት በመስጠት ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡

### 2.11. የምርመራ ራፖርት ማዘጋጀትና ለውሳኔ ለአቃቤ ህግ ማቅረብ

በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 36 መርማሪ ፖሊስ ምርምራ ከተጀመረ ጀምሮ  የእለት ምርመራ መዝገብ መያዝ እንደሚኖርበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ የእለት ምርመራ መዝገብ (1) ምርመራው የተጀመረበትንና የተፈጸመበትን ቀን፣ (2) ምርመራው ሲደረግ የተወሰደውን ማናቸውንም እርምጃ (3) ምርመራው ያስገኛቸውን ሁኔታዎች (4) የተሰበሰቡትን የማስረጃ አይነቶች ሁሉ መግለጽ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ምርመራው ሲጠናቀቅ ከእለት ምርመራ መዝገቡ እና የተሰባሰቡት ማስረጃዎች በማጠናቀር መርማሪው የምርመራ ራፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡ የምርመራ ሪፖርቱ ሊይዛቸው ስለሚገቡ ጉዳዮችም በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 37 ተመልክተዋል፡፡ የምርመራ ራፖርቱ የተከራካሪዎችን ስም(ማለትም የመርማሪውን ስም እንዲሁም የተከሳሹን ስም)፣ተበዳይ ካለ የተበዳዩን ማንነት የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ፣(ስም፣ እድሜ፣ ጾታ፣ አድራሻ፣ የደረሰበትን ጉዳት፣ የተሰጠ የህክምና እርዳታ)፣ የተጠርጣሪው ዝርዝር መረጃ (ሙሉ ስም፣ እድሜ፣ ጾታ፣አድራሻ)፣ የተፈጸመው ወንጀል አጭር መግለጫ፣ ምስክሮች የሰጡት ቃል አጭር መግለጫ፣ ስለቀረበው አቤቱታ እና የነገሩን ሁኔታ ያውቃሉ የተባሉትን ሰዎች ስም፣ የተሰበሰቡትን የማስረጃ አይነቶች እንዲሁም ራፖሩ የአጠባበቅ ወይም ከዚህ የተለየ የተደረገውን ነገር ሁሉ ማመልከት አለበት ይላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የምስክርነት ቃሎቹን ተአማኒ ስለመሆኑ እና የራሱን ጥያቄዎችና ጥርጣሬዎች (ከአለው)፣ የምስክሮቹን ዝርዝር ከነአድራሻቸው፣ የኤግዚቢት ማስረጃዎች ዝርዝር፣ የተሰባሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ዝርዝርና ይዘታቸው ባጭሩ፣ በፎቶግራፍ ተነስተው ሊመጡ የሚችሉ ሊንቀሳቀሱ የማይችሉ የወንጀል ቦታ ወይም ብርበራ የተደረገባቸውን ፎቶግራፎች፣(የተሽከርካሪ፣ መሳሪያዎች ወዘተ) የያዘ ሊሆን ይገባል ይላል፡፡ በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ ገጽ 103 ላይ በሶስተኛ ሰንጠረዥ ሶስተኛ ፎርም የምርመራ ራፖር ቅጽ ተያይዟል፡፡

በፎርሙ ተራ ቁ. 3 ላይ መርማሪ ፖሊስ ‹የሚከተሉት ፍሬነገሮች መኖራቸውን አረጋግጫለሁ› የሚለው እንዲሁም በፎርሙ ተራ ቁ. 6 ‹በእኔ አስተያየት….› ስለወንጀሉና ስለተጠርጣሪዎች አስተያየት እንደሚሰጥ የተመለከቱት በመርማሪው እይታ ያመነባቸውን ፍሬነገሮችና አስተያየቱን እንዲገልጽ የሚያመለክቱ ነው፡፡ ማለትም በምርመራው ሂደት የተሰባሰቡትን የሰነድ፣ የሰው፣ የኤግዚቢት ማስረጃዎች በማመሳከር የደረሰበትን ድምዳሜ የሚገልጽ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ፖሊስ በምርመራ ሂደት አገኘሁ ባለው መረጃ ላይ ተፈጸመ ስለተባለው ወንጀል መፈጸም ወይም አለመፈጸም፣ ወንጀሉ የተፈጸመ መሆኑን ካረጋገጠ ደግሞ በወንጀሉ ተጠርጣሪ(ዎች) ተብለው ምርመራ ስለተደረገባቸው ሰዎች በወንጀሉ ተሳታፊ ስለመሆናቸው ወይም አለመሆናቸው፣ የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች አስተማማኝነት እንዲሁም ስለምስክሮች ቃል እምነት ሊጣልባቸው የሚገባ ስለመሆኑ አስተያየቱን የማስፈር ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

የወንጀል ምርመራው ሲጠናቀቅ በመርማሪው የምርመራ ሪፖርት ተዘጋጅቶ አቃቤ ህግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ይላካል፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል የወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው አጠቃላይ መርሆዎች፣ በወንጀል ምርመራ የሚሰሩ የምርመራ ስህተቶች በአጭሩ ቀርበዋል፡፡ በመቀጠልም የሙስና ወንጀል ምርመራ ስራ ሲጀመር በእቅድ መጀመር እንዳለበት፣ እቅዱ ሲዘጋጅ ሊያካትታቸው የሚገቡ ጉዳዮች ማለትም ወርቃማ የምርመራ ጥያቄዎች ምንን እንደሚያካትቱ በመዘርዘር በዚሁ መሰረት እቅዱን ማዘጋጀት ጠቃሚ እንደሆነ ቀርቧል፡፡ በሙስና ወንጀል ምርመራ ሂደት ወንጀሉ ስለመፈጸሙ ያረጋግጣሉ ሊባሉ የሚችሉ የሙስና ወንጀል ማስረጃዎች አጠቃላይ መገለጫዎች ምን እንደሚመስሉ፣ እነዚህን መረጃዎችና ማስረጃዎች ሊገኙ የሚችሉበት ቦታ የት እንደሆነ፣ የመረጃ ምንጮች፣ ማስረጃዎቹን ለማግኘት ምን አይነት የምርመራ ዘዴዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ፣ ማስረጃዎችን ለማግኘት በህግ ለመርማሪዎች የተሰጡ የምርመራ የህግ ሰልጣኞች ምን እንደሆኑ ቀርበዋል፡፡ በመቀጠልም በሙስና ወንጀል ምስክር የሚሆኑ ሰዎችን ስለመለየት፣ ግብረአበርን ምስክር ስለማድረግ፣ ምስክሮች የሙስና ወንጀል ምርመራውን አቅጣጫ እንዳያስቱ ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ፣ ምስክሮችን በመጠየቅ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ዝግጅቶችና የቅደም ተከተል ተግባራት ቀርበዋል፡፡ በሙስና ወንጀል ማስረጃዎችን ለማግኘት ብርበራና ፍተሻ ስለማድረግ በአጭሩ ቀርቧል፡፡ በመቀጠልም በሙስና ወንጀል ንብረት ስለማገድ፣ ንብረትን ስለማስተዳደር በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች አተገባበር፣ በአተገባበር ስለሚያጋጥሙ ችግሮች እና መርማሪዎች ሊያደርጉት ስለሚገባው ዝግጅትና ጥንቃቄ ተካቷል፡፡ በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ስለሚያዙበት ሁኔታ፣ ከህግ ውጭ መያዝ ስለሚያስከትለው የወንጀል እና የፍትሀብሄር ተጠያቂነትና ሀላፊነት፣ የጊዜ ቀጠሮና የዋስትና መብትን የሚመለከቱ ነጥቦች፣ የተያዙ ሰዎች መብቶች ተካተው ቀርበዋል፡፡ ተጠርጣሪን ስለመጠየቅ የPEACE ሞዴል አጠያየቅ ስርአት በአጭሩ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም በመርማሪው የሚዘጋጀው የምርመራ ራፖርት ስለሚይዛቸው ነጥቦችና ጉዳዮችን ያካተተ ሀሳብ በአጭሩ ቀርቧል፡፡

## አስረጅ ናሙና አንድ

ጉቦ የተጠየቀ ሰዉ ከጉቦ ጠያቂዉ ጋር ያደረገዉን የስልክ ንግግር በራሱ ሞባይል/ በቪዲዮ ካሜራ ቀርፆ ለፖሊስ ሪፖርት አደረገ፡፡ በተመሳሳይ ጉቦ የተጠየቀ ሌላ ሰዉ ለፖሊስ ሪፖርት አድርጎ ንግግሩን እንዲቀርጽ በፖሊስ ሃላፊ ይፈቀድለትና በተሰጠዉ የድምፅ/የምስል ከጉቦ ጠያቂዉ ጋር ያደረገዉን ንግግር ቀርፆ ለፖሊስ ሪፖርት አደረገ፡፡ በሁለቱም ጉዳዮች ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቷል፣ ይሁንና በዳኞች የተለያዩ አቋም ተይዟል፡፡ የመጀመሪያዉ ዳኛ ሁለተኛዉ አግባብ ባለዉ ሃላፊ የተፈቀደ መሆኑን በመጥቀስ ተቀብለዉ በተከሳሽ ላይ ሲወስኑ በመጀመሪያዉ ክስ በግለሰብ እንዲቀረፅ በህግ ባልተፈቀደለት ሰዉ የተቀረፀ በመሆኑ ዉድቅ ያደርጋሉ፡፡ ሁለተኛው ዳኛ በሁለቱም ሁኔታ የተገኘዉ ማስረጃ በህግ ያልተከለከለና የተፈቀደም መሆኑን ተቀብለዉ በተከሳሽ ላይ ዉሳኔ ይሰጣሉ፡፡

## አስረጅ ናሙና ሁለት

በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.31 እንደተመለከትነው ፖሊስ/መርማሪ የምስክሩን ቃል ሲቀበል ተጠያቂውን መደለል፣ ወይም እንዲደለል ማድረግ … እንደማይችል ተደንግጎአል፡፡ የጸ/ሙ/ል/ስ/ስ/ማ/አ አንቀጽ 43 በሙስና ወንጀል ተሳታፊ የሆነ ግብረ አበር በሌላ መንገድ ሊገኝ የማይችል ጠቃሚ ማስረጃን የሰጠ ከሆነ ከተከሳሽነት ወደምስክርነት ሊዞር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

## አስረጅ ናሙና ሶስት

በሙስና ተገኝቷል ተብሎ የሚገመተው የማይገባ ጥቅም ወይም የደረሰ ጉዳት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ነው፡፡ ለዚህም መርማሪ ፖሊስ በተከሳሽ ስም የሚገኝ ሆቴል ላይ እግድ እንዲሰጥ ባመለከተው መሰረት የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ይሁንና ንብረቱ በሙስና የተገኘ ንብረት በሚል ሳይሆን በሙስና ከተገኘው የማይገባ ጥቅም ወይም ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል በሚል ነው፡፡ በዚህ መልኩ እንዲከበር በተደረገ ንብረት ላይ ሊሰጥ የሚችለው እግድ ንብረቱን ለሶስተኛ ወገን ማዛወርን መከልከል ነው፡፡

## አስረጅ ናሙና አራት

በሙስና ወንጀል ተገኝተዋል ተብለው እግድ ከሚሰጥባቸው ንብረቶች መካከል ተሽከርካሪዎች ይገኙበታል፡፡ ይሁንና አሁን ባለው አሰራር ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ንብረት አስተዳዳሪ እንዲሾም አቤቱታ የሚቀርብበትና ንብረት አስተዳዳሪ የሚሾምበት ልምድ የለም፡፡ እነዚህ ንብረቶች ለረጅም ጊዜ እንዳይንቀሳቀሱ ታግደው በመቀመጣቸው ንብረቶቹ ላይ ጉዳት ከመድረሱ በተጨማሪ

ምናልባት ተከሳሽ ነጻ ተብሎ ቢወሰንበት ንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ክስ በመንግስት ላይ ሊመሰርትና መንግስት ሀላፊነት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ለምሳሌ ተሸከርካሪው ገቢ የሚያስገኝ ስራ ላይ እንዲውል ቢደረግ ተሸከርካሪው እንዲወረስ ከተወሰነም ለመንግስት ተጨማሪ ገቢ ያገኛል፣ ለተከሳሽ እንዲመለስ ከተወሰነም በተከሳሽ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ይቀንሳል፡፡

## አስረጅ ናሙና አምስት

ንብረት አስተዳዳሪ በተሾመበት ንብረት ጉዳት ቢደርስ የንብረት አስተዳዳሪው ከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ እንደሚጠየቅ በህጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ግን በጸ/ሙ/ል/ስ/ስ//ማ ህጉ አንቀጽ 12 አግባብ ያለው አካል(የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ወይም ለመክሰስ ስልጣን ያለው አካል) ንብረት ጠባቂው ንብረቱን በአግባቡ ማስተዳደሩን እንደሚከታተል፣ ንብረቱን በአግባቡ አላስተዳደረም ብሎ ካመነ ምክንያቱን በመግለጽ ለፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

## አስረጅ ናሙና ስድስት

በፍትሀብሄር ሕግ ቁ.2126(1)- የመንግስት ሹም ወይም ሰራተኛ በራሱ ጥፋት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ኪሳራውን ለመክፈል ይገደዳል ይላል፡፡ እንዲሁም በንኡስ አንቀጽ 2 የተደረገው ጥፋት የመንግስቱን ስራ ሲሰራ የደረሰ የስራ ጥፋት የሆነ እንደሆነ የተጎዳው ሰው ኪሳራ ከመንግስት ላይ ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ስለከፈለው ገንዘብ መንግስት የተባለውን ሰራተኛ ወይም ሹም መልሶ እንዲከፍለው ለመጠየቅ መብት አለው ይላል፡፡ በቁ.2127 የስራ ጥፋት ማለትም ጥፋት አድራጊው በጥፋቱ ላይ የወደቀው በቅን ልቡና በስልጣኑና ለስራው መልካም ያደረገ መስሎት የፈጸመው ሲሆን ነው ይላል፡፡ ከዚህ በላይ በቀረበው መሰረት መንግስት ላደረሰው ጉዳት እንዲከፍል ሲገደድ፣ ድርጊቱ የስራ ጥፋት ካልሆነ የመንግስት ሰራተኛው ካሳውን እንዲከፍል እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡

## አስረጅ ናሙና ሰባት

በፍትሀብሄር ሕግ ቁ.2126(1)- የመንግስት ሹም ወይም ሰራተኛ በራሱ ጥፋት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ኪሳራውን ለመክፈል ይገደዳል፡፡ ፖሊስ የተያዘውን ሰው በ48 ሰአት ሳያቀርበው ቢቀር እና አካልን ነጻ ለማውጣት ባቀረበው አቤቱታ መሰረት ፍርድ ቤት በነጻ እንዲለቀቅ ቢወስን ወይም ደግሞ የተያዘው ሰው ሳያመለክት ቆይቶ

ፖሊስ ከሁለት ወር በኋላ የተያዘው ሰው ከተያዘበት ሲለቀቅ ለሁለት ወራት ተይዤ በመቆየቴ ለደረሰብኝ ጉዳት (የሞራል እና የገቢ ማጣት) ካሳ ይከፈለኝ ብሎ በፖሊስ ተቋም እና በእስር አቆይተውት በነበሩት የፖሊስ አባላት ላይ ክስ መሰረተ፡፡

## አስረጅ ናሙና ስምንት

አንድ መርማሪ ከጥቂት ወራት በፊት ከተጠርጣሪው ጉቦ ይቀበላል፣ በዘመድና በጉቦ ነው የሚሰራው በማለት በቀረበለት ጥቆማ መሰረት ተጠርጣሪን ይይዘዋል፡፡ በፍርድ ቤት አቅርቦም በጊዜ ቀጠሮ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ አስደርጓአል፡፡ ይሁንና ስለተፈጸመው ወንጀልም ሆነ ስለተጠርጣሪው ሊጠይቃቸው የሚፈልጋቸው ምስክሮች በተለያየ ምክንያት ለጊዜው ስላልተገኙ ቃላቸውን እስካሁን መቀበል አልቻለም፡፡ ተጠርጣሪ በዋስ ልለቀቅ ይገባል ብሎ ለመርማሪው ጠየቀ፡፡

## አስረጅ ናሙና ዘጠኝ

በሰበር መዝገብ ቅ. 12. መ/ቁ. 68407(ገ. 273) ተከሳሽ በጉበት ካንሰር መታመማቸውን የሀኪሞች ቦርድ ውጭ አገር እንዲታከሙ የወሰኑበትን በማያያዝ ውጭ አገር ሄጄ እንድታከም የዋስትና መብቴ ይከበር በማለት ያመለክታሉ፡፡ ይሁንና የተከሰሱበት ወንጀል ስልጣን አላግባብ መገልገል ወንጀል (407(2) ከ7 አመት እስከ 15 አመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ዋስትና መከልከላቸውን ሰበሩ አጽንቶታል፡፡

## አስረጅ ናሙና አስር

መርማሪ ፖሊሱ የተጠርጣሪውን ቃል ሲቀበል ለሚቀርብለት ጥያቄ የሚመልሰው መልስ ረጅምና ተደጋጋሚነት ስላለው ይህንን አሳጥሮ ይጽፈዋል፡፡ በመጨረሻም የተጻፈው ቃል አንተ የገለጽከውን ቢሆንም አሳጥሬ አቅርቤዋለሁ ብሎ ያነብለታል፡፡ ተጠርጣሪውም የተነበበው ቃሌ ነው በማለት ይፈርምበታል፡፡ ይሁንና ይህ የሰጠው ቃል ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ መርማሪው የሰጠሁትን ቃል፣ ቃል በቃል አልመዘገበም፡፡ እሱ እንደፈለገው በጻፈው ላይ ፈርም ስላለኝ ነው የፈረምኩት ስለሆነም በማስረጃነት ሊቀርብብኝ አይገባም በማለት ይቃወማል፡፡ ፖሊሱም ተጠርጣሪው እንዳለው አሳጥሬ ነው ቃሉን የመዘገብኩት፡፡ ይሁንና ይህንን አስረድቼው ተስማምቶ ነው የፈረመው በማለት መልሷል፡፡

## አስረጅ ናሙና አስራ አንድ

ተጠርጣሪ በበወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 27 መሰረት የእምነት ቃል በመስጠቱ፣ መርማሪ ፖሊስ በበወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.35 መሰረት ለፍርድ ቤት ቃሉን እንዲሰጥ ያቀርበዋል፡፡ ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት ቀርቦ የእምነት ቃሉን ይሰጣል፡፡ የእምነት ቃል ጽሁፉ ላይ ይፈርምበታል፡፡ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንትም ይፈርምበታል፡፡ ይሁንና ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶበት ጥፋተኛ ነህ ወይ ተብሎ ሲጠየቅ በፍጹም አልፈጸምኩም ብሎ ይክዳል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎአል ብሎ ይመዘግባል፡፡

### የምእራፍ ሁለት የማጠቃለያ መልመጃ

**ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ሃሳብ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡**

1. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና አንድ መነሻ በማድረግ እናንተ የየትኛው ዳኛ ሃሳብ ትደግፋላችሁ?
2. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና ሁለት መሰረት መርማሪው ምስክሩን እንዲህ ብታደርግ ተከሳሽ መሆንህ ቀርቶ ወደምስክርነት እናዞርሀለን ማለቱ ማባበል ወይም ተስፋ መስጠት አይደለም ወይ? ስለሆነም የሙስና ወንጀል በሆነ ጊዜ በስነስርአት ህጉ ቁ. 31 የተደነገገው መደለል፣ የተስፋ ቃል መስጠት ተፈጻሚነት የለውም ማለት ይቻላል ወይ?
3. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና ሶስት መሰረት መርማሪ ፖሊስ ንብረቱ በንብረት አስተዳዳሪ ስር እንዲሆን ብሎ ማመልከት ይችላል? ፍርድ ቤት በአቤቱታው መሰረት ንብረት አስተዳዳሪ እንዲሾም ትእዛዝ መስጠት ይችላል?
4. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና አራት መሰረት መንግስታዊ የሆነ ንብረት አስተዳዳሪ ተቋም ቢኖር ምን አዎንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶች ይኖሩታል?
5. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና አምስት መሰረት በንብረቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት አግባብ ያለው አካል ተገቢውን ክትትል አለማድረጉ በማስረጃ ቢረጋገጥ ለደረሰው ጉዳት ከንብረት ጠባቂው ጋር ካሳ እንዲከፍል ሊገደድ ይችላል ወይ?
6. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና ስድስት መሰረት የተያዘው ሰው በክሱ መሰረት ካሳ የመክፈል መብት አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

7. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና ሰባትት መሰረት በፖሊስ ተቋም እና በእስር አቆይተውት በነበሩት የፖሊስ አባላት ላይ ክስ ቢመሰርት ካሳ የመክፈል መብት አለው ወይ?
8. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና ስምንት መሰረት መርማሪው ምን እንዲያደርግ ይጠበቃል?
9. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና ዘጠኝ መሰረት አንድ ሰው ካልታከመ በስተቀር የሚሞት ከሆነ(ህክምናው ውጭ አገር ከሆነ፣ የተከሰሰበት ወንጀል ዋስትና የሚያስከለክል ቢሆንም ዋስትናው መከልከል እንዲሞት መወሰን አይደለም ወይ?በዚህ ጉዳይ አመልካች የሆኑት በህይወት የመኖር መብት (ህገመንግስት አንቀጽ 15) ነው መቅደም ያለበት? ወይስ እስከ አስራ አምስት አመት ሊያስቀጣቸው በሚችል ክስ ከመቀጣት እንዳያመልጡ በማለት የዋስትና መብት መከልከል?
10. ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና አስር መሰረት የመርማሪው ፖሊስ ተግባር ተገቢ ነው ብለው ይገምታሉ?

ከላይ በቀረበውን አስረጅ ናሙና አስራ አንድ መሰረት ተከሳሹ በቁ.35 መሰረት ፍርድ ቤት ቀርቦ ማመኑ ጠቀሜታው ምንድነው?በሙስና ወንጀል የምርመራ ስራ ከመጀመሩ በፊት እቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?ለምን?

11. በሙስና ወንጀል ምርመራ በማስረጃ ልናረጋግጠው የሚያስፈልገን የወንጀሉ መሰረታዊ ፍሬነገሮች ምንድናቸው?
12. አንድ ሰው በመያዙ ምክንያት የሚቀነሱበት ወይም የሚጣሱበትን ሰብአዊ መብቶች ይዘርዝሩ፣
13. የሙስና ወንጀል ማስረጃዎች ሊገኙ የሚችሉት የት ነው?
14. በሙስና ወንጀል ተገኘ የተባለውን ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት ሳይጠቀስ የተጠርጣሪና ቤተሰቦችን ንብረት እንዲታገድ በሚል አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል ወይ? በዚህ መልኩ አቤቱታ ቢቀርብ ፍርድ ቤት ውድቅ ሊያደርገው ይገባል? ወይስ በተጠየቀው መሰረት እግዱን መስጠት ይችላል?
15. ህገመንግስት አንቀጽ 20(3) የተከሰሱ ሰዎች በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አላቸው ብሎ ደንግጎ ባለበት ሁኔታ እንዲያዝ በማድረግ እነዚህ መብቶቹ መጣሳቸው አግባብነት ተገቢ ነው ብለው ይገምታሉ ወይ?
16. በመያዝ ምክንያት የሚከሰቱትን ጉዳቶች ለመቀነስ እንደፖሊስ ምን ሊያደርጉ ይገባል?

17.በበወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 25. መሰረት መርማሪው ፖሊስ በመጥሪያ የጠራው ሰው ቀርቦ ለፖሊስ ቃሉን እንዲሰጥ ካደረገ በኂላ ፖሊስ የጠራውን ሰው ያለምንም ተጨማሪ ግዴታ ማሰናበት ይችላል? ያለዋስትና መልቀቅ ይችላል? በተቃራኒው ሰውየውን መያዝ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ምን ማድረግ ይችላል?

18.በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 28 መሰረት በፍርድ ቤት መያዣ ወጥቶበት የተያዘን ሰው ፖሊስ በዋስትና መልቀቅ ይችላል?

19.ተጠርጣሪ በፍርድ ቤት ወይም ያለፍርድ ቤት መያዣ ትእዛዝ ከተያዘ በኂላ ቃሉን ሲቀበል ተጠርጣሪው ወንጀል አለማድረጉን በሚያሳምን ሁኔታ ለመርማሪው ቢያስረዳው እና መርማሪውም በስህተት እንደያዘው ቢረዳ መርማሪው ምን ማድረግ ይችላል? በነጻ መልቀቅስ ይችላል? የማይችል ከሆነ ለምን? ከዋስትና ውጪ መልቀቅ አይችልም ከተባለ ሰውየው ተጠርጣሪ አለመሆኑ እየታወቀ ዋስትና እንዲያቀርብ መጠየቅ አላግባብ መብቱን መጣስ አይሆንም?

20.የተጠርጣሪን ቃልን መቀበልን በተመለከተ በተለይ የሙስና ወንጀሎች ጋር በተያያዘ አንዳንድ መርማሪዎች ወንጀሉ ስለመፈጸሙና ስለፈጻሚው በቂ የሰነድ ማስረጃ ስላለ የተከሳሽነት ቃል መቀበል ስለማያስፈልግ የምርመራ መዝገብ አደራጅተው ለዐቃቤ ሕግ የሚልኩበት አጋጣሚ ያለ ሲሆን ዐቃቤ ሕግ ደግሞ የተጠርጣሪነት ቃል ተሟልቶ ይቅረብ በማለት የሚመልስበት ሁኔታ አለ፡፡ የተጠርጣሪን ቃል መቀበል ግዴታ ነው ወይ?

21.በመርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪን ቃል ሲቀበል ሊፈጸሙ የሚችሉ የተለያዩ የማስገደድ ስልቶችን ወይም ዘዴዎችን ይዘርዝሩ፣

# ማጣቀሻ ጽሁፎች/ዋቢዎች

## አዋጆችና ደንቦች ስራ ላይ በዋሉበት አመት ቅደም ተከተል


1. የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ 1949
2. የፍትሀ ብሄር ህግ 1952
3. የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት ህግ 1954
4. የፍትሀብሄር ስነስርአት ህግ 1958
5. የልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁ 8/1967
6. የልዩ የወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ማሻሻያ  አዋጅ ቁጥር 214/1974
7. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁ. 1/1987
8. የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988
9. የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.213/1992
10. የፀረ-ሙስና ልዩ ሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/93
11. የፌዴራል ፖሊስ አዋጅ ቁ. 313/1995
12. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ 1996
13. የተሻሻለው የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/97
14. የተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/97
15. ሀብትን ለማሳወቅና ለማስመዝገብ የወጣ አዋጅ ቁጥር 668/2002
16. የጠቋሚዎችና ምስክሮች ጥበቃና ከለላ አዋጅ ቁ. 699/2003
17. የፌዴራል ፖሊስ ማቋቋሚያ አዋጅ 720/2004
18. የፌዴራል ፖሊስ አባሎች መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 268/2005
19. የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006
20. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁ. 881/2007
21. የጸረ ሙስና ልዩ ስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ማሻሻያ ቁ. 882/2007
22. የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁ. 943/2008
23. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
24. የፌዴራል የአቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 443/2011
25. የፌዴራል ፖሊስ የሙስና ወንጀል ...የክስና ጥቆማ አቀባበል ..... ማንዋል 2009
26. የኢትዮጵያ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ መመሪያ፣ 2011 ዓ.ም

27.የፌዴራል የስነምግባርና የጸረ ሙስና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 1236/2013

**የሰበር መዝገብ ቅጾች**

1. የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች መዝገብ ቅ.7. ሚያዚያ 2001ዓ.ም አዲስ አበባ
2. የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች መዝገብ ቅ.9. ህዳር 2003 ዓ.ም አዲስ አበባ
3. የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች ቅ.11. ህዲር 2004 ዓ.ም አዲስ አበባ
4. የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች ቅ.12. ህዲር 2004 ዓ.ም አዲስ አበባ

**የታተሙና ያልታተሙ መጽሀፍቶች፣ የምርመር ጽሁፎች፣ የስልጠና ሰነዶች**

5. ቢልልኝ ማንደፍሮ፣ <u>የሰበር ስርአት በኢትዩጵያ አጠቃላይ ገፅታ</u>፣ ህጋዊነት፣ ሚያዚያ (1981)
6. የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ (1993)
7. ጸሐይ ዋዳ፣ **<u>የወንጀል ሕግ መሰረታዊ መርሆዎች</u>** (አዲስ አበባ 1994 አ.ም)
8. የስነምግባርና የጸረ ሙስና ሞጁሎች (2000)፣
9. በሪሁ ተክለብርሀን፣ **<u>ለዳኞችና አቃቤ ህጎች የተዘጋጀ የወንጀል ስነስርአት ስልጠና ማንዋል(የፍትህ አካላት የስልጠና ማእከል)</u>**(ያልታተመ)(2000)
10. መስፍን ማሬ፣ **<u>የወንጀል ክስ አመራር በኢትዮጵያ</u>** (አዲስ አበባ 2013 አ.ም)
11. መካሻ አበራ እና አንሙት ላቀው፤ **<u>የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ የስልጠና ማንዋል ለማዘጋጀት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት</u>**(ያልታተመ) (2013)
12. ሰብአዊ መብትና የፖሊስ ሚና (ከፍትህ ለሁሉም የስልጠና ማንዋል)2004
13. የማስረጃ ህግ-- ለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል(ያልታተመ)
14. የኢትዮጵያ ወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ማስተማሪያ ማንዋል (በፍትህ አካላት ስልጠና ማእከል)
15. ኑር ሰኢድ፤ **<u>የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ስነስርአት</u>**

16. AFRICAN UNION CONVENTION ON PREVENTING AND COMBATING CORRUPTION
17. Amercian Bar Association website (posted on September 2019
18. Attorneys Paul Bergman & Sara J. Berman-Barrettrepresent yourself in court (2003)
19. Best Practices in Investigating and Prosecuting Corruption Using Financial Flow Tracking Techniques and Financial Intelligence A Handbook,APEC Anticorruption and Transparency Working Group (ACTWG) September 2015
20. Bryan A. Garner(ed.), *Black's Law Dictionary*, (Washington: West Publishing Co., 8th ed ., 2004).
21. CODE OF CONDUCT FOR CROWN PROSECUTORS: November 28, 2006
22. Declaration of Independence 1775
23. Fundamentals of Criminal Law (internet accessed)
24. Graham Gooch and Michael Williams, 2014, **Oxford A dictionary of Law Enforcement** (1ed), 2007
25. Google- internet / Standards of professional responsibility and statement of the essential dities and rights of prosecutors adopted by the international association of prosecutors on the twenty third day of April 1999
26. Kahsay and Andualem; law of evidence teaching material Justice and Legal System Research Institute 2009
27. International Association of Prosecutors, Standards of professional responsibility and statement of the essential duties and rights of prosecutors, April 1999
28. John Stwart Mill, On Liberty 1859 (Batoche Books Kitchener (2001)
29. Lindy Muzila and others: **On the Take Criminalizing Illicit Enrichment to Fight Corruption** (2012)

30. Mizan Law Review, The Preliminary Inquiry in Ethiopa and its Adverse Impact on the Rights of the Accused (Wondwossen Demissie Kassa) (2020)
31. OECD Corruption Investigation and Prosecution Training Manual (2012)
32. Paul Mageean, Belfast, The Role and Indepenedence of Prosecutors Northern Ireland 17 th May 2005, Cairo
33. Philipe Graven, An introduction to Ethiopian Penal Law (1965)
34. Proposed draft Evidence Code of the Federal Demorcatice Republic of Ethiopia (prepared by the Faculty of Law of Jimma University, Jimma, Ethiopia)
35. Robert H.Aronson and Donald T.Weckstein, Professional Responsibility in a Nutshell,(2d,1991)
36. Robert Klitgaard; A Holistic Approach to the Fight against Corruption; Bali, Indonesia January 29, 2008
37. ROD GEHL AND DARRYL PLECAS; Introduction to Criminal Investigaton-Processes- Practices-and- Thinking (2016)
38. The competence of supreme courts: the second meeting of central and Eastern European countries, Council of Europe, 1998
39. The Code for Crown Prosecutors. 2004/www.cps.gov.UK (internet document)
40. THE GLOBAL PROGRAMME AGAINST CORRUPTION UN ANTI-CORRUPTION TOOLKIT 2004
41. THE JUDICIAL INTEGRITY GROUP, COMMENTARY ON THE BANGALORE PRINCIPLES OF JUDICIAL CONDUCT,2007
42. A THINNING BLUE LINE? POLICE INDEPENDENCE AND THE RULE OF LAW The Police Foundation John Harris Memorial Lecture, delivered by Shami Chakrabarti, Director of Liberty, on July 2, 2008

43. THE Works of Epictitus, translated from the Greek by Thomas Wentworth Higginson, 1890, Boston

44. Transparency International, Global Corruption Report 2007

45. UN BANGALORE PRINCIPLES OF JUDICIAL CONDUCT, 2006

46. UN Code of Conduct for Law Enforcement Officials,1979

47. UN Guidelines on the Role of Prosecutors,1990

48. UNITED NATIONS CONVENTION AGAINST CORRUPTION, New York , 2004

49. UNITED NATIONS HANDBOOK ON PRACTICAL ANTI-CORRUPTION MEASURES FOR PROSECUTORS AND INVESTIGATORS (2004)

50. UNITED NATIONS *Office on Drugs and Crime* THE GLOBAL PROGRAMME AGAINST CORRUPTION UN ANTI-CORRUPTION TOOLKIT (2004)

51. Vincent Barry, **Philosophy a Text with Readings**(2nd,1983)

52. Worku Yaze Wodage; **Burdens of Proof, Presumptions and Standards of Proof in Criminal Cases** (2014)

53. Worku Yaze Wodage; **Criminalization of 'Possession of Unexplained Property' and the Fight against Public Corruption**(2014)

54. W. Todd Barron October 2017 St. John's, Newfoundland; **THE PEACE MODEL OF INVESTIGATIVE INTERVIEWING: A COMPARISON OF TRAINED AND UNTRAINED SUSPECT INTERVIEWERS**

**አባሪ1 ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ግምገማ ቼክሊስተ**

**ሰልጣኞች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች ስልጠና ከመጀመራቸው በፊት እና ስልጠና ከማጠናቀቃቸው በኋላ እንዲሞሉት ይጠበቃል፡፡**

**በቁጥሮች ትይዩ ባሉት ሳጥኖች ውስጥ የ Ö ምልክትበማድረግ ምላሻችሁን አመላክቱ**

| ተ.ቁ | ርዕስ ጉዳይ | በርዕስ ጉዳዩ ያለ የግንዛቤ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ |
| | የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወደምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን | | | | |
| | በጥቆማ ላይ የተመሰረተ የሙስና ወንጀል ምርመራ ውሱንነት | | | | |
| | ጥቆማ የማቅረብ መብትና ግዴታ | | | | |
| | ጥቆማን መመዝገብ እና ከጠቋሚው ሊገኝ የሚችለውን መረጃ | | | | |
| | ጥቆማ ሲቀርብ በጠቋሚዎች ሊመጣ ከሚችል አደጋ ስለመጠንቀቅ | | | | |
| | ጠቋሚዎችን ስለመጠበቅና ከለላ ስለመስጠት | | | | |
| | ምርመራ እንዲደረግ ስለመወሰን | | | | |
| | በሙስና ወንጀል ከሚያስከስሱት ወንጀሎች ከባድ የህግ ጥሰት የማይባሉት | | | | |
| | የወንጀል ምርመራ ምንነት | | | | |
| | የወንጀል ምርመራ የሚመራባቸው አጠቃላይ መርሆዎች | | | | |
| | የምርመራ እቅድ ማዘጋጀት | | | | |
| | ማስረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር መተንተን | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምስክሮችን ስለመለየት የምስክሮችን ቃል ስለመቀበል | | | | |
| | ንብረት ማሳገድ፣ማስከበርና ማስተዳደር | | | | |
| | ተጠርጣሪን ስለመያዝ፣ዋስትና፣ጊዜቀጠሮ እና የተጠርጣሪን ቃል ስለመቀበል | | | | |
| | የምርመራ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለውሳኔ ለአቃቤ ህግ ማቅረብ | | | | |